# አሰብ የማን ናት?

## (የኢትዮጵያ የባህር በር ጥያቄ)

በያዕቆብ ኃይለማርያም (ዶ/ር)

2003 ዓ.ም. አዲስ አበባ

© መጽሐፉን በሙሉም ሆነ በከፊል ያለ ደረሲው ፈቃድ መልሶ ማሳተም በሕግ የተከለከለ ነው።

## መታሰቢያነቱ

ለዴሞክራሲ፤ ለፍትሕና ለአንድነት ሲታገሉ ለወደቁ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊያት ነው።

ከመጽሐፉ ሽያጭ የሚገኘው ገቢ ለበጐ አድራጐት ድርጅት/ድርጅቶች ይውላል።

## ማስታወሻ

ምዕራፍ 13 ላይ የሚገኙ መጣጥፎች የኢትዮ-ኤርትራ የድምበር ውዝግብ ለድምበር ኮሚሽኑ ከመቅረቡ በፊት የኢትዮጵያ የባህር በር መብት እንዲከበር ለኢሕአዴግ ከተሰጡ ማሳሰቢያዎች በጣም ጥቂቶቹ ናቸው።

በእንግሊዝኛ ቋንቋ የቀረቡት ደግም አሰብን ወደ ኢትዮጵያ ለማስመለስ የዓለምአቀፉ ማህበረሰብ ድጋፍ ስለሚያስፈልግ ለእነዚህ ሰዎች መጠነኛ ግንዛቤ እንዲሰጥ የተዘጋጀ ነው።


## ምስጋና

ይህንን መጽሐፍ በማረምና በማስተካከል ለረዱኝ ለታዋቂው ደራሲ ለአቶ ማህለ ሥላሴ ብርሃነ ማርያም፤ ለአዝማች ይርጋ ገብሬንና ለታናሽ ወንድሜ ደነቀ ኃይለ ማርያም ምስጋዬን አቀርባለሁ።



ለአስተያየትዎ e_mail yacobhm@Gmail.Com
ስልክ 0922115987

# ማውጫ


መግቢያ……………………………………………………1

## ምዕራፍ 1

1. የባህር በር ለአገር የሚያስገኘው ጥቅምና አለመኖሩ ደግሞ የሚያስከትለው ጉዳት……………………………………11
   - 1.1. በኢኮኖሚው ዘርፍ……………………………………11
   - 1.2. በዲኘሎማሲው በኩል……………………………………20
   - 1.3. ከጠላት መከላከልን በተመለከተ ……………………………21

## ምዕራፍ 2

2. የኢትዮጵያ የባህር በር ባለቤትነት በታሪክና የባህር በር ለማስመለስ የተደረጉ ትግሎች……………………………………27
   - 2.1. የኢትዮጵያ የባህር በር ይዞታ በታሪክ……………………27
   - 2.2. የኢትዮጵያ የባህር በሮችን ለማስመለስ የተደረጉ ትግሎች……………………………………32
   - 2.2.1. የአጼ ቴዎድሮስ ትግል……………………………………32
   - 2.2.2 የአጼ ዮሐንስ ትግል……………………………………33
   - 2.2.3. የአጼ ምኒልክ ትግል……………………………………37
   - 2.2.4. ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ልዑል አልጋ ወራሽ ራስ ተፈሪ በኋላም አፄ ኃይል ሥላሴ ያደረጉት ትግል…………41
   - 2.2.5. የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር መንግሥት (ደርግ) ጥረት….44
   - 2.2.6. የባህር በር ለማዘጋት ሕወሓት/ኢህአዲግ/ ያደረገው ጥረት….48

## ምዕራፍ 3

3. ሁለተኛው የዓለም ጦርነት አሸናፊ የነበሩት አራቱ አገራት፣ የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባዔ ፣ ጣልያን ኢትዮጵያና ኤርትራን አስመልክቶ የደረሱባቸው ውሳኔዎች……………………65

ምዕራፍ 4

4. የኤርትራ በጦር ኃይል መገንጠል ኢ-ሕጋዊነትና በኢትዮጵያ የተሰጣት ዕውቅ ........................................80

ምዕራፍ 5

5. የአልጀርስ ስምምነት ኢ-ፍትሐዊነት ሲገመገም........................92
   5.1. ተዋዋዩቹ........................................................93
   5.2. የተዋዋዮች አቅም አለመመጣጠንና ኢትዮጵያ በውሉ ለሰጠችው ምንም አለማግኘቷ ......................................94
   5.3. ኢትዮጵያ ለሀላዊ ግዛቶቿን እንድታስርክብ ተገድዳ የፈረመቻቸው ውሎች................................................95
   5.4. የውሎቹ ጉድለቶችና ውድቅ መሆናቸው.......................98
   5.5. የቅኝ ግዛት ውሎች ለወሰን መካለል መሠረት እንዲሆኑ የአሜሪካ መንግሥት የተጫወተው ሚና .......................101
   5.6. ፍትሀና ዕርት ለድምበር ኮሚሽኑ ውሳኔ መሠረት እንዳይሆን የተደረገ ገደብ......................................103
   5.7. የውሉ አፈፃፀምና የኢትዮጵያ የተዛባው አካሄድ.......105

ምዕራፍ 6

6. በአልጀርስ ስምምነት መሠረት የተቋቋመው የድምበር ኮሚሽን አመሠራረትና ኮሚሽኑ የሰጠው ውሳኔ ሲገመገም......................107
   6.1. የየአገራቱ ተወካዮች ማንነት.......................................108
   6.2. የድርድሩ የጊዜ ሰሌዳ ..............................................110
   6.3. የድርድሩ ቀጣናና የአደራዳሪው ማንነት...................112
   6.4. የድንበር ኮሚሽኑ ዳኞች ማንነት ..........................114
   6.5. ዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት ወይስ የግልግል መድረክ 116
   6.6. የክርክር ፍሬ ነገሮች...............................................118

ምዕራፍ 7

7. በድምበር ኮሚሽኑ ክርክር ኢትዮጵያን የወከለው ቡድን ለኤርትራ ያስረከባቸው የኢትዮጵያ መብቶች........................124.
   7.1. በምስራቅ በኩል ............................................. ......124
   7.2. ከአሰብ በስተ ምዕራብ ያለው ቡሬ የኢትዮጵያና የኤርትራ ወሰን ሊሆን እንዴት ቻለ ?.............................................127
   7.3. ምዕራብ ትግራይ.........................................................128
   7.4. የደብር ቢዘን ገዳም.....................................................130
   7.5. የህግ አመራረጥ.........................................................131
   7.6. ሁለት ወደ አይሆንም ...................................................132
   7.7. "በያዝከው እርጋ" (UTI POSSIDETIS JURIS)............133
   7.8. የድምበር ኮሚሽኑ መሬታቸውን ወደ ኤርትራ ያካለላቸው ኢትዮጵያውያን የዜግነት መብት .......................137
   7.9. ከጦርነቱን በፊትም ሆነ በኋላ አሰብን ማስመለስ የሚያስችሉ የነበሩ ሁኔታዎች.......................................................139
   7.10. ኢትዮጵያ ሽንፈትን ከድል መንጋጋ አወጣች" (ፕሮፌሰር ክላፋም) .......................................................................143

ምዕራፍ 8

8. የድምበር ኮሚሽኑ ውሳኔ ኢትዮጵያ መሰረዝ ይገባታል......145
   8.1. የተኩስ አቁም ስምምነት መጣስ.................................145
   8.2. ምሰሶ ወይንም ችካል በወሰኑ ላይ ስለመትከል.......145
   8.3. አንዳንድ የሰላም አስከባሪ ኃይል አባላት ከኤርትራ መባረር.......................................................................149
   8.4. የሰላም ቀጣናው በኤርትራ ጦር መወረር...............153

## ምዕራፍ 9

9. የኢትዮጵያ የባህር በር መብትን አስመልክቶ የተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲዎች የሲቪክ ማህበራትና የሕዝባዊ ድርጅቶች አቋምና ያደረጉአቸው ትግሎች ....155
9.1. የፖለቲካ ፓርቲዎች ....155
9.2. የሲቪክና፣ የኃይማኖት ተቋማት በውጭ አገር ያደረጉአቸው ትግሎች ....165

## ምዕራፍ 10

10. አሰብ - የኢትዮጵያ የተፈጥሮ የባህር በር ....170
10.1. አሰብናታሪካ ....170
10.2. የአሰብ እድገት ....170
10.3. ጁቡቲ፡ አሰብን አትተካም ....174
10.4. ኢትዮጵያ የባህር በር (አሰብ) እንዳይ[illegible] የሚጠነሰሰው ሤራ ....177
10.5. አሰብ ፤ሰላምና ልማት፤ የቀይ ባህር አፋሮች ኢትዮጵያዊነት ....179

## ምዕራፍ 11

11. በአግባቡ የተስተናገደ የካሜሩንና የናይጀርያ የድንበር ውዝግብ ...184

## ምዕራፍ 12

12. የኢትዮጵያ የባህር በር ጥያቄ መደምደሚያና አንዳንድ
12.1. የመፍትሔ ጥቆማዎች .... 190

## ምዕራፍ 13

13. አባሪዎችና የተለያዩ የሕብረተሰቡ ክፍሎች አስተያየቶች ....201

## መግቢያ

ኢትዮጵያውያን በተለያዩ የታሪክ ወቅቶች በአገር ውስጥ ብቅ ያሉ አምባገነን መሪዎች የሚኑባቸው በደሎች ሰው ሠራሽም ሆኑ ተፈጥሮ የወለደቻቸው ችግሮች በትዕግስት ያስተናገዱ ሲሆን፤ኢትዮጵያውያን በትዕግስት የማይመለከቱት ነገር ቢኖር የድንበር መደፈርን ነው ማለት ይቻላል፡፡

ኢትዮጵያ ቅኝ ገዢዎች ገመድ ወጥረው ወርድዋንና ርዝማኔዋን ለኩተው አጎራባቾቿ እነማን እንደሚሆኑ ወስነው የቀረጹአት አገር አይደለችም፡፡ የጥንቱን ታሪክ እናቆየውና አፄ ቴዎድሮስ፣ አጼ ዮሐንስና አጼ ምኒልክ እንደሩሲያዊው ታላቁ ጴጥሮስ፤ እንደጣሊያኑ ጋሪባልዲ፤እንደ ጀርመኑ ቢዝማርክና ሌሎችም የዓለም ነገሥታት፤ እነዚህ የኢትዮጵያ ነገሥታትም የጎረቤት ህዝቦችን በጦር ኃይል በግዛታቸው በመጠቅለል በታልቅ ተጋድሎና መስዋዕትነት ዛሬ የምናውቃቸውን የኢትዮጵያ ዓለም አቀፍ ድምብሮችን መሠረቱ፡፡ እነዚህ ወሰኖች በኢትዮጵያ ህዝብ አጥንት የተገነቡ በደሙ የተለሰኑ ቅዱስ መሬቶች በመሆናቸው እንደ ድንበር መደፈር ኢትዮጵያውያንን የሚቀሰቅስ ነገር የለም ማለት ይቻላል፡፡ የአገር ድንበር ተደፈረ ሲባል ሕዝቡ አገሩን ለመታደግ "አመልህን በጉያህ ስንቅህን በአህያህ" ብሎ ጠመንጃውን በትከሻው አንግቶ ክተት ብሎ ወደ ጦር ግንባር መትመም የቆየ ልምዱ ነው፡፡ ያም ሆኖ ተከታታይ የኢትዮጵያ መንግሥታት በህዝቡ ላይ በፈረቃ የፈፀሙብትን በደል ችላ ብሎ አገሬ ይበልጥብኛል በማለት የሕይወት መስዋዕትነት ከፍሎ አንዳንድ ድሎችን ቢጐናጸፍም፤ በተጐናፀፋቸው ድሎች እርካብ እረግጦ ወደ ዴምክራሲ ፍትሕና ብልጽግና ሊሸጋገር አልቻለም፡፡

ቅርብ ጊዜ ኤርትራ ያልተካለለውን የአስተዳደር ወሰን በመጣስ ወደ ትግራይ ዘልቃ የኢትዮጵያን ግዛቶችን በያዘች ጊዜ ሕዝቡ በመንግሥት ላይ የነበረው የተለያዩ ቅሬታዎትን ከስሌት ሳያስገባ ልዩነቱን ወደ ጐን አድርጎ በብዙ መስዋዕትነት ጠላትን ወደ መጣበት መመለስ ቢችልም በፖለቲካ አመራር ድክመት፤ምናልባትም ከዚያም በዘለለ, ምክንያት የባህር በር መብቱን ሊያስከብር ካለመቻሉም ባለይ፤ ለዚያ ሁሉ ሕዝቡ

የተከፈለው ወርታ ዴሞክራሲን አቅጭጮ የሕዝቡ ተባተፎ አመንምኖ ሥልጣን በአንድ ፓርቲ አምባ ገነንነት ሥር ማጠቃለል ነበር።

ኤርትራ በ1983 ዓ.ም በጦር ኃይል ከኢትዮጵያ ከተገነጠለች በኋላ የኢትዮጵያ ወደ ውጭ መተላለፊያና መግቢያ የባህር በር መዘጋትን ያህል ኢትዮጵያውያንን ያስቆጣና ያሳዘነ ብሔራዊ ጉዳይ በአገሪቱ ከቶም ተከስቶ አያውቅም ቢባል ከእውነት የራቀ አይሆንም። የኢትዮጵያ የባህር በር መቀርቀር አባቶቻችንና እናቶቻችን ምስጋና ይግባቸውና በድል ከተወጡአቸው ከአድዋም ይሁን ከማይጨው የጣልያን ወረራዎች በላይ የከፋ በደል ተደርጎ በብዙ ወች ዘንድ ይቆጠራል። ይህንኑ አስተሳሰብ በማንጸባረቅ ዶ/ር አክሎግ ቢራራ"ከሁሉም የከፋና ተቀባይነት ከሌላቸው የኢሕአዴግ ፖሊሲ የኢትዮጵያን የባህር በር አሰብን ለኤርትራ መንግሥት ማስረከቡን"[1]ነው ሲሉ ጽፈዋል።

ኤርትራ በሰሜን የኢትዮጵያ ግዛቶች ላይ እ.አ.አ በግንቦት 1998 ዓ.ም ወረራ ከፍታ የኢትዮጵያ የመከላከያ ኃይል ወረራውን ለመቀልበስ በሚዋደቅበት ሰዓት የኢትዮጵያ ምሁራን፤ በእንግሊዝና በፈረንሳይ መሃከል የተደረገው የአንድ መቶ ዓመት ጦርነት እንኳን በድርድር እንደተቋጨ ሁሉ በዚህ በወንድማማቾችና በእህትማማቾች መሃከል የተከሰተው ትርጉም የለሽና አላስፈላጊ ጦርነት በኢትዮጵያ አሸናፊነት እንደሚደመደም ቢገመትም እንደማንኛውም ጦርነት ወቅቱን ጠብቆ በድርድር እንደሚጠናቀቅ አስገንዝበው ነበር። በማያያዝም በድርድሩ ወቅት የኢትዮጵያ የባህር በር መብት እንዳይጨናገፍና አሰብ ወደ ኢትዮጵያ እንዲካለል የኢትዮጵያ ህዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባርን (ኢሕአዴግን) በብዙ ተማፅነዋል። በአገር ውስጥና ከአገር ውጭ ያሉ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያዊያት ጦርነቱ ሳይቋጭ ገና ከጠዋቱ ለድርድሩ ጠቃሚ ግብአት ይሆናሉ ብለው ያመኑባቸውን የክርክር ነጥቦች በተለያዩ ጋዜጦችና ጥናታዊ ጽሁፎች በአገርና

[1] Aklog Birara, Ph.D <u>Endemic Poverty that Globalization Can't Tackle But Ethiopians Can</u>. Signature Printing (2010), p. 76.



የኢትዮጵያ ጉዳይ የለም ቢባል ማጋነን አይሆንም። ጦርነቱ እየጋመ እያለ በኢዴፓ አሰባሳቢነት በመቶ ሺዎች የሚቆጠር ፊርማ ለተባበሩት መንግሥታት ማቅረብና በኒውዮርክ በተባበሩት መንግሥታት ደጃፍ፤ "የኢትዮጵያ የተፈጥሮ የባህር በር አይዘጋም"፤ "አሰብ የኢትዮጵያ አንጡራ ሃብትና የተፈጥሮ የባህር በር ነች"፤"የአፋር ህዝብ አይከፋፈልም" የሚሉ መፈክሮችን በማንገብ ሰላማዊ ሰልፍ ማድረግን ጨምሮ፤ በሙያቸው የተካኑ በዓለም አቀፍ ደረጃ በትምህርታቸውና በሙያ ብቃታቸው የታወቁ ኢትዮጵያውያን ምሁራን ኢሕአዴግን አሳምኖ በድርድሩ ወቅት ለኢትዮጵያ የባህር በር እንዲሟገቱ ያልፈነቀሉት ድንጋይ፤ ያልማሱት ስር የለም ማለት ይቻላል። (ለአብነት ያህል ለጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ የተፃፈ ግልፅ ደብዳቤ ገፅ 213 ላይ መመልከት ይቻላል)። ከእነዚህ አገር ወዳድ ምሁራን ውስጥ ፕሮፌሰር ንጉሤ አየለ፤ አቶ በላይ አባይ፤ አቶ ዘርኡ ክሃሸን፤ ፕሮፌሰር ተክላ ወርቀ ሐጎስ፤ ሜጀር ጄኔራል አበበ ተክለሃይማኖት ካህሳይ፤ ፕሮፌሰር ጌታቸው በጋሻው፤ አቶ አሥራት አብርሃም፤ አቶ ስዬ አብርሃ፤ አቶ ሞገስ ሰለሞን፤ ፕሮፌሰር መብራሁቱ በጋዬና አቶ ገብሩ አሥራት ጥቂቶቹ ናቸው[*]።

እነዚህ ምሁራን አሰብን ወደ ኢትዮጵያ ለማስመለስ የሚያስችሉ በዋቢነት ሊጠቀሱ የሚችሉ የታሪክ፤ የሕግ፤ የፖለቲካ መረጃዎች በግል ጋዜጦችና በሌሎችም መገናኛ ብዙሃን አማካኝነት ለኢሕአዴግ አቅርበው ነበር። የቀይ ባህር አፋር ህዝብ አንድነትና ኢትዮጵያዊነት የአሰብ ባለቤትነትም ጭምር በታሪክ አስረግጠው ለኢሕአዴግ ብዙ መረጃዎችን አቅርበው ነበር።

የአሰብ ኢትዮጵያዊነት ወይንም አሰብ የኢትዮጵያ የተፈጥሮና ሕጋዊ የባህር በር መሆንዋን የማይቀበለውና ኤርትራን

[*] ከዚህ በላይ ስማቸው የተዘረዘሩት ግለሰቦች በአንድ ወይንም በሌላ ወቅት በጽሁፍ ወይንም በቃል አሰብ የኢትዮጵያ የባህር በር መሆንዋ የተከራከሩና የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ከፈነዳ ማግስት ጀምረው በጦርነቱ ወቅትና ከዚያም በኋላ ኢሕአዴግ የኢትዮጵያን የባህር በር መብት እንዲያረጋግጥ በብዙ የወተወቱ ምሁራን ናቸው

ከኢትዮጵያ "ቅኝ ግዛት ቀንበር" ነፃ ለማውጣት የተዋደቀው ሕዝብ ወያነ ሓርነት ትግራይ (ሕወሓት) አሰብ የኢትዮጵያ አካል ነች ወደ ኢትዮጵያ መታጠፍ ይገባታል ለሚሉ ኢትዮጵያውያን ኢሕአዴግ መልስ የመስፋፋት አባዜ የተጠናውተችው ናቸው በማለት ያወግዛቸዋል። በኢሕአዴግ በሻቢያ መሃከል የተደረገው ጦርነቱ በተደመደመ ማግስት ኢትዮጵያና ጣሊያን ከመቶ ዓመታት በፊት በተፈራረሙአቸው በቅኝ ግዛት ውሎችና በሌሎች ወደፊት በሚብራሩ ሕጋጋት መሠረት የኤርትራ አገራዊነትን ለማረጋገጥና የኢትዮጵያን የባህር በር ለማዘጋት ኢሕአዴግ በሶምሶማ ሩጫ ለድርድር ወደ አልጀርስ አቀና። አልጀርስ ከደረሰም በኋላ ኢሕአደግ በአጼ ምኒልክ ላይ በግድ በተጫኑ በኋላም ጣልያን እራሷ፤ ኢትዮጵያና የተባበሩት መንግሥታት በሰረዙአቸው የኢትዮጵያን የባህር በር በሚዘጉ የቅኝ ግዛት ውሎች መሠረት የኢትዮጵያን ዳር ድንበር ከኤርትራ ጋር ለመካለል ኢሕአደግ ተስማማ፡

የኢትዮጵያ የባህር በር ባለቤትነት መብትን አስመልክቶ በኢትዮጵያውያን በኩል ሁለት አቋማት ይንጸባረቃሉ። አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ ምናልባትም ከዘጠና ከመቶው በላይ አሰብ በታሪክ በህግና በሕዝብ አሰፋፈር የኢትዮጵያ የተፈጥሮ የባህር በር ነች፤ ሲሆን በዲፕሎማሲያዊ ትግል ካልሆነም አስፈላጊ በሆነ መንገድ ሁሉ ከኤርትራ ማስለቀቅ አለብን ሲል፤ ሌላው በጣም አናሳው ደግሞ አሰብ የኤርትራ አካል ነች፤ ወደ ኢትዮጵያ ለማጠፍ ሕጋዊም ሆነ ታሪካዊ ምክንያት የለም በማለት ይከራከራሉ። እነዚህ ወደብ "አስረካቢዎች" አሰብ ለኢትዮጵያ ትገባለች ባዮችን የአሰብ ኤርትራዊነትን የሚክዱ፤ የደርግና የፊውዳል ሥርዓት ርዝራዦችና አቀንቃኞች፤ የወደብ አባዜ የተጠናወታቸው፤ የሰውን አገር ለመቀማት የሚቋምጡ፤ ሰላምን የማይወዱ፤ የኢትዮጵያና የኤርትራ ሕዝቦችን በጦርነት ለመማገድ የሚፈልጉ፤ ጦርነት ናፋቂዎች፤ ለጥያቄአቸው ምንም ህጋዊም ሆነ ታሪካዊ መሠረት ሊያቀርቡ የማይችሉ ተስፋፊዎች ናቸው በማለት ያወግዙአቸዋል። ሆኖም ግን ዛሬ ይህንን አቋም የሚያራመዱ ከሕወሓትም ውስጥ ቁጥራቸው እጅግ እየተመናመነ ሄዶአል። ምናልባትም ከአቶ መለስና ዜናዊ፤ ከጥቂት የሕወሓት



አባላትና ከአገሪቱ ፕሬዝዳንት ከአቶ ግርማ ወልደ ጊዮርጊስ* በስተቀር ዛሬ የአሰብን ኢትዮጵያዊነት የሚክድ የለም።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ አቋማቸውን ቀይረው አሰብ ወደ ኢትዮጵያ እንድትታጠፍ ከሚከራከሩት ከከፍተኛ የኢሕአዴግ ባለሥልጣናት ውስጥ የኢትዮጵያ የቀድሞው የአየር ኃይል አዛዥ ሜጀር ጀኔራል አበበ ተክለሃይማኖት ካሕሣይ እንደሚከተለው ፅፈዋል።

*እ.ኤ.አ እስከ 1994 ዓ.ም የማእከላዊ ኮሚቴ አባልና ከፍተኛ የመከላከያ አዛዦች አንዱ እንደመሆኔ መጠን በጊዜው [የኤርትራ ነፃነትና የኢትዮጵያ የባህር በር ጥያቄ] አስመልክቶ የመንግስት አቋም አውቅ ነበር። የባህር በር ጥያቄ የሚያነሱ [ኢትዮጵያውያን] ሕገ መንግሥቱን በተለይም የብሔር ብሔረሰቦችን የራስን ዕድል በራስ የመወሰን [እስከ መገንጠል] የሚደነግገው አንቀፅ 39 የማይቀበሉ የፊውዳል ሥርዓትና የወታደራዊው አገዛዝ የሚናፍቁ የኤርትራ ነፃነትን የማይቀበሉ ጦርነት ናፋቂዎች አድርጌ እቆጥራቸው ነበር።*

*አሰብ ወደብ ውስጥ ብቻ የነበረው የኢትዮጵያ ሃብት ዝርፊያ [2]የባህር በር ጥያቄ እንዳነሳ ቀስቃሰኝ። ለምን [ሕዋሃት/ኢሕአደግ] ይህንን አቋም እንደወሰደ ታሪክ እስኪያጣራ ምስጢር ሆኖ ይቆያል። ሆኖም ለኔ ምክንያቱ ድንቁርናና አጉል ትዕቢት ነው[3]።*

---

* በኤርትራና በኢትዮጵያ መሃከል የተደረገው ጦርነት ተጠናቅቆ ህዝቡ ስለ አሰብ ጉዳይ የሞቀ ውይይት በሚያደርግበት በአንድ ወቅት ክቡር ፕሬዝዳንቱ፡ አሰብ የኤርትራ ሉዓላዊ ግዛት መሆንዋን በኢትዮጵያ ቴሌቭዥን በተገለጸው ዘገባ ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል። ከዚያም በኋላ፤ይህንን አቋማችውን ለመለወጣቸው ምንም ማስረጃ የለም።

[2] "ከአሰብ ወደብ ብቻ ከኢትዮጵያ የተዘረፈው ንብረት ከአምስት መቶ ሚሊዮን ብር አያንስም። ይህም የመንግሥትና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ንብረት አይጨምርም። ባለቤቶቹ የባንክ ባለዕዳ ሆነዋል"። ብዙነህ እሸቱ ከፍጥጫው በስተጀርባ (ጥናታዊ ፅሁፍ)፤አዲስ አበባ፤የካቲት 12 ቀን 1997.ዓ.ም ገፅ 90

[3] Abebe T. Kahsay "Ethiopia's Sovereign Right of Access to the Sea Under International Law". A Thesis, University of Georgia, Athens, Geogia (2007) (unpublished).

የቀድሞው ከፍተኛ የኢሕአደግ ባለሥልጣንና የመከላከያ ሚኒስትር የነበሩት አቶ ስዬ አብርሃ ተመሳሳይ አቋም በማንፀባረቅ የኢሕአደግን ስህተት ሲገልጹ "ጦርነቱ አይቀሬ ከሆነ የራሳችን [የሕወሓት] እምነትና ጠባብ አመለካከት ብቻ ሳይሆን ከታሪክና ከአገራችን ጥቅም አኳያ የአገራችንን ምሁራኖች አማክረን የባህር በር የምታገኝበት መንገድ ቀይሰን ያንን በሚያረጋግጥ መልኩ እንዲፈፀም ማድረግ ይገባ ነበር። ሊረሳ የማይቻለው በወቅቱ የሠራነው ስህተት ይሄ ነው። ይህ ደግሞ ያመጣው የራሳችን ግትርነት ነው። እኔ ብቻ ነኝ ትክክል ብሎ መጭጭ ማለት ራስን መፈተሽና የሌሎች ሃሳብ ለማድመጥ አለመሞከር የኖረ የድርጅቱ ችግር ነው"[4] ሲሉ አቶ ስዬ ጸጸታቸውን ገልጸዋል።

በአሁኑ ጊዜ ብዙዎች የኢሕአደግ አባላት በኢትዮጵያ የባህር በር መዘጋት እንደ ብዙዎቻችን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያዊያት ከቁጭት አልፎ እንደሚበግኑ አያጠራጥርም። በተመሳሳይ መልኩ ከፍተኛ የሕወሓት/ኢሕአዴግ አመራር አባላት የነበሩ ግለሰቦች፤ የአሰብ በኤርትራ መያዝ በአገር ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያደረሰ መሆኑን በመገንዘብ በነበራቸው አቋም መጸጸታቸውና የኢትዮጵያን የባህር በር መብት ለማስከበር እንደሚታገሉ በአደባባይ ቃል ገብተዋል። አንዳንዶቹ ሁኔታው በፈቀደ ሁሉ እየታገሉም ነው። በምሳሌነትም አቶ ገብሩ አስራት የቀድሞው የሕወሓት ከፍተኛ ባለስልጣና የትግራይ አስተዳዳሪ የነበሩ በአሁኑ ወቅት የትግራይ ለዴሞክራሲና ሉዓላዊነት ፓርቲ (ዓረና) ኘሬዝዳንትና የኢትዮጵያ ፌደራላዊ መድረክ (መድረክ) ሊቀመንበር፤ እንዲሁም ሕወሓት ውስጥ ከፍተኛ ሥልጣን የነበራቸውና አሁንም የመድረክ የሕዝብ ግንኙነት ሃላፊ አቶ ስዬ አብርሃ፤ የዓረና የሕዝብ ግንኙነት ሃላፊ አቶ አሥራት አብርሃምና ሌሎችንም መጥቀስ ይቻላል።

የዚህ ጽሁፍ ዋናው ዓላማ ታሪክን፣ ዓለም አቀፍ ሕግን፤ የቀይ ባህር አፋሮች አንድነትና መብትን ከግንዛቤ አግብቶ፤ የአሰብ ወደብ ሕጋዊ ባለቤት ኤርትራ ወይስ ኢትዮጵያ ነች ለሚለው

[4] ሪፖርተር እሁድ የካቲት 07 ቀን (2003)ዓ.ም.



ጥያቄ ለሚያነሱ ምላሽ ለመስጠት መሞከር ሲሆን ለዛሬም ሆነ ለነገው ትውልዶች አንዳንድ ግብአት ለመስጠትና የአሰብ ጉዳይ እንደ አሁኑ በኢትዮጵያውያን አእምሮ እየተንቀለቀለ እንዲኖርና ምላሽ እስኪያገኝ ድረስ ከዋነኛ ብሄራዊ አጀንዳነት እንዳይወርድ ለማድረግ ነው።

የጽሁፉ ተጨማሪ ዓለም የኢትዮ-ኤርትራ የድምበር ኮሚሽን በዘሄግ ኔዘርላንድስ እ.አ.አ ኤፕረል 13 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መገምገም አይደለም። የድምበር ኮሚሽኑ ውሳኔ በዚህ ጽሁፍ የተጠቀሰው፤ ውሳኔው ለኢትዮጵያ የባህር በር መዘጋት ያደረገው አስተዋጽኦ በሚመለከት ብቻ ነው። ጠቅላላው የድምበር ኮሚሽኑ ውሳኔ ግምገማ የአካባቢው ጂኦግረፊ፤ ታሪክና የሕዝብ አሰፋፈር ጠንቅቆ በሚያውቅ ሰው እንዲሚደረግና ስህተቶች ወይንም እድሎዎች ካሉ እንደሚያወጣቸው ተስፋ ይደረጋል። በዚህ አንጻር አቶ በላይ አባይ <u>የኢትዮጵያ መንግሥት ብሄራዊ ግዛቶችን ለኤርትራ ሰጠ</u> (<u>The Ethiopian Regime Cedes National Territories to Eritrea</u>,1991) በሚለው መጽሐፋቸው ያደረጉት ጥረት የሚመሰገን ነው።

ዶ/ር አክሎግ ቢራራ እንደሚሉትም "አብዛኛው ኢትዮጵያዊ ኢትዮጵያ ወደብ አልባ በመሆንዋ የሚደርስባት ጉዳት ጠንቅቆ ያውቅ እንደሆነ ግልፅ አይደለም። እንደ አብዛኛው አገራዊ ጉዳይ ይህንንም ገዢው ፓርቲ አዳፍኖት ተቀምጦአል"[5]። ስለሆነም ገዢው ፓርቲም ስህተቱን ተገንዝቦ እርማት ለማድረግ ወይንም ወደፊትም የሚያደርገው የዲፕሎማሲያዊም ሆነ ሌላ ጥረት ስለሌለ ለባለጉዳዩ ለኢትጵያ ሕዝብና ለመጪው ትውልድም በተቻለ አቅም ግንዛቤ ማስጨበጥ የጽሑፉ ሌላው ዓላማ ነው።

ፅሁፉ በመጀመሪያ የአንድ አገር የወደብ ባለቤት መሆን የሚያመጣው ጥቅም ወደብ አልባ መሆን ደግሞ የሚያስከትለው ጉዳት ከኢኮኖሚው ልማት፤ የአገሩ ሰላምና ደህንነት ከማረጋገጥና ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ ሕብረተሰብ ዘንድ ከሚ...ት

5 Aklog Birara, PhD. supra note 1, p.77.

ተጻማጭነት አኳያ ምን ያህል ጫና እንደሚጥል ለመዘርዘር ይሞክራል። ቀጥሎም ኢትዮጵያ በታሪክ የነበራት የባህር በር ባለቤትነት በአጭሩ በመገምገም የኢትዮጵያ ጠላቶች አቶማን ቱርኮች፣ ግብፆችና ጣሊያኖች የሰሜኑ የኢትዮጵያ ግዛቶች በመቆጣጠራቸው ለተወሰነ ጊዜ ቢሆንም ኢትዮጵያ ከቀይ ባህር አካባቢ መገለልዋን በአጭሩ ያትታል። በመቀጠልም የኢትዮጵያ የባህር በር ለማስመለስ ከሕወሓት/ኢሕአደግ በስተቀር በየጊዜው በአገሪቱ የተፈራረቁ መንግሥታት ምን ያህል እንደኳተኑ ይዳስሳል። በማስከተልም የኢትዮጵያን የባህር በር መብትን አስመልክቶ የዓለሙ ሕብረተሰብና የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባዔ ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ቲያምድሞ የኤርትራን የወደፊት እጣ ፈንታ በወሰነበት ጊዜ የወሰዱት አቋም ምን ይመስል ነበር የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ይሞክራል።

ጽሁፉ እ.አ.አ በታህሣሥ 2000 ዓ.ም በኢትዮጵያና በኤርትራ መካከል በአልጀርስ ስተፈረመው የወሰን መካለል ስምምነት መሠረት የሆኑት ጣሊያን በግድ በኢትዮጵያ ላይ የጫነቻቸው የ1900፣1902፣ እና 1908 ውሎች (treaties) በሕግ ፊት ውድቅነት ይተነትናል። ቀጥሎም ጣሊያን በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ከተሸነፈች በኋላ የቀድሞው የጣሊያን ቅኝ ግዛቶች የነበሩት አገራት መጻኢ ዕድል እንዲወስኑ የተሰየሙት አራት ኃያላን አገራት አሜሪካ እንግሊዝ፣ፈረንሳይ፣የሶቭየት፣ኅብረትና የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባዔ በዋናነት የኢትዮጵያ የባህር በር ባለቤት እንድትሆን ከኢትዮጵያ ጋር አዲስ አሳሪ ውል በመዋዋል ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ዘውድ ስር በፌዴሬሽን እንድትቀላቀልና ኢትዮጵያ የባህር በር ባለቤት እንድትሆን መወሰኑ ጽሁፉ ይተነትናል።

ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ዘውድ ስር በፌዴሬሽን እንድትተሳሰር በሁለተኛ የዓለም ጦርነት ድል አድራጊ አራቱ ኃያላን አገራትን በመወከል የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባዔ ጣልያንና ኢትዮጵያ የተፈራረሙት ውል ተጥሶ የኢትዮጵያ የባህር በር መብት ሙሉ በሙሉ ለመዝጋት ያበቃው የአልጀርስ ስምምነትና የድምበር ከሚሽኑ ውሳኔ ሲሆን የስምምነቱና



የውሳኔው ኢ-ሕጋዊነት እንመረምራለን። ኢትዮጵያና ኤርትራ በፌዴሬሽን ሲተሳሰሩ ቀጥሎም ፌዴሬሽኑ በኤርትራ ፖርላማ ውሳኔ ፈርሶ ውህደት ሲፈጥሩ የኢትዮጵያ የባህር በር መብት መረጋገጡን አመላክተን ኤርትራ ከኢትዮጵያ ስትገነጠል የኢትዮጵያ ሉዓላዊት የባህር በር አሰብን ይዛ መሄድዋ ሕገ ወጥ ድርጊት መሆኑን እንፈትሻለን።

ጹሁፉ አሰበን ወደ ኢትዮጵያ ለማካለል የነበሩ እድሎች በኢሕዴግ ድክመት እንዳመለጡ ከዘረዘረ በኋላ የኢትዮጵያ የባህር በር [አሰብን] ማስመለስ የሁሉም ኢትዮጵያዊ ብሔራዊ ግዴታ እንደመሆኑ መጠን እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ አቅሙ የሚፈቅደውንና ሊያደርግ የሚችለውን እንዲያደርግ ይማጸናል። በመጨረሻም የአሰብ ጉዳይ የሁለት ወንድማማቾችና፣ እህትማማቾች፣ ሕዝቦች ሰላምና መልካም ጉርብትናን በሚያጉለበትና ፍትሐዊ በሆነ መልኩ እንዲፈታ አንዳንድ አማራጭ ሃሳቦችን ጠቁመን ጽሑፉን በዚሁ እንዘጋዋለን።

# ምዕራፍ 1

## 1. የባህር በር ለአንድ አገር የሚያስገኘው ጥቅምና አለመኖሩ ደግሞ የሚያስከትለው ጉዳት

### 1.1. በኢኮኖሚው ዘርፍ

ኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት የተለያዩ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች እንደዘገቡትና የኢትዮጵያ መንግሥትም እንዳረጋገጠው ከ አራት ሚሊዮን በላይ አረሃብተኞች የሚገኙባት አገር ስትሆን ሥራ አጥነት፣ የአካባቢ ውድመት፣ ጣራ የነካ የኑሮ ውድነትና ከፍተኛ የህዝብ ቁጥር ግሽበት በሰፊው ተንሰራፍተውባት ከመጨረሻ ድሀ ከሚባሉት አገራት ተርታ ትሰለፋለች። ኢትዮጵያ እነዚህን ችግሮችን ሁሉ ታቅፋ ኢሕአደግ በ1983 ዓ.ም በኢትዮጵያ ሥልጣን ከመያዙ በፊት አስር ሳንቲም መክፈል ቀርቶ እንዲያውም ከፍተኛ የገቢ ምንጭ ለነበረው የወደብ አገልግሎት ዛሬ አገሪቱ በቀን ከሦስት ሚልዮን ዶላር በላይ ለጅቡቲ ትከፍላለች። ይህ ለወደብ የሚከፈለው በጣም ከፍተኛ ገንዘብ ውሃ እንደበላው የሚቆጠር ነው። ምክንያቱም በለውጡ ኢትዮጵያ የምታገኘው ዕቃም ሆነ ገንዘብ ወይንም ሌላ ጥቅም የለምና። ይህም ማለት ድህነትን ለመቅረፍ ሊረዱ ይችሉ የነበሩ በየዓመቱ ሃያና ሰላሳ ፋብሪካዎች ሊገነባ የሚችል ወይንም መጠነ ሰፊ ለሆነ መሠረተ ልማት ግንባታ ሊውል ይችል የነበረ ገንዘብ በሕወሓት መሪዎች የዲፕሎማሲና በሌሎች ሌሎችም ደካሞቶች ምክንያቶች ኢትዮጵያ ይህንን ሁሉ ገንዘብ ለጅቡቲ ትገብራለች።

የኢትዮጵያ የወጪና የገቢ ንግድ የሚካሄደው አብዛኛው በባህር ላይ ሲሆን ኢትዮጵያ የኬንያ፣የሱዳን፣የጅቡቲ፣አንዳንዴም የሶማሊያ ወደቦች ትጠቀማለች። ሆኖም ኢትዮጵያ ወደ ውጭ የምትልከውና ከውጭ የምታስገባው ጠቅላላ ንግድ 90% በዱባይ

የወደብ ባለሥልጣን በሚተዳደረው በጅቡቲ በኩል ነው[6]:: አ.ኤ.አ በ3 ሜይ 2009 በአፍሪቃ ፐሬስ ኤጀንሲ እንደተዘገበውና እንዲሁም የኢትዮጵያ የመገናኛ ሚኒስቴር እንደገለጸው ኢትዮጵያ በአንድ ወደብ ላይ ብቻ በመንጠልጠልዋ የንግዱን እድገት አቅጭጮታል:: እንዲሁም ለጅቡቲ ወደብ በኢትዮጵያ በኩል የሚከፈለው ታሪፍ በየጊዜው እየጨመረ በአንድ ወቅት በአንድ ጊዜ 25% ጭማሪ ታሪፍ መቆለልዋ የሚታወስ ነው[7]::

የአሰብ ወደብ በአካባቢው ካሉ ኢትዮጵያ ልትጠቀምባቸው ከምትችል ወደቦች በሙሉ ለመሃል አገሩ የቀረበች ነች:: የኬንያው ሞምባሳ ወደብ ለሰሜኑ ኢትዮጵያ ከሺህ ስምንት መቶ ኪሎ ሜትር በላይ የሚርቅ ሲሆን በኬንያና በኢትዮጵያ መሃከል ያለው የመኪና መንገድም የተበላሸና ለከባድ የጭነት መኪኖች አዳጋችም ነው::

[6] Getachew Begashaw, Ph.D ``Port of Assab as a Factor for Economic Development and Regional Conflict`` http//ethiomedia.Com. Accessed on January 8, 2010.

በሆነ ምክንያት ጅቡቲ ከኢትዮጵያ ጋር የሚያገናኛት መንገድ ቢዘጋና ወደቡ ለጥቂት ቀናት እንኳን ለኢትዮጵያዝግ ቢሆን የሚያስከትለው ጉዳት ሲታሰብ ያስደነግጣል::. በኢትዮጵያ በኤርትር ጦርነት ጊዜ እንዲህ ዓይነት አደጋ እንደሕሰት ኢሕአደግ በጂቡቲ ወደብ አካባቢ 4000 የሚጠጋ የኢትዮጵያ ጦር አሰፍሮ እንደነበር ይነገራል::

[7] Id.



ሠንጠረዥ 1

በአዳስ አበባና በአካባቢዋ የሉት ወደቦች መሃከል ያለው እርቀት በኪሎ ሜትር

| | | |
|---|---|---|
| አዲስ አበባ | ሞምባሳ | 1804 |
| አዲስ አበባ | ፓርት ሱዳን | 1696 |
| አዲስ አበባ | ሞቃዲሾ | 1520 |
| አዲስ አበባ | በርበራ | 943 |
| አዲስ አበባ | ጅቡቲ | 910 |
| አዲስ አበባ | አሰብ | 624 |

ምንጭ [8]

በዚህ ሰሌዳ መሠረት ዕቃ ጭነው ከጅቡቲ ወደ አዲስ አበባ የሚመጡ ወይንም ከአዲስ አበባ ወደ ጅቡቲ የሚሄዱ መኪኖች አሰብ ደርሰው ከሚመጡ መኪኖች ወደ አንድ ቀን የሚጠጋ ተጨማሪ ጉዞ አለባቸው ማለት ነው:: ለዚህ ጉዞ የነዳጅ ወጪ፣ሹፌሮች የሚያጠፉት ጊዜና በመኪናዎቹ ላይ የሚደርሰው ብልሽት እንዲሁም ለወደብ የሚከፈለው ታሪፍ በሙሉ ቢተመን በአገሪቱ ላይ ከፍተኛ የኢኮኖሚ ክስረት እንደሚያስከትል ማንም አይስተውም::

እንደ ኢትዮጵያ ወደብ አልባ የሆኑ አገሮች ከዋና ዋና የንግድ ማዕከሎች የተገለሉና ከንግድ ማዕከሉ የራቁ ሲሆኑ ወደብ አልባነት

[8] Id.

ለኢኮኖሚ እድገታቸው ከፍተኛ ማነቆ ሆኖባቸዋል፡፡ ቻውድሪና ኤርዳነቢልግ የተባሉ ምሁራን ባደረጉት ጥናት መሠረት አንድ ወደብ አልባና ወደብ ያለው በሌላ በሁሉም ነገር ተመሳሳይ የሆኑ ሁለት አገሮች ብንወስድ ወደብ አልባው አገር በኢኮኖሚ እድገቱ በ1% ወደብ ካለው አገር ወደ ኋላ ይቀራል፡፡ ይህም ማለት ወደብ ያለው አገር በ24 ዓመት ውስጥ ኢኮኖሚው በእጥፍ ሲያድግ ወደብ አልባው አገር ኢኮኖሚው በእጥፍ እንዲያድግ 36 ዓመታት እንደሚፈጅበት እነዚህ ምሁራን ያረጋግጣሉ[9]፡፡ በሌላ ጥናት እንደተረጋገጠው ደግሞ ወደብ አልባ በመሆን ብቻ የአንድ አገር የውጭ ንግድ መጠን ከ33% እስከ 43% ሊቀንስ ይችላል፡፡ ዶ/ር አክሎግ ቢራራ በቅርብ ጊዜ ከሰሃራ በታች በሚገኙ አገራት የተደረገ ጥናት ሲጠቅሱ ከሰሃራ በታች የሚገኙ ወደብ አልባ አገራት የውስጥ ለውስጥና ወደ ወደቡ የሚያሸጋግረው የትራንስፖርትና ተያያዥ ወጪዎች ወደብ ካላቸው አገራት በአራትና በአምስት እጅ እንደሚበልጥ ይገልጻሉ፡፡ ይህም ከዕቃው ሽያጭ የሚገኘው አብዛኛውን ገንዘብ ይወስደዋል ማለት ነው፡፡ ይህም ማለት ኢትዮጵያ ወደ ውጭ የምትልካቸው ምርቶች ዋጋቸው ስለሚንር በዓለም ገበያ ተወዳዳሪ ሊሆኑ አይችሉም፡፡ እንዲሁም ወደ አገር የሚገቡ ሸቀጦች ዋጋቸው በጣም ከፍ ይላል፡፡ ይህም በመሆኑ ገዥው ፓርቲ የአሰብ ወደብ ለኤርትራ በማስረከቡ የአገሪቱ ደህንነትና እድገቷ በከፋ ሁኔታ ላይ ጥሎአል ማለት ነው[10]፡፡

በ2008 ዓ.ም በዓለም 44 ወደብ አልባ አገሮች ሲኖሩ ከእነዚህ ውስጥ ሠላሳ አንዶቹ ድሃ ሲሆኑ አሥራ ሦስት ደግሞ የድሃ ድሃ የሚባሉ ናቸው፡፡ አሥራ ሦስቱም የድሀ ድሀ አገሮች አፍሪካ ውስጥ የሚገኙ ሲሆን ኢትዮጵያም ከእነዚሁ አሥራ ሦስቱ ድሃ አገሮች ተርታ ትሰለፋለች፡፡ እነዚህ ወደብ አልባ ድሃ አገሮች ወደ ውጭ የሚልኳቸው ምርቶቻቸው በአብዛኛው በአንድና በሁለት ሰብሎች ወይንም በአንድ በሁለት በእንዱስትሪ

[9] Chowdhury A.K and Erdnebileg Sondagdory. Geography against Development:
A Case for Landlocked Countries, United Nations, (2008) p. 77

[10] Aklog Birara, Ph.D. supra note 1 p.78



ውጤቶች ወይንም ጥሬ እቃ የተወሰኑ ናቸው፡፡ ስለሆነም ከድህነት የመላቀቅ እድላቸው በጣም የመነመነ መሆኑ ሊቃውንት ይናገራሉ፡፡ የኢኮኖሚ ልማት ሊቅ ፖል ኮልየር (Paul Collier) "የመጨረሻዎቹ ድሃ ቢሊዮኖች (The Bottom Billion) በሚለው መጽሃፋቸው ቀጥሉ ያለውን አስፍረዋል፡፡ "ድሃ በሆኑ አካባቢዎች የሚገኙ ወደብ አልባ አገሮች ከአራቱ የልማት ማነቆዎች በአንዱ [በወደብ አልባነት] ተጠፍረው የቱያዙ ናቸው፡፡ የባህር በር ካለህ ገበያህ መላው ዓለም ነው፡፡ የባህር በር ከሌለህ ደግሞ ገበያህ የጎረቤት አገር ብቻ ነው"[11]፡፡ ስለሆነም አገራት ወደብ አልባ ላለመሆን ጥረት ያደርጋሉ፡፡ ኮልዬር በተጨምሪ ወደብ አልባ አገሮች የጎረቤቶቻቸው እስረኞች ናቸው[12] ብለዋል፡፡

እንዲሁም ጄፍሪ ሳክስ (Jeffrey Sachs) የተባሉ የኢኮኖሚ ልማት ሊቅ የባህር በር የሌለው አገር ከሚገጥሙት ዋነኛ የኢኮኖሚ ችግሮች ወደብ አልባ መሆን ገልፀዋል፡፡ በመቀጠልም የባህር ጠረፍ ለኢኮኖሚ ልማት የላቀ ሚና ይጫወታል ማለት ማጋነን አይደለም፤ የባህር በር አለመኖር ደግሞ በጠቅላላው ለአንድ አገር የኢኮኖሚ ልማት ወደ ኋላ መቅረት ዋነኛ ምክንያት መሆኑን ጄፍሪ ሳክስ ይገልፃሉ[13]፡፡

በተጨማሪም ኪሾር ኦፕሬቲ (Kishor Uprety) የተባበሩት መንግሥታት የንግድና የልማት ኮሚሽንን (United Nations Commission on Trade and Development) በመጥቀስ የባህር በር አለመኖር ለኢኮኖሚ እድገትና ለልማት ዋነኛ እንቅፋት መሆኑን ያረጋግጣል ብለዋል[14]፡፡

[11] Path Cother, The Bottom Billion. Why the Poorest Countries are Felling and what Can Be Done About it Oxford University Press, (2007) p.54-63

[12] Id

[13] Fayc. M. Macarthur, J.Sachs, J Snow. T. " The Challenges Facing Land Locked Developing Countries," Journal of Human Development.(1) (2004)

[14] Kishor Uprety "Right of Access to the Sea of Land Locked States Retrospect and Prospect for Development". Journal of

ይህንኑ በማረጋገጥ፤ "የተባበሩት መንግሥታት የዓለም የመጨረሻ ድሀ አገሮች ተወካይ" ሚስተር ቻይክ ሲዲ ዲያራ በአዲስ አበበ በተደረገ ስብስባ ተገኝተው ወደብ አልባ አገሮች ለእድገት የሚያስፈልግ እርዳታ ቢጨመርላቸውም፤ ዕዳ ቢሰረዝላቸውም፤ በዓለም ገበያ ለመሳተፍ ሁኔታው ቢመቻችላቸውም፤ በዓለም ኢኮኖሚ ያላቸው ድርሻ የበይ ተመልካች ሆነው እንደቀሩና መሠረታዊ ለውጥ ማስመዝገብ እንዳልቻሉ ገለጡ[15]።

የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ መለስ ዜናዊ በታቃራኒው የባህር በር ለአንድ አገር እድገት ምንም የሚጫወተው ሚና እንደሌለ በመግለጽ የሚከተለውን ብለዋል።

"…..አሁን የአሰብንም የምጽዋንም ወደብ አንጠቀምም። እነዚህ ወደቦች ባለመጠቀማችን ምንድን ነው የቀረብን ነገር የለም። ልማት ቢሆን በኢትዮጵያ ታሪክ ትልቅ ልማት፤ፈጣን ልማት የተመዘገበው በአለፉት አራት ዓመታት ነው። ስለዚህ ወደብ ስላመኖሩ እረሃብ አያመጣም፤ በጐረቤት አገር ወደብ በመጠቀም መሥራት ይቻላል። ያለ ነገር ነው። ስለዚህ ኢትዮጵያ ያለወደብ ቀረች ብለን የምንቆጭበትና የምናዝንበት ምክንያት የለም። ወደብ አለመኖር አይጐዳንም፤ ሊጐዳንም አይችልም። ወደብ በነበረን ጊዜ ኢትዮጵያ ድሀ ነበረች። አሁን ወደብ የለንም። እድገት ግን እያስመዘገብን ነው። ስለዚህ ለማደግ ወደብ አስፈላጊ አይደለም"[16] በማለት የወደብ ጠቃሚነት አጣጥለዋል።

ከላይ የተጠቀሰው የአቶ መለስ አባባል በባህር በር መዘጋት የሚበግኑና የሚበሳጩ ስፍር ቁጥር የሌላቸው ኢትዮጵያውያንን አያጽናናም፤ ምክንያቱም ሀቁ ከላይ የጠቀስናቸው በጣም የታወቁ የኢኮኖሚ ልማት ሊቃውንት ከሚሉት ፍጹም የተለየ ብቻ ሳይሆን ተቃራኒም ነው።

---

International Legal Studies, 21(1995)

[15] አባይ ሚድያ ሰኔ 11 ቀን 2000ዓ.ም.

[16] እሥረት አብርሃም ከአገር በስተጃርባ፤ሕዋሀትና ሻቢያ የትርያ ፈረስና የባለፋረሱ ተልኮ 2ኛ ዕትም ሕዳር 2003 ገጽ 156



ለአንድ አገር ልማት አስፈላጊ ከሆኑ ዋነኞቹ ግብአቶች አንዱ ከውጭ ወደ አገር የሚገባውና በሥራ ላይ የሚውለው ገንዘብ (foreign investment) ነው። አንድ የውጭ ኢንቬስተር በሌላ አገር ገንዘቡን ሥራ ላይ ከማዋሉ (ኢንቬስት ከማድረጉ) በፊት የሚጠይቃቸው አያሌ ጥያቄዎችና የሚያደርጋቸው ምርምሮች አሉ። ከእነዚህም ጥያቄዎቹ ከዋነኞቹ አንዱ የሚያመርተው ምርት እንዴት አድርጎ ወደ ዓለም ገበያ ማዝለቅ እንደሚችል ሲሆን ለዚህም እስተማማኝ የሆነ በቅርብ የሚገኝ ብዙ ወጪ የማያስወጣው መገናኛ መኖርና አለመኖር ነው።

ወደብ አልባው አገር የሚያመርተው ዕቃ ግዙፍ ዓይነት ከሆነ በየብስ ትራንስፖርት ወደ ባህር ተሸጋግሮ ከዚያም ወደ ዓለም ገበያ ለማዝለቅ ወጪው ቀላል አይሆንም። ስለዚህ አንድ ኢንቬስተር በአንድ አገር ውስጥ መዋለ ንዋዩን በሥራ ላይ ከማዋሉ በፊት ይኸ አገር የባህር በር ባለቤት ነው ወይስ አይደለም የሚለው ወሳኝነት ያለው ጥያቄ ይጠይቃል።

አገሩ የባህር በር ከሌለው በባህር በሩና ዕቃው ከተመረተበት አካባቢ ያለው እርቀት ከረዘመ ለወደብ ግልጋሎት የሚከፍለው ገንዘብ ከፍተኛ ከሆነ በወደቡና ዕቃው በተመረተበት መሃከል ያለው መንገድ ጥራት ከጐደለው ኢንቬስተሩ ገንዘቡ ሥራ ለይ የሚያውልበት የተሸለ አማራጭ ይፈልጋል ።

በኢትዮጵያ የኢንዱስትሪም ሆነ የእርሻ ውጤቶች የሚመረቱት ከወደቡ በራቀ አካባቢ በአብዛኛው በመሃሉና በምዕራቡ የአገሪቱ ክፍል ስለሆነ እነዚህን ምርቶች ወደ ወደቡ ለማዝለቅ ብዙ ወጪ ይጠይቃል። ስለሆነም ከባድ ዕቃ ለማምረት ለሚፈልግ ኢንቬስተር ወደብ አልባዋ ኢትዮጵያ የመጀመሪያው ምርጫ አትሆንም። በእርግጠኝነት ለልማት ጠቃሚ የሆነውና ለብዙ ዜጎች የሥራ እድል የሚከፍተው ቴክኖሎጂ ወደ አገር የሚያስገባው የኢንቨስትመንት መስክ የከባድ ዕቃ ማምረቻ ኢንዱስትሪ ወይንም ፋብሪካ ነው። በኢትዮጵያ ሁሉም ነገሮች ተስተካክለው ቢገኙ እንኳን ወደብ አልባ በመሆንዋ ብቻ እንደዚህ ካሉ ኢንቬስትመንቶች የመቋደስ ዕድሏ በጣም ይቀንሳል።

ቀይ ባህር ወደ አፍሪቃ፤ ባብኤል መንደብ፤ሜዲቲሪንያንና ሕንድ ውቅያኖስ የሚያሸጋግር ከፍተኛ ትራፊክ የሚያስተናግድ መስመር ነው። ወደ እነዚህ አካባቢ,የሚጓዙ መርከቦች አሰብ ላይ በሚቆሙበት ጊዜ ከፍተኛ ገቢ ያስገባሉ። ቀደም ሲል ከዚህ ዘርፍ ኢትዮጵያ ትሰበስበው የነበረ ገቢ ከአሰብ ወደ ኤርትራ መታጠፍ ጋር ወደ ኤርትራ መንግሥት ካዝና ይገባል ማለት ነው። እንዲሁም የወደብ ግልጋሎት ብዙ ሠራተኛ የሚይዝ ሲሆን ከአሰብ ወደ ኤርትራ መታጠፍ ጋር የብዙ ኢትዮጵያውያን የሥራ እድልም ተዘግቶ እነዚህ ሠራተኞች ለብዙ ጊዜ አዲስ አበባ መጠለያ ጣቢያዎች ውስጥ ሰፍረው በችግር ይንገላቱ እንደነበር ይታወቃል።

አሰብ ከፍተኛ የቱሪስት መስብህ ስትሆን ባህሩም በአሳ ሃብት የበለፀገ መሆኑ ተረጋግጧል። ወደ 1960ዎቹ መባቻም በአሰብ አካባቢ ከከርሰ ባህር የፈነዳው የተፈጥሮ ጋዝ አሰብ የነበሩ መሃንዲሶች መዝጋት ተስኖአቸው ፍንዳታውን ለመዝጋት መሳሪያዎችና ኢንጂነሮች ከሊቢያ ነበር የመጡት ። ስለነዳጅ እውቀት ያላቸው ሰዎች የተፈጥሮ ጋዝ ፈንድቶ መውጣት ከተፈጥሮ ጋዝ ሌላ በተጨማሪ በአካባቢው ነዳጅ (ቤንዚን) መኖሩ ዓይነተኛ ማስረጃ መሆኑ ያረጋግጣሉ። በተጨማሪም በቀይ ባህር ልዩ ልዩ እንደ ማንጋኒዝ የመሳሰሉት ማዕድናት መኖራቸው በተለያዩ ጊዜያት ተጠቁሞአል።

ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት ኢትዮጵያን ለከፍተኛ ኪሣራ የሚዳርጉ ሁኔታዎች እያሉ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚንስትር አቶ መለስ ዜናዊ እ.አ.አ. በ2000 ዓ.ም "አሰብን ወደ ኢትዮጵያ እንመልስ ማለት ከኢትዮጵያ መንግሥት እምነትና መርህ ውጭ ነው። አሰብ የምንታገልለት ጉዳይ አይደለም፡ ሌሎች አማራጭ ወደቦች አሉን። አሰብ በመሄዱ ምንም አላጣንም። ስለዚህም ነው እሁንም በድርድር [በአልጀርስ] ወቅት አሰብን ያላነሳነው"[17] ብለው ነበር። ሁኔታው እርሳቸው እንደሚሉት ሳይሆን የአሰብ ወደ ኤርትራ መታጠፍ በኢኮኖሚው ላይ ያስከተለው ጉዳት በአሃዝ አስልቶ

[17]መለስ ዜናዊ እ.አ.እ በጁን 20 ቀን 2000ዓ.ም ከአሜሪካን ድምፅ ራድዮ ጋር ያደረጉት ቃለ ምልልስ



መናገር ይቻላል። በአጭሩ ሌላ ሌላው ሳይዘረዘር ከላይ እንደተጠቀሰው ኢትዮጵያ በዓመት ለወደብ አገልግሎት በቀን ከሦስት ሚሊዮን ዶላር በላይ እንደምትከሰክስ የአደባባይ ምስጢር ነው።

በአገር ደረጃ ከለይ የተገለጸው እንዳለ ሆኖ፤ ወደብ አልባነት ከእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ የቀን ተቀን ኑሮ ጋር ቁርኝት አለው። በአሁኑ ወቅት በአገሪቱ ለተከሰተው በየቀኑ ወደ ሰማየ ሰማያት የሚመጥቀው የብዙ ኢትዮጵያውያን ሕይወት የስቃይ ኑሮ ያደርገው የእቃዎች የዋጋ መናር እጅግ ውድ የሆነው የወደብ አገልግሎትና ቀረጥ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው። በዚህ በአስጨናቂ ጊዜ ኢትዮጵያ የራስዋ ወደብ ቢኖራት ኖሮ ለሰው ሕይወት አስፈላጊ የሆኑትን ምግብን የመሳሰሉ ሸቀጣ ሸቀጦች ከቀረጥ ነፃ ወይንም አነሰተኛ ቀረጥ ተከፍሎባቸው ቢገቡ ለተከሰተው የኑሮ ውድነት ማስተንፈሻ በሆነ ነበር።

በዓለም የበለጸጉ ጥቂት ወደብ አልባ አገሮች እንዳሉ ሲታወቅ በእነዚህ አገሮች አካባቢ የሚገኙ ሰፋፊ ገበያና የዳበረ ኢኮኖሚ በመጠቀም የወደብ አገልግሎት አለመኖር የሚያስከትለው ጉዳት መቀነስ ችለዋል። እነዚህ አገራት የደረጁ የመገናኛ አውታሮችና መጓጓዣዎች በመጠቀም ያለ ብዙ ችግር ወደ ወደብ ይዘልቃሉ። ለምሳሌ ያህል ኦስትርያ ሉክሳምቡርግ እና ስዊዘርላድ ወደብ አልባ ቢሆኑም ወደብ አልባነቱ እጅግም አልጉዳቸውም። ድሀ በሆኑ አገሮች ግን ወደብ አልባነት የአንድን አገር ንግድ ከላይ እንደተጠቀሰው ከ33% እስከ 43% ስለሚቀንሰው ይህንን በመረዳት የተባበሩት መንግሥታት እነዚህ ወደብ አልባ አገሮች ወደ ውጭ የሚልኩዋቸውና ከውጭ የሚያስገቡአቸው ዕቃዎች በቀላሉና በተቀላጠፈ መልኩ እንዲከናወኑ በተባበሩት መንግሥታት በውሳኔ ቁ. 1028 (x1) በ2002 እና 2003 ዓ.ም. የወደብ ባለቤት የሆኑ አገሮችን ጠይቋል[18]።

[18] United Nations Resolutions, No. 1028 (x1) 2002 and 2003

## 1.2 በዲፕሎማሲው በኩል

ኢትዮጵያ ከ90 ሚሊዮን በላይ ሕዝብ ያላት እና በሕዝብ ብዛት በአፍሪቃ ሁለተኛዋ አገር ስትሆን፣ የአፍሪቃ ሕብረት ዋና ጽህፈት ቤት፣ የተባበሩት መንግሥታት የአፍሪቃ ኢኮኖሚክ ኮሚሽንና ሌሎችም ዓለምአቀፍ ድርጅቶች አዲስ አበባን ቤታቸው አድርገዋል። ከእነዚህ አንጻር ሲታይ ኢትዮጵያ በዓለምም ሆነ በአፍሪቃ የተባ የዲፕሎማሲ ሚና ልታደርግ የምትችልና የምትደመጥ አገር መሆን ይገባት ነበር። አሁን ግን እንደሚታየው በዲፕሎማሲው ድክመት ምክንያት ብቸኛ መውጪያና መግቢያ የባህር በርዋ ከመዘጋት በተጨማሪ ሉዐላዊነቷ ለአደጋ ሊጋለጥ በሚችልበት ሁኔታ ውስጥ ትገኛለች። የአለም 70% የንግድ ዕቃዎች ከሚተላለፉበት እጅግ ስትራተጂክ ከሆነው ከቀይ ባህር አካባቢ በመገለልዋ በአካባቢው ተሰሚነትና ክብር ከባህር በሮቿ ጋር ሄደዋል። ለዚህም ማስረጃ የሚሆነው አሜሪካኖችና ምዕራባውያን ሽብርተኞችን ለመዋጋት ኃይላቸውን ያደራጁት ጅቡቲ ውስጥ ሲሆን ጅቡቲ ለዚህ ግልጋሎትዋ ብዙ ጥቅማ ጥቅሞችን ታገኛለች ። ዛሬ ጅቡቲ ሲያሰኛት በኢትዮጵያ ላይ ከምትቀልለው ከፍተኛ የወደብ አገልግሎት ክፍያና ሌሎችም በርካታ ክፍያዎች ከአሜሪካና ከምዕራባውያን በምታገኘው ገቢ በታሪክዋ ታይቶ የማይታወቅ የኢኮኖሚ እድገት በማስመዝገብ ላይ እንደላች ይነገራል ከዚህ ቀደም እንደነበረው ሳይሆን ዛሬ ጅቡቲ የሚያስፈልጋትን ነገር ሁሉ ከኢትዮጵያ መግዛቱን ቀንሳ ከተለያዩ የአረብ አገሮች ጋር የነበራትን የንግድ ግንኙነት ስለአጠናከረች ኢትዮጵያ በጅቡቲ ላይ ሊኖራት የሚችል ሚና እምብዛም ነው።

አረቦችም ከብዙ ጊዜ ጀምሮ ብቸኛ የቀይ ባህር ተቀናቃኛቸው የነበረችው ኢትዮጵያን ከባህሩ አካባቢ አግልለው ቀይ ባህርን የአረብ ሃይቅ (Arab Lake) ለማድረግ ሲታገሉለት የነበረው ዓላማቸውን አሳክተው ዛሬ በአብዛኛው ቀይ ባህር "የአረብ ሃይቅ" ሆናለች።

ስለሆነም በቀይ ባህር በተለይ በአሰብ የኑክሌር መሣሪያ ቢጠመድበትና የጠላት ጦር ቢሰፍርበት፤ ለኢትዮጵያ ለህልውናዋ



ሥጋት የሚፈጥር ሁኔታ ቢጠነሰስባት ይህንን ለመከላከል ኢትዮጵያ ልታደርገው የምትችል ምንም ነገር አይኖርም።

## 1.3 ከጠላት መከላከልን በተመለከተ

ኢትዮጵያ በድንበር ዘለል ወንዞችዋ፣ በታሪካዊና በጂኦ-ፖለቲካዊ ምክንያቶች በአንዳንድ በመካከለኛው ምሥራቅ አገሮች በጠላትነት የተፈረጀች አገር ለመሆንዋ ጥርጥር የለውም። ከዚህ ቀደም እንዳልተኙላት ሁሉ አሁንም ወደፊትም እንደማይተኙላት በገቢር አረጋግጠዋል። በዓለም ሁኔታዎች ከፍተኛ ዕውቀትና ተሞክሮ ያላቸው አቶ በላይ አባይ የኤርትራ የአረብ ሊግ ታዛቢ አባል መሆን አረቦች በቀይ ባር ያላቸውን የበላይነት እምብዛም እንዳማይቀንሰው አሳሰበው፤ አቶ አባይና አቶ ዘሩዕ እንደሚከተለው አስጠንቅቀዋል። "ኢትዮጵያ የባህር በር ኖሮአት ካልተቋቋመቻቸው በስተቅር የታሪክ ጠላቶችዋ በባህር በር በኩል ገብተው ነው የሚያንቋት። እንደ ጥንቱ ግብጽ በአባይ ላይ ባላት ጥቅም ምክንያት ኢትዮጵያ አባይን ለልማትዋ እንዳታውል ግብጽ ኢትዮጵያን ማተራመስዋን ትቀጥላለች"[19]።

"ኤርትራና ሶማሊያ ቀይ ባህርንና ሕንድ ውቅያኖስን ሲቆጣጠሩ ኢትዮጵያን ለማነቅ እድሉ ይኖራቸዋል። በተጨማሪም ኢትዮጵያ አገልግሎቶችና ሸቀጥ ታስገባበት የነበረው ወደብም ኢትዮጵያን ለመሰለል ተግባር ይውላል"[20]። የእነዚህ ሰዎች አባባል ከዚህ በፊት በገቢር እንደታየው በኢትዮጵያ ጥናት የታወቁ ፕሮፌሰር ሃሮልድ ማርከስ (Harold Marcus) ታሪክን በማጣቀስ የሚከተለውን አሰገንዝበዋል።

*ኢትዮጵያና ፈረንሳይ በ1908 ዓ.ም. ከጅቡቲ እስከ አዲስ አበባ ስለተገነባው ባቡር ስምምነት ባደረጉበት ወቅት በአንቀጽ 11*

---

[19] See Belai Abbai and Zeru Kihishen, "Meles" Assab Policy Threatens,Ethiopia's.National.Security," http://www.ethiopians.com/belai_and_zeru.htm,(July15,2000), Accessed on January 12, 2011.

[20] Ibid.

*በጦርነት ጊዜ ሁሉ ባቡሩ በኢትዮጵያ ግልጋሎት ስር ይውላል የሚለውን በመጣስ እ.አ.አ.በ1935/1936 ዓ.ም. ጦርነት ጊዜ ኢትዮጵያ የጦር መሣሪያ በጅቡቲ በኩል ለማስገባት ስትሞክር ፈረንሳይ ውሉን በመጣስ አሻፈረኝ ብላ ከለከለች። ይህ መሣሪያ የማስገባት ክልከላ ለኢትዮጵያ በጦርነቱ መሸነፍ ከዋነኞቹ ምክንያቶች አንዱ ነበር። ኢትዮጵያ ወደ ባህር የሚያዘልቀውን ባቡር ብትጠቀምም ወደብ አልባ ከመሆን አልዳነችም። ኢትዮጵያ ከባህሩ አካባቢ የሚያገለግሉት የቅኝ ገዢዎች ውል ባትቀበላቸውም ካለወደቦችዋ በጕረቤት አገራት ቅኝ ገዢዎች ጫና ስር መውደቅዋ አልቀረም። ባልያኖች በጦርነቱ ወቅት በኢትዮጵያ ወታደር ላይ ከነስነሱት በዓለም ሕግ ከተከለከለው የመርዝ ጢስ ውጭ ኢትዮጵያን በጦርነቱ ለሽንፈት የዳረጋት ቀጥተኛና ወቅታዊ ዋነኛ ምክንያት የምድር ባቡር በፈረንሳይ የፖለቲካ ጫና መውደቁ ነው። ይህም ማለት በአጭሩ ለኢትዮጵያ በጦርነቱ መሸነፍ ዋነኛው ምክንያት ወደብ አልባ መሆንዋ ነው[21]።*

እንግዲህ ኢትዮጵያ ለጠላት ጥቃት የተጋለጠች እንደመሆንዋ መጠን መከላከያ ኃይልዋን ማጠናከር ይገባታል ማለት ነው። ለዚህም የመከላከያ ኃይልና መሣሪያ መኖሩ የግድ ይላል። ተፈላጊው መሣሪይ ማለፍ ያለበት በሌላ አገር ወደብ አድርጐ በመሆኑ እንቅስቃሴው እክል ሊገጥመው ይችላል። የዓለም አቀፍ ሕግ እንደሚደነግገው አንድ ወደብ አልባ አገር ሰላማዊ ዕቃዎችን በሌላው አገር ወደብ የማስተላለፊ መብት አለው። ይህ የሚሆነው ግን ባለወደቡ አገር የሚጠይቃቸው ሥርዓቶችንና ክፍያዎችን ፈጽሞ ሲገኝ ነው። ባለወደቡ አገር በወደቡ ላይ ሉዓላዊ መብት ስላለው የፈለገውን ቅድመ ሁኔታዎችን ከማስቀመጥ የሚያግደው ነገር የለም። ለምሳሌ አንዱ አገር የጦር መሣሪያ በወደቡ አድርጎ ወደ አገሩ ለማሻገር ቢፈልግ ይህ ከጠላት ለመከላከለ ከሚያስፈልግህ በላይ ነው በማለት ማስተላለፍ ሊከለክለው ስለሚችል የወደብ አልባው አገር ሉዓላዊነቱ ዘወትር በቋፍ ላይ ነው ማለት ይቻላል።

---

[21] See, Marcus Harold, <u>Ethiopia, Great Britain and the United States,</u> 1941-1974, University of California Press, (1983), p.238.



የባህር በር ከኢኮኖሚው ጠቀሜታ ይልቅ የአገርን ነፃነትና ደህንነት ከማረጋገጥ አንጻር የሚኖረው ሚና የላቀ ነው። በአንድ ወቅት የኢትዮጵያው ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ መለስ ዜናዊ ወደብ ሸቀጥ ማስተላለፊያ መሆኑና እራሱም ሸቀጥ ስለሆነ እንደማንኛውም ሸቀጥ ዋጋ አወዳድሮ ከረከሰበት ሄዶ መግዛት እንደሚቻል ተናግረው ነበር። ሆኖም ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ካሉት በተቃራኒው ወደብ ከሸቀጥነቱ አልፎ የሕልውና ጥያቄ መሆኑ ብዙዎቹ ይቀበሉታል። ሳሙኤል ፒዮአት ሜንፊ (Samuel Pyeatt Menfee) ስለኢትዮጵያ የባህር በር መዘጋት የሚቀጥለውን ብለዋል። "ከአፍሪቃ ቀንድ በሕዝብ ብዛት አንደኛ፤ በአህጉሪቱ ደግሞ ሦስተኛ [በአሁኑ ወቅት ሁለተኛ] የሆነችው አገር ወደብ አልባ በመሆንዋ ደህንነትዋ በቋፍ ላይ ተንጠልጥሎአል[22]። ጠቅላይ ሚኒስትሩ የባህር በር የአገርን ነፃነትና ደህንነትን በማረጋገጠ በኩል ያለው ወሳኝነት ሳይገነዘቡት ቀርተው ሳይሆን ሸቀጥ ማስተላለፊያ ነው ያሉት ኤርትራ የአሰብን ወዳብ በመከልከልዋ ምክንያት የሚበግነውን ሕዝብን ለማዘናጋት ይመሳሳል።

በባህር በኩል አድርጎ የሚመጣን ወራሪ ኃይል ለመመከትና እዚያው ባህሩ ውስጥ ማስቀረት ከመሬት ውጊያ በጣም የቀለለ ለመሆኑ የጦር ስልት አዋቂዎች ይናገራሉ። ወደብ አልባ አገርን ለመውረር በወደብ በኩል ገብቶ ወደ ተወራሪው አገር ለመዝለቅ በየብስ አድርጎ ከመሄድ በባህሩ በኩል መግባት የቀለለ መሆኑ እነዚሁ የጦር ስልት አዋቂዎች ይናገራሉ[23]። ኢትዮጵያ በተደጋጋሚ ጠላቶችዋ በቀይ ባህር በሚገኙ የባህር በሮች በኩል አድርገው ገብተው የአገሪቱን የሰሜን ክፍል ይዘው ነው ወደ መሃል አገር የዘለቁት። የእንግሊዙ ጀኔራል ናፒዮር አጼ

---

[22] Samuel Pyeatt Menefee, "The Oar of Odysseus: Landlocked and Geographically Disadvantaged States In Historical Perspective", 1992, 23 <u>Cal.W.Int'l L.J.</u>1 Cited in Abebe T. Kahsay supra note 3

[23] ብርጋድዬር ጀኔራል ተሰፋዬ ሃብተ ማርያም፤ የአብዮታዊት ኢትዮጵያ ወደር የሌለው ጀግና፤ ግንቦት 5 ቀን 2003 ዓ.ም ከዚሁ ፀሐፊ ጋር ባደረጉት ውይይት የገለፁት

ቴዎድሮስን ለመውጋት ወደ ኢትዮጵያ የገባው በዚሁ በቀይ ባህር ወደብ በኩል በዘይላ አድርጎ ነው።

አቶ ኃይለ ሚካኤል ገብረአናንያ የቀድሞው የተባበሩት መንግሥታት ባለ ሥልጣን፤ ከኤርትራ ጋር የተደረገውን ጦርነትን አስመልክቶ በጦርነቱ ወቅት በሰጡት ቃለ ምልልስ በቅርብ ጊዜ የሆነውን በመገምገም.... "ወደ ኤርትራ የሚጫነው የጦር መሣርያ ኢትዮጵያን ለመውጋት መሆኑን ገልጸው የራሳችን የባህር በር ቢኖረን ኑሮ ጠላት የኢትዮጵያ መሬት ሳይረግጥ መሣሪያውን መቆጣጠር ይቻል እንደነበር አሁን ግን ዘመሬታችን ድረስ እስኪደርስ እጃችንን አጣምረን እያየን በመሆኑ ቅሬታቸውን ገልጸዋል[24]።

ከታሪክ መረር ተሞክሮዎች በመነሳት ነበር ኢትዮጵያ በምጽዋ ጠንካራ የባህር ኃይል ገንብታ የአገሪቱ የጦር መርከቦች ባለቤት በመሆን የኢትዮጵያ የጦር መርከቦች ቀይ ባህርን እያሰሱ እስከ ሜዲቴራንያንና ሕንድ ውቅያኖስ ድረስ ይዘልቁ የነበረው። እንደዛሬ ኢትዮጵያዊነት በዘር በሚመነዘርበት ዘመን የመጀመርያ የጦር መርከብ ስሙ "ዘርዓይ ደረስ" ይባል እንደነበር መዛግብት ያስረዳሉ።[25] ዛሬ ሁኔታው በሙሉ የተገላቢጦሽ ሆኖ አሰብ የነበረው የባህር ኃይሉ ቅርንጫፍ ጣቢያ (base) በኤርትውያን እጅ ወድቆ እንደጥንቱ አሰብ ኢትዮጵያን ለማጥቃት ዋነኛ መግቢያ በር ልትሆን እንደምትችል መገመት አያዳግትም።

በሻቢያና በደርግ መካከል የነበረው ጦርነት ተደምድሞ አሰብ የነበረው የባህር ኃይሉ ማዕከል ተዘግቶ የኢትዮጵያ የባህር ኃይል ተበታትኖ ወደ የመን ይሸሹ ከነበሩት የባህር ኃይሉ አባላት አንዱ እንዲህ ሲል አንጎራጉረ ይባላል።

[24] ኃይለ ሚካኤል ገብርአናንያ ሪፖርተር እሁድ የካቲት 7ቀን 2002

[25] ኢትዮጵያ የባህር ጠረፍና ባህር ኃይሏ፤ (አዲስ አበባ) ፤ (2000 ዓ.ም)፤ገጽ 494.



*የባህር ኃይላችን መልሀቅ የጣለበት፤*
*የጠቅል አሽከሮች በፓሪስ በኒውዮርክ የተሟገቱለት፤*
*የአሉላ ፈረሶች ውሀ የጠጡበት፤*
*የኢትዮጵያ ወጣቶች ዋና የዋኙበት፤*
*የት አለ ባህሩ በደም የማልንበት?* *

ከዚህ በታች በዝርዝር እንደተገለጸው የኑክሌር መሣርያ ለመታጠቀ መንፈቅ የሚቀራት የኤርትራና የግብጽ ወዳጅ ኢራን በአሰብ አካባቢ ጦርዋን አስፍራለች የሚለው ዘገባ በአንድ ወቅት በዓለም አቀፉ ሚዲያዎች ተደምጦአል።

ኢትዮጵያ ከኤርትራ ጋር በጠላትነት እስከ ተፋጠጠች ድረስ አሰብ የጠላት መርከብ ማረፊያ ሆና የጦር አይሮፕላኖች ከመርከቦች ወይንም ከወደቡ እየመጠቁ ተነስተው መሃል ኢትዮጵያን ለማጥቃት ይችላሉ። ወይንም ጠላት ጦሩን አሰብ ላይ አስፍሮ ወደ ኢትዮጵያ ለመዝለቅ አመቺ የሆነ በኢትዮጵያ ድሀ ገበሬ ሃብት የተገነባ ጥሩ መንገድ አለለት።

- ለማጠቃለል አንድ አገር የወደብ ባለቤት መሆንና አለመሆን ለአገሩ ድክመትና ጥንካሬ ምን ያህል ወሳኝነት እንዳለው ፕሮፌሰር ሺመት ሲሻኝ፡ የራሳችን ታሪክ በመጥቀስ ቁልጭ አድርገው እንደሚከተለው፡ አስቀምጠውታል።

*ኢትዮጵያ በታሪኳ ያለፈቻቸው መነሳትና መውደቅ ከባህር ጋር ከነበራት ቅርበትና ርቀት ጋር ቀጥተኛ የሆነ ግኙነት አለው። የባህር በሮቿ በእጇ በነበሩበት ዘመን የጉላበተችና የበለፀገች ኢትዮጵያን መመሥረት ተችሎአል። በአንፃሩ የባህር በሯን በተነጠቀችባቸው ዘመኖች ኢኮኖሚዋ የከሰሰ ባሕሏ የደበዘዘ ፓለቲካዊ የተናጋ ኢትዮጵያን በተደጋገሚ አይተናል። በኢትዮጵያ እጅግ ፈንጣባራቂ የነበርው የአክሱም ሥልጣኔ እንዲያ መግነኑ በሌላ አጋጣሚ ባልሆን አክሱም፤በቀይ ባህር*

* በአቶ አሥራት አብርሃም ከአገር በስተጀርባ ህዳር 2003 ገጽ 9 ላይ በተለየ መልኩ ቀርቧል።

*ጠረፍ ላይ በገነባችው የበላይነት ምክንያት ነበር። አዱሊስን ዋና በር በማድረግ በወቅቱ በነበረው ዓለማቀፋዊ ንግድ በማንባር ቀደምትነት በመሳተፏ አክሱም እስካሁን የሚያስደንቀው ብሩህ ሥልጣኔ መገንባት ቻለች[26]።*

ለአሁኑ የኢትዮጵያ ትውልድ የሚቀርበው ግልጽ ጥያቄ ኢትዮጵያ ወዳብ አልባ ሆና ኢኮኖሚዋ የኮሰሰ በህሏ የደበዘዘ ፓለቲካዋ የተናጋ ሆኖ ትቀጥላለች ወይስ የባህር በር ኖሮአት ጥንት በአንድ ወቅት እንደነበርችው የጉለበተችና የበለጸገች ትሆናለች፤ መልሱ አሰቸኳይ ነው። ምክንያቱም በኮሰሰችና በደበዘዘች ኢትዮጵያ ውስጥ መኖር የሚፈልግ ኢትዮጵያዊ የለምና።

[26] ሹመት ሲሻኝ፣ ፕሮፌሰር፣ ጦቢያ መጽሔት፣ጥር 6 ቀን 1993 ዓ.ም ገጽ20.



# ምዕራፍ 2

## 2. የኢትዮጵያ የባህር በር ባለቤትነት በታሪክና የባህር በር ለማስመለስ የተደረጉ ትግሎች

### 2.1. የኢትዮጵያ የባህር በር ይዞታ በታሪክ

ኢትዮጵያ የባህር በር ባለቤት እንደነበረች በመጀመሪያ የታወቀው ከ100 እስከ 150 ዓ.ም. ባለው ጊዜ ውስጥ እንደተጻፈ በሚገመተው በፒሪፕለስ ኦቭ ዘ ኤሪትሪያን ሲ (PERIPLUS OF THE ERYTHREAN SEA) በሁሰኘው መጽሐፍ ነው። ይህም መጽሐፍ የአክሱም መጠነ ሰፊ ንግድ በዋነኛው የባህር በርዋ በአዱሊስ በኩል ይተላለፍ እንደነበረ አትቶአል[27]።ቀጥሎም ኮስሞስ (Cosmos) የተባለ ሰው በጻፈው የክርሲቲያን ፎቶግራፊ (Christian Photography) በሚለው መጽሐፍ አዱሊስን መጐብኘቱና በጊዜው የነበረው ንጉሠ ነገሥት አጼ ካሌብ እንደነበረ አጼ ካሌብም እጅግ የዳበረ የባህር ኃይል እንደነበረውና ቀይ ባህርንም ተሻግሮ የመንንና ደቡብ አረቢያን ይቆጣጠር እንደነበር ጽፎአል[28]።

የአክሱም መዳከምና የዛጉዌ ሥርወ መንግሥት ሥልጣን ላይ መውጣት ኢትዮጵያን የባህር በር አሳሳጣትም ነበር። ነገሥታቱ በቀጥታም ይሁን ወይንም በጥገኞቻቸው (Vassals) አማካይነት የቀይ ባህር ወደቦችን ይቆጣጠሩ ወይንም ይገለገሉ ስለነበር

[27] W.H Schoff ed. The Periplus of the Erythrean Sea,1912 p.4, cited in Moges Solomon "Outlet to the Sea and Ethiopia's claim over the port of Assab," Thesis, Addis Ababa University Faculty of Law, (May 2003) (Unpublished)

[28] Ibid

አክሱም ሙሉ በሙሉ ከቀይ ባህር የተገለለችበት ጊዜያት ጥቂት ነበር ማለት ይቻላል።

የባህር በርን በቀጥታ በቁጥጥር ስር በማዋል ኢትዮጵያን የባህር በር ባለቤት ያደረጓት አጼ ዘርዓ ያዕቆብ (1434-1468) ሰሜን ትግራይና ደጋውን ኤርትራ በመቆጣጠር የግብጽ ጥገኞች ይፋቶችን ድል አድርገው ቀይ ባህርን ሊቆጣጠሩ በቻሉበት ወቅት ነበር[29]።

ከዚያም በኋላ ቱርኮች ምጽዋን ከመያዛቸው ቀደም ብሎ ጥንታዊት ኢትዮጵያ በቀይ ባህር ዳርቻ ላይና ታቹ የባህር በሮች እንደነበሩአት የታሪክ ጸሐፍት ያረጋግጣሉ። እነዚህ ወደቦችም አዱሊስ፣ ገምበዛን፣ ዘይላና ምጽዋ ይባሉ ነበር። የዘይላ ወደብም ዋነኛው የይፋቶች ሡልጣን መኖርያ እንደነበርና ሡልጣኖች ደግሞ የኢትዮጵያ ነገሥታት ጥገኛ በመሆናቸው ኢትዮጵያ በተዘዋዋሪ የባህር በር የዘላ ባለቤት እንደነበረች ተዘግቦአል[30]። በዚህ ወቅት ማዕከላዊ መንግሥት በመዳከም ላይ ሆኖ ዘመነ መሳፍንት እያቆጠቆጠ በነበረበት ጊዜ ነበር።

ለመጀመሪያ ጊዜ ቱርኮች በ1557 ዓ.ም. ምጽዋን ከጥቂት ጊዜ በኋላም የባህረ ነጋሽ ግዛት ዋና ከተማ ደባርዋን መያዝ ችለው ነበር። ሆኖም በቱርኮች አማካይነት ግብጾች ምጽዋንና አርኪኮን በመቆጣጠራቸው ቱርኮች ምጽዋን ግዛታችን ነው በማለት ይዞታቸውን አጸኑ። ቱርክ ምጽዋ የያዘችው ሦስት ኃያላን መንግስታት እንግሊዝ፤ ፈረንሳይና ጣልያን አፍሪቃ ለመቀራመት ትግል በሚያደርጉበት ጊዜ፤ፈረንሳይ ከምዕራብ አፍሪቃ እስከ ምስራቅ ቀይ ባህር ኩታ ገጠም የሆነ ቅኝ ግዛት ለመያዝ ስትጥር፤እንግሊዝ ደግሞ በበኩሏ ከሰሜን አፍሪቃ ከግብጽ ወይንም ከሱዳን እስከ ደቡብ አፍሪቃ ኩታ ገጠም ግዛት ለማድረግ በምትንቀሳቀስበት ጊዜ ነበር። እንግሊዝ ከፈረንሳይ ጋር በነበራት ፉክክር ኢጣልያን የራስዋን መሣሪያና ደጋፊ ለማድረግ አቅዳ ከአሰብ እስከ ምጽዋ ያለውን የባህር በር ጠረፍ ጣሊያን እንድትይዝ ሁለቱ አገሮች ተስማሙ። በዚህ ጊዜ ጣሊያን ኃያሏ ታላቋ ብሪታንያ ከጉኗ ከማሰለፍም በላይ ከብሪታንያ ድጋፍና

[29] Ibid

[30] ኢትዮጵያ ጠረፍዋና የባህር ኃይሏ፣ ዝኒ ከማሁ 25 ገጽ 45



እርዳታ ስላልተለያት ያለምንም መከላከያ ትገኝ ወደ ነበረች ምጽዋ በኮ/ሌ ሳሌታ የሚመራው 802 የጣልያን ጦር አዝምታ ፌብርዋሪ 1885 ዓ.ም ያለምንም ደም መፍሰስ ምጽዋን በቁጥጥርዋ ስር አደረገች። ሩባቲኖ ኩባንያ አሰብን በገንዘብ ከገዛው ከ10 ዓመታት በኋላ ነበር ጣልያኖች ምጽዋን በቁጥጥራቸው ስር ያደረጉት[31]። በምጽዋና በአካባቢዋ ይዞታቸውን ከአጠናከሩ በኋላ ጣልያኖች ግዛታቸው በአዋጅ "የአሰብ የኢጣልያ ቅኝ ግዛት" የሚል ስያሜ ቀርቶ "በቀይ ባህር የኢጣልያ የቅኝ ግዛቶች" የሚል አዲስ ሥያሜ ከሰጡአቸው በኋላ ሁለቱንም የአሰብና የምጽዋ ግዛቶቻቸው በማጠቃለል በ1890 ዓ.ም "ኤርትራ" የሚል ስም ሰጥተው ቅኝ ግዛት መሠረቱ። ምጽዋ ለ300 ዓመታት በቱርኮች እጅ በነበረችበትም ጊዜም ይሁን፤ ከቱርኮችም በኋላ ግብጾች ተረክበዋት በሚያስተዳድሩበት ጊዜያት ሁሉ የኢትዮጵያ ነገሥታት በምጽዋ ወደብ ላይ አለከልካይ በወደቡ ይጠቀሙ ነበር[32]።

በዘመነ መሳፍንት ጊዜ ማዕከለዊ መንግሥት ከመዳከሙ ቀደም ብሎ በአጼ ፋሲል ሞትና (1667) በአጼ በካፍ መንገሥ መሃከል ለ65 ዓመታት የኢትዮጵያ የባህር ጠረፍ ይዞታ እየተዳከመ ቢሄድም በአጼ በካፋ (1721-1730) ፤በአጼ ኢያሱ ll (1730-55) ፤በአጼ ኢዮአስ (1755-69) ዘመነ መንግሥታት ኢትዮጵያ በቀይ ባህር ጠረፍ የተጠናከረ ይዞታ እንደነበራት ታሪክ ይገልጻል[33]።

የኢትዮጵያና የባህር በር ጥያቄ ኤርትራ ምን ያህል የኢትዮጵያ አካል ነበርች ከሚለው ጋር የተያያዘ ነው። የኢትዮጵያና የኤርትራ የታሪክ ትስስር ወርዱ፤ስፋቱና ጥልቀቱ ብዙ ሰዎችን ያከራከረ ጉዳይ ሲሆን የተከራካሪዎቹ አቋም በአብዛኛው በፖለቲካ አቋማቸው ላይ የሚያጠንጥን ነው ለማለት ይቻላል።

አንዱ ጽንፈኛው ወገን ዛሬ በምናውቃት መልኳ ኤርትራ ምንም ሳይቀነስላት እንዲያውም ከዚህም በላይ ተጨምሮ የኢትዮጵያ አካል ነበረች ሲሉ ይከራከራሉ። ሌላው ጽንፈኛ ወገን

[31] ተወልደ ትኩእ ዶ/ር ፤የኢትዮጵያ አንድነትና ኢጣልያ፣ አዲስ አበባ (ሚያዝያ 1990 ዓ.ም) ገጽ 158

[32] ዝኒ ከማሁ

[33] ተወልደ ትኩእ ዶ/ር ፤ዝኒ ከማሁ 31 ገጽ159

ደግሞ ኤርትራ በዛሬው ቅርጽዋ ዝንተ ዓለም በነፃነት ከኖረችዋ ከኢትዮጵያ ጋር ከጉርብትና ውጭ ሌላ ምንም ዓይነት ግንኙነት ያልነበራት እራስዋን ችላ የቆመች አገር ነበረች በማለት ይከራከራሉ።

ሐቁ ግን ከእነዚህ አቋሞች ከሁለቱም ሳይሆን ኤርትራዊው ምሁር ፕሮፌሰር ተስፋጽዮን መድሃኔ የሁለቱም ጽንፈኞች አቋም በማጣጣል ኤርትራ ቢያንስ ከ4ኛው እስከ 8ኛው ምዕተ ዓመታት በራስዋ የቆመች የተለየች የፖለቲካ ተቋም እንዳልነበረች ሲገልጹ በአንጻሩ ደግሞ ዛሬ የምናውቃት ኤርትራ በሙሉ የኢትዮጵያ አካል ነበረች የሚለውም እንደማያስኬድ ያስረዳሉ። በመቀጠልም ፕሮፌሰሩ ከ4ኛው እስከ 8ኛው ምዕተ ዓመታት ደጋው ኤርትራ የአክሱም ነገሥታትና ሥልጣን መዐከል እንደነበረች የዛሬይቱ ኢትዮጵያም ከአክሱም ተያይዛ የወረደች ለመሆንዋ ይቀበላሉ[34]።

ፕሮፌሰር ሪቻርድ ፓንክረስትም በታሪክ የምትታወቀው ኢትዮጵያ ከቀይ ባህርና ከኤደን ገልፍ ጋር ትዋሰን እንደነበር ሲያረጋግጡ ይህም ኢትዮጵያ የባህር በር ባለቤት እንዳነበረች አንድ ሌላ ማስረጃ ነው[35]። አንድ የአፋር ተወላጅ የታሪክ ጸሐፊ ስለ አፋር ሕዝብ ታሪክ ሲጽፉ በ16ኛው ምዕተ ዓመት አካባቢ ኢትዮጵያ በቀይ ባህር ዙሪያ የበላይነቱን ይዛ እንደነበርና ሰፊም ይዞታ እንደነበራት የአንድ በአረብኛ የተጻፈ ካርታ ያረጋግጣል ብለዋል። ጸሐፊው ካርታውን ሲጠቅሱ

"......ካርታ ቁ.3/4(ለ) በአረብኛ የተጻፈ ካርታ ነው። በዚህ ካርታ ላይ Ethiopia (ኢትዮጵያ) ተብሎ የተሰየመው ግዛት በቀይ ባህር ዙርያ ያሉትን የቤጃ ሕዝቦች ምድር፣ የሃበብና የበለው ሕዝቦችን ምድር እንዲሁም በአፋር ግዛት ከዳህላክ ደሴቶች እስከ ዘይላ ድረስ ያለውና ከዚያም ያለው የሱማሌን ግዛት ያጠቃልላል ሲሉ ጽፈዋል[36]። ፕሮፌሰር መስፍን ወልደ ማርያም ኮንቲሮሲኒና

[34] Tesfatsion Medhane, Professor, Eritrea Dynamics of a National Question, B.R. Gruner Amsterdam (1986) p.6-7.

[35] Richard Pankhurst, Professor "Images of Ethiopa over the Centuries, Capital, Sunday October 31, 2010 p.38.

[36] ሸህ ጁማለዲን ኢብራሂም ኸሊል ኡሻሚና በልጃቸው ሃሺም ጃማለዲን ኢብራሂም ኡሻሚ (ዶ/ር) (የተጻፈ) የአፍር/ ደናኪል ታሪከና መረጃ አርኪ ምንጫ፤ አዲስ አባባ 2000 ዓ.ም ገጽ 89.



ታዲያ የተሠኙ ጣልያናዊያንን ካመረር የተባለ ፈረንሳዊ ፀሐፊ እና ሌሎችም የውጭ አገር ፃህፍትንና አገር ጉብኚዎችን በዋቢነት ለመጥቀስ የጥንታዊት ኢትዮጵያ የምሥራቅ ወሰን ቀይ ባህር እንደነበረ ማረጋገጣቸውን አሰምረውበትል። ፕሮፌስር መስፍን ወደ አገር ምንጮች በመመለስ በምሳሌነት የአፄ አምደ ፅዮን (1312-1392)፤ የአፄ ገላውዴዋስ (1532-1551)፤ የአፄ ሠርፀ ድንግል (1555-1587) እና ሌሎችም ዜና መዋዕሎችን በማመላከት የኢትዮጵያ፤ የምሥራቁ ወሰን ቀይ ባህር እንደነበር ይልፀዋል [37]

የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ከአክሱም ጀምሮ ሳያቋረጥ አንዱ ሥርወ - መንግሥት ከሌላው እየተወራረሰ የወረደች ማህበረሰብና አገር እንደሆነችና የባህር በሮችም እንደነበሩአት ቀደም ሲል ሲክድ የነበረው ሕወሓት አንኳን ዛሬ በዚህ ጉዳይ ከመላው ሕዝብ ጋር ሰልፉን አሣምሮ ይገኛል። አሁንም ሕወሓት በድፍረት ወጥቶ ጥንት እንደነበረው የኢትዮጵያ የባህር በር መከበር አለበት ለማለት ግን ወኔው የገደበው ይመስላል።

ኢትዮጵያ የሰሜን ግዛቶችዋና የባህር ጠረፏ በ1885 ዓ.ም በቱርኮች በግብጾች፤ በጣልያኖችና በፈረንሳዮች ሤራ ከተያዙባት ጊዜ ጀምሮ የባህር በሮችዋን ለማስመለስ በየጊዜው የተፈራረቁ ነገሥታት የዓለምን ሕብረተሰብ ከመማጠንና ሁለገብ ትግል ከማድረግ የቦዘኑበት ጊዜ የለም።

ከኢሕዴግ መንግሥት በስተቀር ከአጼ ቴዎድሮስ ጀምሮ አጼ ዮሐንስ፣ አጼ ምኒልክ፣ ንግሥተ- ነገሥታት ዘውዲቱና፣ አጼ ኃይለ ሥላሴ ሁሉም የባህር በር ማስመለስ ከውጭ ግንኙነቶቻቸው ፖሊስ ግዙፉና ቀዳሚውን ቦታ አስይዘውት ነበር ማለት ይቻላል። የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግም በሻቢያና በኢህአዴግ በጦርነቱ ሊሸነፍና ኤርትራም ልትገነጠል እንደምትችል ከተረዳ በኋላ ኢትዮጵያ ወደብ አልባ እንዳትሆን የበኩሉን ጥረት አድርጓል።

[37] መስፍን ወልደ ማርያም ፕሮፌሰር ፤የክህደት ቀልቅሎት አዲስ አበባ (2003) ዓ.ም 28-32 ያለውን ማየት ይቻላል

## 2.2. የኢትዮጵያ የባህር በሮችን ለማስመለስ የተደረጉ ትግሎች

### 2.2.1. የአጼ ቴዎድሮስ ትግል

አጼ ቴዎድሮስ እ.አ.አ. በ1855 ዓ.ም. በጥቅምት 20, ጉዳም ሳሉ ለንግሥት ቪክቶርያ በጻፉት ደብዳቤ ጥንት የኢትዮጵያ ነገሥታት ባህረ ነጋሽ እያሉ ተጠሪዎቻቸውን ይሾሙበት የነበረውን የቀይ ባህር አካባቢና ወደቦቹን የያዙት ቱርኮችን ለማስለቀቅ ጽኑ ፍላጉት እንዳላቸው ለንግሥቲቱ አስታውቃው ነበር። ይህንኑ በመግለጽ "....ቱርኮች የአባቶቼን መሬት ልቀቁ ብላቸው እምቢ ብለውኝ በእግዚአብሔር ኃይል ይኸው ልታገል ነው። ቱርኮች በባህር ላይ ሆነው መልእክተኞቹን አላሳልፍም ብለው ችግር ፈጥረውብኛል"[38]የሚል ነበር ደብደቤው።

በተጨማሪም አጼ ቴዎድሮስ የእንግሊዝ ቆንስል ኘላውደንና እረዳቱ ካሜሩንን ተቀብለው ባነጋገሩበት ጊዜ ምኞታቸው ከእንግሊዝ ንግሥት እርዳት ጋር የቱርክና የግብጽ አገዛዝ ከኢትዮጵያ ጠረፎች ለመንቀልና የጥንት ኢትዮጵያን የባህር በር ለማስመለስ ማሰባቸውን ለእንግሊዞቹ ገልጻውላቸው ነበር[39]።

ሆኖም አጼ ቴዎድሮስ ቱርኮችንና ወኪሎቻቸው የነበሩት ግብጾችን አባርረው የኢትዮጵያን የባህር በር መብት ለማስመለስና ኢትዮጵያን የባህር በር ባለቤት ለማድረግ የወጠኑት ዓላማ ግቡ ሳይመታ ሞት ቀደማቸው።

[38] ተክለጻዲቅ መኩርያ፤ አጼ ቴዎድሮስና የኢትዮጵያ አንድነት፤ኩራዝ ማተሚያ ድርጅት አ.አ.አ (1981 ዓ.ም) ገጽ 301.
[39] ዝኒ ከማሁ.



### 2.2.2. የአጼ ዮሐንስ ትግል

አጼ ዮሐንስ አራተኛው ሥልጣን ላይ ሲወጡ ኢትዮጵያ በቱርኮች፣ በግብጾች፣ በጣልያኖችና በእንግሊዞች ሤራ ከአክሱም ነገሥታት ጊዜ ጀምሮ የነበሩአት የባህር በሮችዋ ተነጥቃ ሙሉ በሙሉ ወደብ አልባ የነበረችበት ጊዜ ነበር።

ይህ ወደብ አልባ መሆን አጅግ ካሳሰባቸውና የችግሩ ጥልቀት ከገባቸው የኢትዮጵያ መሪዎች አጼ ዮሐንስ ግንባር ቀደሙ ሳይሆኑ አይቀሩም። የባህር በር ለአንዲት አገር ሉዓላዊነት መከበርና ለኢኮኖሚ ዕድገት ምን ያህል ወሳኝነት እንዳለውና የባህር በር አለመኖር የአገር ሉዓላዊነትን ለከፍተኛ አደጋ ሊዳርግና ኤኮኖሚውንም ምን ያህል ሊያቀጭጭ እንደሚችል አጼ ዮሐንስ በቅጡ የተረዱ ለመሆኑ ለእንግሊዝ ንግሥት ቪክቶርያ በተለያዩ ጊዜያት የጻፉአዋቸው ደብዳቤዎችና የአደረጉአቸው የዲኘሎማሲያዊ እንቅስቃሴዎች ዋቢ ሊሆኑ ይችላሉ።

ከነዚህም ከመጀመሪያዎቹ እንቅስቃሴአቸው አንዱ ከአክሱም ከተማ ሰኔ 10 ቀን 1872 ዓ.ም ለእንግሊዝ ንግሥት ቪክቶርያ አጼ ዮሐንስ ምጽዋን እንዲይዙ እንዲረዱአቸው የጻፉት ደብዳቤ ነበር።

> *"..........የምጽዋን በር እኔን ደስ ይበለው ብለው እንደከፈቱልኝ ኢያሱስ ክርስቶስ የማያልፈውን የመንግሥተ ሰማይን በር ከፍቶ ደስ ያሰኝልኝ። በመንግሥትዎ ውስጥ ያሉት መማከርትዎ እኔን ደስ ሊያሰኙ ይህን አሰበው ስለመከሩ እግዚአብሔር በመንግሥተ ሰማይ ደስ ያሰኛቸው። እኔንም ከእርስዎ ጋር በምክርዎ አንድ ሆኜ ከፈቃድዎ ለማዋል ያብቃኝ። ጥንቱንም በእግዚአብሔር ፈቃድ ለመንግስት የበቃሁት እርስዎ በሰጡኝ መድፍና ነፍጥና ባሩድ ነው። አሁን ደግሞ ይልቁንም ይበልጥ ፈጽመው ደስ አሰኙኝ። ከዚህ በፊትም እናት ለልጅዋ እንድትጨነቅ ለኔ መንግሥት ሲጨነቁ ይኖራሉ ። ነገር ግን በቅርብ ቀን ቀርቶ ነው እንጂ እንኳን እርስዎ የአውሮፖ ነገሥታት መላው ያውቃሉ።*

*የምጽዋ በር የአባቶቼ የነገሥታት ኢትዮጵያውያን ነው አሁንም እንዝብል በር ቤተ መንግሥት አይቀርምና በእርስዎ ወኪልነት እርዳታ የምጽዋን በር እንድይዘ ያድርጉልኝ ብዬ እለምናለሁ የቀረው ነገር ሁሉ ሲወሰን የዚህ ነገር አልተወሰነልኝም።(ሰርዝ የተጨመረ) ደግሞ ሪር አድሚራስ ሰር ውሌም ሂዌት ሹምዎ የምጽዋን ቀረጥ እኩሌታውን የያዙ አለኝ እሺ አትምልኝና ልያዝ ብለው ማህተምስ ንግሥትን ሳልጠይቅ ላላትምም ብሎኝ መጥቷል*[40]።

ቀደም ሲልም አጼ ዮሐንስ፤መቀሌ ላይ ሆነው ጥቅምት 27 ቀን 1870 ዓ.ም ለፈረንሳይ ፕሬዝዳንት በጽፉት ደብዳቤ ጉርዳን ፓሻ የተባለ ሰው ተልኮባቸው ከቱርኮች ጋር እንዲያስታርቃቸው ቢጠየቁ ከቱርኮች ጋር ሊታረቁ የሚችሉት ቱርኮች የያዙትን የኢትዮጵያን መሬት በሙሉ ለቅቀው ሲወጡና ድንበር ሲካለሉ ብቻ መሆኑን አስታወቁ።

አጼ ዮሐንስ ዋና ዓላማቸው ምጽዋንና አካባቢውን ይዘውባቸው የነበሩትን ቱርኮችንና ወኪሎቻቸው ግብጾችን ከአካባቢው ማባረር እንደነበር ሆኖ የሂዌት (Hiwot Treaty) ስምምነት የተባለው ውል "..... ከታተመበት ቀን ጀምሮ በምጥዋ ወደ ሐበሻ የሚገባ ከሐበሻ የሚወጣ ዕቃ ሁሉ የጦር መሣሪያ ነፍጥና መድፍ ጥይትም ቢሆን በእንግሊዝ ውክልና በነፃ እንዲወጣና እንዲገባ"[41] በመፍቀዱና ቦጐስ የተባለው ግዛታቸው የዛሬው ሐማሴን ስለተመለሰላቸው ለጊዜውም ቢሆን አጼ ዮሐንስ ውሉን ተቀብለው ፈረሙ። በመጀመሪያ እንግሊዞች ወደቡ ለኢትዮጵያ እንዲመለስ በመሠረተ ሃሳቡ ቢስማሙም የግብጽን መንግሥት ሳያስቀየም ሲሉ ኢትዮጵያ ወደቡን በነጻ እንድትጠቀም አሳሰቡ። የሂዌት ውል በሚደነግገው መሠረትም የግብጽ ጦር ካርቱም ውስጥ ተከብቦ ለእልቂት ሊዳረግ ሲል እንግሊዞች አጼ ዮሐንስ እንዲያስለቅቁአቸውና በለውጡም ምጽዋን ከቱርኮችና ከግብጾች አስለቅቀው እንደሚሰጡአቸው ቃል ገብተውላቸው ነበር። ሆኖም

[40] ታደሰ ገድሌ ከአሰደናቂዎቹ የነገሥታትና የመሳፍንት ደብዳቤዎች ፤ (ከዲፕሎማሲና ከወዳጅነት አንጻር) አዲስ አበባ (2002 ዓ.ም) ገጽ 61.

[41] ተክለ ጻድቅ መኩሪያ ዝኒ ከማሁ 38 ገጽ 270.



ራስ አሉላ ደርቡሾቹን ወግተው ግብጾችን ካስለቀቁ በኋላ እንግሊዝች እራሳቸው "በታሪክ ጥቂት ተወዳዳሪ ብቻ የሚገኝለት" ያሉትን ክህደት በመፈጸም ምጽዋን ለጣልያን ሰጡባቸው። ፈረንሳዮችም በበኩላቸው እምነታቸው ሙሉ በሙሉ በጅቡቲ ላይ ስለጣሉና ጅቡቲንም ለማሳደግ ስለፈለጉ ኢትዮጵያ የባህር በር እንዳይኖራት ከእንግሊዞች ጋር አሴርውባት ነበር[42]።

በዚህ ጊዜ ቁርክን ተክታ የነበረችው ግብጽ በደረሰባት የኢኮኖሚ ውድቀት ምክንያት ተዳክማ በእንግሊዞች ጫና ስር ስለነበረች እንግሊዞች ከዲብ ተውፊቅን በመጫን ምጽዋ ወይንም ዙላ ለኢትዮጵያ መመለስ በቻሉ ነበር። ሆኖም የሂዌት ውል ዓላማው ምጽዋና አካባቢው ለጣልያኖች አሳልፎ ለመስጠት የተጠነሰሰና ኢትዮጵያን ከአካባቢው ለማግለል የታቀደ ሴራ ስለነበር እንግሊዞች ውሉን ለመጣስ አላመነቱም[43]።

ጣሊያኖች በእንግሊዞች ፈቃድ ምጽዋን ሲይዙ እንግሊዞች እንዳላዩ በመሆን ፊታቸውን አዞሩ። ከላይ እንደተገለጸው እንደ ዶክተር ተወልደ አባባል ጣልያን "ተዝናንታ ነበር የገባችው"[44]። ጣልያን እንግሊዝን ከጐኗ አሰልፋ አስፈላጊውን ድጋፍ በእንግሊዝ እየተሰጣት ያለ ምንም መከላከያ በግብጽ እጅ ትገኝ የነበረችው ምጽዋ- በኰሎኔል ሳሌታ የሚመራው 802 ወታደሮችን የያዘ የጣልያን ጦር አዝምታ እ.አ.አ. ፌብርዋሪ 1885 ዓ.ም ያለ ምንም ደም መፋሰስ ምጽዋን በቁጥጥርዋ ሥር አደረገች[45]።

ጣልያኖች በዚህ ዓይነት አለአንዳች ተቃውሞ ሰተት ብለው ገብተው ምጽዋን መያዝ የቻሉት፤ራስ አሉላ ጦራቸውን ይዘው የሂዌት ውል በሚደነግገው መሠረት የውል ግዴታቸውን ለመፈጸም ከላይ እንደተገለጸው በደርቡሾች ተከበው የነበሩ

[42] ተፈራ ኃይለ ሥላሴ (አምባሳደር) ኢትዮጵያና ታላቋ ብሪታንያ የዲፕሎማቲክ ታሪክ 1970-1996፤ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ አዲስ አበባ፤ (1999 ዓ.ም) ገጽ 106.

[43] Shumet Sishagne, Professor. Unionists and Separatists; The Vagaries of Ethiopia Eritrean Relations 1940-1991. Hollywood, CA. 90078, 1982.

[44] ተወልደ ትኩእ ዶ/ር ዝኒ ከማሁ 31 ገጽ 42

[45] ዝኒ ከማሁ ገጽ159

ግብጾችን ለማስለቀቅ ሱዳን ሄደው በቦታው ባለመገኘታቸው ነበር[46]::

አጼ ዮሐንስ ከአክሱም ከተማ ለንግሥት ቪክቶርያ በሰኔ 10 ቀን 1870ዓ.ም ደብዳቤ ከጻፉ ከሁለት ወራት በኋላ እንግሊዞች ምጽዋን ለጣልያን በመስጠታቸው ከደብረ ታቦር ሆነው ለንግሥቲቱ እንደገና በጻፉት ደብዳቤ ባስተላለፉት መልክት "ቱርኮች ሲለቁ የምጽዋን በር እይዛለሁ ስል ጣልያን መጥቶ ምጽዋንና ሌላውን አገሬን ያዘብኝ..... አሁንም ምጽዋ ይሰጠኝ:: ቀድሞም የአባቶቼ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥታት እንደሆነ ያውቃሉ:: የተለቀቀበት ጊዜም ቅርብ እንደሆነ አይጠፋዎትም"[47] ብለዋል:: ለደብዳቤያቸው ምንም መልስ ባለማግኘታቸው በእንግሊዞች ክህደት የተበሳጩት አጼ ዮሐንስ አሁንም ጣልያን መሬታቸውን እንዲለቅ በማሳሰብ ለንግሥቲቱ እንደገና ቁጣ አዘል ደብዳቤ ጻፉ:: "ለጥንት ለልጅ ልጅ ሊሆን የታረቅነው አሁን ዓመት ሳይሆነው ሥስቱም [የሂዌት] ውል ፈርሶ እንደሆን እኔ ግድ የለኝም:: መልካም ነገር ከማድረግ በቀር! አሁንም የጣልያን ጦር መምጣቱ በእናንተ ፈቃድ ነው"[48] ሲሉ እንግሊዞችን ወቅሰዋል::

በዚህን ጊዜ ጣልያኖቹ ምጽዋ ይገባናል የሚለው ጥያቄአችውን እንዲተዉ እንግሊዞች ኢትዮጵያና ጣልያንን ለማግባባት ወይንም ኢትዮጵያን ለማታለል ራስ አሉላ ምጽዋንና አካባቢውን ሰሐጢን ጨምሮ ለጣልያን እንዲለቅቁ ባሳሰቡ ጊዜ ራስ አሉላም "የኢትዮጵያ የተፈጥሮ ድምበር ቀይ ባህር ነው:: ይህንን ለቅቄ ወዴት እሄዳለሁኝ" በማለት ጽኑ አቋም ወሰዱ[49]::

በእንግሊዞች አታላይነት ምጽዋና አካባቢዋ በጣልያኖች እጅ መውደቅና የአገራቸውን ወደብ አልባ መሆን አጼ ዮሐንስን እጅግ ያሳዘነ ጉዳይ ነበር:: አንዳንዴ ንግሥቲቱን በመለመን ሌላ ጊዜ አካባቢውን በቱርኮች ስም ይቆጣጠሩ የነበሩ ግብጾችንም በመውጋትና ድል በማድረግ ምጽዋ እንዲመለስላቸው የእንግሊዝ

[46] S.Rubenson, King of Kings Tewodros of Ethiopia, London (1966), p. 25.

[47] ታደሰ ገድሌ ደጋዬ ዝኒ ከማሁ 40 ገጽ 58

[48] ዝኒ ከማሁ

[49] አሥራት አብርሃ ዝኒ ከማሁ 16 ገጽ16



እርዳታ ለመጠየቅ ንጉሠ ነገሥቱ ለእንግሊዝ ንግሥት አምስት ጊዜያት ያህል ደብዳቤ ጽፈዋል:: እንግሊዞች የኢትዮጵያ ነፃ አገር ሆና መቆም በፍጹም የማይፈልጉት ነገር ስለነበር በአጼ ዮሐንስ ላይ በፈጸሙአቸው ደባዎች ኢትዮጵያ ወደብ አልባ ሆነች::

አጼ ዮሐንስ በአካባቢው ልዕለ ኃይል የነበረችውን እንግሊዝን በመፍራት ተቆጥበው ነው እንጂ ራስ አሉላ ቱርኮችንና ግብጾችን ከኢትዮጵያ ምድር ማባረር ባላቃታቸውም ነበር:: ምክንያቱም ራስ አሉላ ግብጾችን በተደጋጋሚ በጦር ሜዳ ድል በማድረግ ከአካባቢው ሊያስወጡአችው ይችሉ እንደነበረ አስመስክርዋል::

አጼ ዮሐንስና የሐማሴኑ ገዢ ራስ አሉላ ለአገራቸው ነፃነትና ለባህር በር ባላቸው ቁርጠኝነትና ቀነአኒነት አጼ ዮሐንስ መተማ ላይ ባይሰዉና ጊዜ ቢያገኙ ኖሮ ምጽዋንና ቢያንስ ደጋውን ኤርትራና አሰብንም ከጣልያኖች መንጋጋ ፈልቅቀው ማውጣት ባልገደዳቸውም ነበር::

አጼ ዮሐንስ "ያለ ባህር በር ቤተ መንግሥት አይቆናም" ሲሉ ያለ ባህር በር የአንድ አገር ሉዓላዊነት አደጋ ላይ ሊወድቅ እንደሚችል መግለጻቸው መሆኑ መረዳት ይቻላል:: የዛሬዎቹ የኢትዮጵያ ገዢዎች የባህር በር አሰብ ከዕቃ ማስተላለፊያነት ውጪ የሚፈይደው ነገር የለም ሲሉ ከመቶ አምሳ አመታት በፊት ኢትዮጵያን ይገዙ የነበሩት ንጉሠ ነገሥት ያህል ግንዛቤ የላቸውም ማለት ነው፤ ወይስ "እውቆ የተኛ ቢቀሰቅሱት አይሰማም" ሆኖ ሃቁን ለማሽመድመድ ነው::

## 2.2.3. የአጼ ምኒልክ ትግል

አጼ ምኒልክ የኢትዮጵያን ግዛት ለማስፋፋት ከተያያዙት ትግል በተጨማሪ በሰሜኑ እንግሊዞች በምሥራቅ ጣሊያኖች፤ ፈረንሳዮችና እንግሊዞች፤በምዕራብ እንግሊዞች፤ በደቡብ አሁንም እንግሊዞች ከብበዋቸው ኢትዮጵያን በቅኝ ግዛታቸው ውስጥ ለመጠቅለል በተናጠልና በቡድን አስጨንቀው የያዛቸው ወቅት ነበር:: ስለሆነም ኢትዮጵያን የባህር በር ባለቤት የማድረጉ ጉዳይ ከአገር ነጻነትና ሉዐላዊነት ቀጥሎ በሁለተኛ ደረጃ የሚታገሉለት ግብ ነበር ማለት ይቻላል:: ያም ቢሆን አጼ ምኒልክ በምሥራቅ

በኩል ወደ ባህር የሚያሻግር ወደብ በመሻት ለጣልያን ንጉሥ ኡምቤርቶ በ1876 ዓ.ም. በጻፉት ደብዳቤ "የዘይላን በር ነገር በሚቻልዎ ነገር ሁሉ ተጣጥረው በእኔ እጅ ቢሆን እንኳን በሐረርጌ፤ በአሩሲ በጉንባታ በጅማና በከፋ ያለው ንግድ ሁሉ በዘይላ አድርገው ነበር፤ ስለዚህ ጠንቅቀው ቢያስለቅቁልኝ እወዳለሁ። ይህም ማለቴ ለእርስዎ እንዳይቸግርዎ ባውቀው የኢትዮጵያ ልጆች በንጉሥ ኡምቤርቶ ብርታት የዘይላ በር እጃችን ተመልሶ ገባ እያሉ እንዲሉ ለምዎ በነገሥታት ታሪካችን ይተከላል"[50]።

አጼ ምኒልክ ለጻፉት ደብዳቤ ምላሽ ከሰማግኘታቸውም ሌላ ንጉሥ ዑምቤርቶም ኢትዮጵያ የባህር በር ባለቤት እንድትሆን ምንም ያደረጉት ዕርዳታ አልነበረም። አጼ ምኒልክ ግዛታቸውን ለማስፋፋት ኢትዮጵያን ቅኝ ግዛታቸው ውስጥ ለማስገባት ይቋምጡ ከነበሩበት ጠላቶቻቸው ለመከላከል መግቢያ የሚያስገቡት ከምጽዋ ይልቅ ለሸዋ ቅርብ በሆነው በአሰብ በኩል ነበር።

አጼ ዮሐንስ በተሰዉበት በዚያው ዓመት አጼ ምኒልክ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ሆነው መላው አገሪቱን ማስተዳደር ሲጀምሩ የግዛታቸው መጠንና የኢትዮጵያ ወሰን የትና የት እንደሚያካልል ለዓለም መንግሥታት ለማስታወቅ ለንግሥት ቪክቶሪያ በጻፉት ደብደቤ ገልጸው ነበር። በምሥራቁ በኩል የኢትዮጵያን ወሰን ሲዘረዝሩ "ከሃምበሳ እንስቶ የአሰልን ባህር ጨምሮ የጥንት ዜጋችን የምሃመድ ሃንፋሬን ግዛት ሙሉ ይዞ በባህር ዳር እየሄደ አረፋሲ ይደርሳል"[51] ሲሉ አስታውቀው ነበር።

አጼ ምኒልክ በዚሁ ለንግሥት ቪክቶርያ በጻፉት ደብዳቤ "....የጥንቱ ዜጋችን የመሃመድ ሃንፋሬን ግዛት" ሲሉ የአፋርን ምድር ያስተዳድሩ የነበሩት የሱልጣን ሃንፋሬን የዛሬው የቢትወደድ አሊ ሚራህ አባትን ሲጠቅሱ ነው። ሱልጣን አሊሚራህ ደግሞ እንደዛሬው የኢትዮጵያና የኤርትራ አፋር የሚባል ክፍፍል ስላልነበር ዋና ቀያቸው አውሳ ሆኖ የሁሉም

[50] ታደሰ ገድሌ ጸጋዬ ገጽ ዝኒ ከማሁ 40 ገጽ 71.
[51] ተክለ ጻዲቀ መኩሪያ ዝኒ ከማሁ 38 ገጽ 301



አፋሮች መሪ ነበሩ። አጼ ምኒልክ ይህንን የጠቀሱት ግዛት የአሰብን ወደብ እንደሚጨምር ግልጽ ነው።

ቀድመዋቸው ከነበሩት ነገሥታት ሁሉ አጼ ምኒልክ ኢትዮጵያን የባህር በር ባለቤት ማድረግ ጉዳይ አሳልተው የያዙት ቢመስልም ዘወትር ያሳስባቸው እንደነበር ጸሐፍት ይገልጻሉ። አጼ ምኒልክ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥትነት ሥልጣን በያዙበት ጊዜ አውሮፖውያን አፍሪቃን እየተቀራመቱ በነበረበት ጊዜ ሆኖ ኢትዮጵያንም የቅኝ ግዛት ቀንበር ለማሸከም በብዙ የሚጥሩበት ወቅት ስለነበር አጼ ምኒልክ ለባህር በር ለመታገል ፋታ አላገኙም ነበር።

አጼ ምኒልክ ዋነኛው ይጠቀሙበት የነበረው የባህር በር ፈረንሳዮች ቀደም ሲል ይዘውት የነበረው አቦክ የዛሬይቱ ጅቡቲ ሲሆን አጼ ምኒልክ ኢትዮጵያን የባህር በር ባለቤት ለማድርግ ዲፕሎማሲያዊ ትግላቸውን በመቀጠል በጃንዋሪ 29, 1897 ዓ.ም. ራስ መኩንን ከፈረንሳይ ሱማሌ ተወካይ ኤም ላጋርድ ጋር የተፈራረሙት ውል በተደራደሩበት ወቅት አጼ ምኒልክ ጅቡቲ የኢትዮጵያ የተፈጥሮ ወደብ መሆኑ የሚያረጋግጥ አንቀጽ እንዲያካትት ለራስ መኩንን ትዕዛዝ ሰጥተው ነበር[52]። ይህ አጼ ምኒልክ በውሉ እንዲካተት ያዘዙት አንቀጽ በሙሉ ተካትቶ እንደነበረ ወይንም እንዳልነበረ መረጃ የለም።

አጼ ምኒልክ የአሰብም ሆነ የጅቡቲ ያባህር በሮች ለኢትዮጵያ የሚያመጡት የኢኮኖሚ ጥቅምና የደህንነት ዋስትና እየተረዱ እነዚህን የባህር በሮች ለማግኘት ለምን ጥረት አላደረጉም የሚለው ጥያቄ ብዙዎችን ያከራከረ ጉዳይ ነው።

[52] R.K.Pankhurst "Ethiopia and The Red Sea and The Gulf of Aden Ports in the Nineteenth Century Ethiopia.The Observer, vol.8 no.1 (1964) p. 73.

ይልቁንም አጼ ምኒልክ እ.አ.አ በ1896 ዓ.ም በአድዋ ጦርነት ጣልያንን ድል ከአደርጉ በኂላ ወደ ሰሜን አለመግፋታቸውና ቢያንስ ከደጋው ኤርትራ ጣልያንን አባርረው ጥንት የኢትዮጵያ አካል እንደነበረ የማያጠራጥረው አካባቢ እንኳን አለመያዛቸው በአንዳንዶቹ ዘንድ እንደ ብልህ ውሳኔ ሲቆጠር በሌሎች ደግሞ እንደ ክህደትም ተቆጥሮባቸዋል[53]*።

ከላይ እነደተገለጸው አውሮፖውያን አፍሪቃን በቅኝ፣ ግዛትነት የሚቀራመቱበት ወቅት ነበርና ብቸኛዋ ነፃ አፍሪቃዊ አገር ኢትዮጵያንም ለመዋጥ ምክንያት የሚፈልጉበት ሁኔታ ላይ ነበሩ።አንዳንድ የታሪክ ፀሐፊዎች ግምት አፄ ምኒልክ ጣልያንን እ.አ.አ. በ1896 ዓ.ም አድዋ ላይ ድል ቢያደርጉትም ወዳ ኤርትራ የማስወጣት አቀም ግን አልነበራቸውም፤ በሌሎቹ ዓይነ ደግሞ ንጉሡ ወዳ ሰሜን ሊዘልቁ እንደማይችሉ ከመገንዘባቸውም በላይ አድርገውት ቢሆን ኖሮ ተጠናክሮ ይጠብቃቸው የነበረውን የጣሊያንን ጦር ሊቋቋሙት አይችሉም ነበር። [54] ከምጽዋም ሆነ ከአፋር ሰላጤ ጣልያኖችን ለማስወጣት ቢሞክሩ ኖሮ አሥመራ ውስጥ ተጠናክሮ ለተቀመጠው የጣልያን ጦር ሰለባ ሆነው ሌላውንም የኢትዮጵያ ክፍሎች አደጋ ላይ በጣሉ ነበር። ቡተጨማሪም እንግሊዝ፣ ጣልያንና ፈረንሳይ ምኒልክን የ1908

[53] See Tecola W.Hagos Professor http://www.tecolahagos.com/part4.html

*ፕሮፌሰር መስፍን ወልደ ማርያም ለዚህ ወቀሳ መልስ ሲሰጡ የሚከተለውን ጽፋዋል። "ዶ/ር ተውልደ ትኩእ አፄ ሚኒልክን ከጣልያኖች ጋር አባሪና ከሃዲ አድርገው መወቀሳቸው ብዙ ሁናቴዎችን ካለመገንዘብ የመነጨ ይመስለኛል። ከብዙ የኢትዮጵያ ስሜት ያለችው የኤርትራ ተወላጆች ጭምር የሚሰማ ወቀሳ ነው።.........አጼ ምኒልክ ከኢጣልያ ጦር ጋር የተዋጉበት ዘመንና የኢትዮጵያ ሁኔታ አብዛኛው የኢትዮጵያ ጦር ከመሃል አገር ከሺህ ኪሎ ሜትር በላይ ነበር የሚመጣው ። የራሱን ስንቅ እየያዘና በራሱ መሣርያ የ[illegible]ት መሆኑን፤ ትግራይም ሆነ ኤርትራ ይህንን ሠራዊት ለመመገብ [illegible]ለመቻላቸውና የኤርትራም ሰዎች ምንም ነቅናቄ አለማድረጋቸው መታሰብ አለበት። እንዲህ ያለ አጋጣሚ በሌሎች አገሮችም ላይ በሃያኛው ምዕተ ዓመትም የደረሰ ነው"። ሲሉ ገልጸዋል። ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም ዝኒ ከማሁ 37 ገጽ 48 የግርጌ ማስታወሻ 13.

[54] Haggai Erlich, Ethiopia and Eritea During the Scramble for Africa. London (1982), p 193.



ዓ.ም. ውል ጭነውባቸው ስለነበር በዚህ አስጨናቂ ሁኔታ እያሉ ጣለያኖችን ከምጽዋም ይሁን ከአሰብ አባርረው ኢትዮጵያን የባህር በር ባለቤት ሊያደርጉ አልቻሉም[55]።

## 2.2.4. ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ልዑል አልጋ ወራሽ ራስ ተፈሪ በኂላም አፄ ኃይል ሥላሴ ያደረጉት ትግል

ኢትዮጵያን በተጨባጭ የባህር በር ባለቤት ለማድረግ በንግሥት ዘውዲቱና በልዑል ራስ ተፈሪ በኂላም በግርማዊ ቀደማዊ አጼ ኃይለ ሥላሴ ከፍተኛ ጥረት ተደርጎ እንደነበር በታሪክ ተዘግቦአል።

እ.ኤ.አ. በ1924 ዓ.ም ልዑል ራስ ተፈሪ አውሮፖን በጐበኙበት ወቅት ኢትዮጵያ በጅቡቲ በኩል የባህር በር እንዲኖራት ፈረንሳዮችን ጠይቀው አልተሳካለቸውም። እንዲሁም ሮማ ዘልቀው ይህንኑ የባህር በር ጥያቄ ቀይቶ ደመኛ ጠላታቸው ለሆነው ለሙሶሎኒ አቅርበው ኢትዮጵያ በአሰብ ለዘጠና ዘጠኝ ዓመታት በነፃ እንድትጠቀም ጣልያኖች ሲፈቅዱ በለውጡ ደግሞ ኢትዮጵያ ከጣልያኖች ውጭ ከማንም ጋር እንዳትገበያይ ገደብ ያስቀምጥ ስለነበር በኢትዮጵያ በኩል ተቀባይነት አላገኘም። ራስ ተፈሪ እንግሊዞችንም ከመጠየቅ ባይቦዝኑም እንግሊዞች ግን ለጥያቄአቸው መልስ ሳይሰጡ ቀሩ[56]።

አሁንም ባለመታከት የንግሥት ዘወዲቱ መንግሥት በጣልያኖች እጅ የነበረውን አሰብን የኢትዮጵያ ወደ ባህር መግቢያና መውጫ በር ለማድረግ በማሰብ ለጣልያኖች የንግሥቲቱ መንግሥት ጥያቄ አቅርቦ በሁለቱ መንግሥታት መሃከል ድርድር ተካሂዶ ከድርድሩ በኂላ ኢትዮጵያን ወደ ቀይ ባህር የሚያዘልቅና አሰብንም ለመጠቀም የሚያስችል ከቀረጥ ነጻ የሆነ መተላለፊያ (corridor) እንዲኖራት እ.አ.አ. በአገስት 1928

[55] Teggai Mebrahtu, http://ethiopia first.com/news2002 mar.rule_of_law_and_justice_Lasting_place.html

[56] ኢትዮጵያ ጠረፍዋን የባህር ኃይሏ ፤ ዝኒ ከማሁ 25 ገጽ 65.

ዓ.ም. ጣልያንና ኢትዮጵያ ውል ተፈራረሙ። ሆኖም ጣልያኖች የውል ግዴታቸውን በመሻር ከቀረጥ ነፃ ይሆናል የተባለው መተላለፊያ ሳይፈቀድ ቀረ[57]።

አፄ ኃይለ ሥላሴ በማናቸውም ዓይነት በጭሰኝነት እንኳን ቢሆን ኢትዮጵያ የባህር በር እንዲኖራት ከጣልያን መሪ ጋር ተነጋግረው በኮንሴስዮን ሊሰጣቸው ታስቦ የነበረው ከጥቂት ሺህ ካሬሜትር የማይበልጥ እንደነበረ ይነገራል። ያም ሆኖ ይህንን ትንሽ የወደብ መሬትንም ሊያገኙ አልቻሉም[58]።

በእነዚህ አፍሪቃን በቅኝ ግዛትነት ጠቅልለው የያዙ አውሮፓውያን (ጣልያን፣ እንግሊዝና፣ ፈረንሳይ) ኢትዮጵያን ከቀይ ባህር በማግለል የባህር በር እንዳይኖራት ውስጣዊ ስምምነት አድርገው ስለነበር እስከ 1952 ዓ.ም. ኢትዮጵያ ወደብ አልባ ሆና ቀጠለች።

ጣልያኖች በአፍሪቃ ቅርምት ሊቢያና ሶማሊያ የደረሳቸው ሲሆን ሰፊዋና ለሟን ኢትዮጵያ በቅኝ ግዛትነት ይዞ ሃብቷን ለመበጥበጥ ለኑሮ ምቹና ነፋሻ በሆኑ አካባቢዎች ጣለያኖችን ለማስፈር ሲደክሙ ከቅኝ ግዛት አጋሮቻቸው ጋር ሲያሤሩ ብዙ ቆይተዋል። ስለሆነም እ.አ.አ. በ1933 ዓ.ም. ጦርነት ከፍተው ማይጨው ላይ ኢትዮጵያ ድል ሆና ለሚቀጥሉት አምስት ዓመታት ኢትዮጵያ በከፊልም ቢሆን በፋሽስት ጣልያኖች ሥር ማቃሰች።

ሁለተኛው የዓለም ጦርነት በቃል ኪዳን አገራት አሸናፊነት ከተደመደመ በኋላ፣ የኢትዮጵያ አርበኞችና እንግሊዝ ጣልያንን ከኢትዮጵያ አባረሩ። አጼ ኃይለ ሥላሴ እንግሊዞች ወደ ሥልጣናቸው እንደሚመልሷቸው ከተረዱ በኋላ ኤርትራን ከኢትዮጵያ ጋር ለመቀላቀልና ኢትዮጵያን የባህር በር ባለቤት ለማድረግ ወዲያውኑ ከፍተኛ የዲፕሎማቲክ ዘመቻ ጀመሩ[59]።

በዚህም መሠረት አሜሪካኖች ኤርትራ ወደ ኢትዮጵያ እንድትመለስና አገሪቱ የባህር በር እንዲኖራት እንዲደግፉ እ.አ.አ በ1943 ዓ.ም. አጼ ኃይለ ሥላሴ የውጭ ጉዳይ ምክትል

[57] Tseggai Mebrahtu, supra note 55.
[58] Ibid.
[59] Shumet Sishagne, Professor, supra note 43, P.98.



ሚኒስትራቸውን አቶ ይልማ ደሬሳን ወደ ዋሺንግተን ዲሲ ልከው አሜሪካኖችም ሃሳቡን ሊደግፉት እንደሚችሉ ለአቶ ይልማ አረጋገጡላቸው[60]።

አጼ ኃይለ ሥላሴ በፌብርዋሪ 13 1945 ዓ.ም. ከያልታ (Yalta) ስብሰባ መልስ የአሜሪካ ፕሬዝዳንት ሩዝቬልትን (Roosevelt) ባነጋገሩበት ወቅት ቀደም ሲል በጦርነቱ ጊዜ ጅቡቲ ደርሶ የነበረውን መከላከያ መሣሪያ ወደ አገር እንዳይገባ በፈረንሳይ መከልከሉ የተሰማቸውን ቅሬታ በምሬት ገልጸው የባቡር ግልጋሎት቏ ቢኖርም ኢትዮጵያ ሙሉ በሙሉ በመሬት የታጠረች በመሆንዋ በፋሽስቶች በጦርነቱ ለመሸነፍዋ ዋናው ምክንያት ይኸው ወደብ አልባ መሆንዋ ነበር ሲሉ ገለፁ። አጼ ኃይለ ሥላሴ ኢትዮጵያ ወደብ እንዲኖራት የአሜሪካን ዕርዳታ ጠይቀው ይኸም ሊፈጸም የሚቻለው ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር ስትዋሃድ መሆኑን ለሚስተር ሩዝቬልት አስረዱ።

አጼ ኃይለ ሥላሴ ኢትዮጵያን የወደብ ባለቤት ለማድረግ የማያወላውል አቋምና ፅኑ እምነት ስለነበራቸው ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር በፌዴሬሽን ከመተሳሰርዋ አምስት ዓመት ቀደም ብሎ እ.ኤ.አ በ1947 ዓ.ም "አዱሊስ፣ ባህረ ነጋሽና ወልወል" ብላ የሰየመቻቸውን ሦስት መርከቦች ገዝታ ቀይ ባህር ላይ አሰማርታቸው ነበር[61]።

አጼ ኃይለ ሥላሴ በአፍሪካና በሌሎችም አካባቢዎች መልካም ስምና ይልቁንም ትልቁ የአዓም አቀፍ የሕግና የዲፕሎማሲ ምሁር ጸሐፊ ትዕዛዝ አክሊሉ ኃብተወልድና ሌሎችም ባደረጉት እልህ አስጨራሽ ትግል ኤርትራ በ1952 ዓ.ም. በኤርትራ ሕዝብ ተወካዮች ፍላጐትና በተባበሩት መንግሥታት ውሳኔ ከኢትዮጵያ ጋር በፌዴሬሽን ተቀላቀለች። ለዘመናት ትግል ሲደረግለት የኖረው የባህር በር ጥያቄም በአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ዕውን ሆኖ ኢትዮጵያ የሁለት ወደብ ማለት የምጽዋና የአሰብ ባለቤት ሆነች። በሂደትም ፌዴሬሽኑ ፈርሶ ኤርትራ የኢትዮጵያ ሙሉ አካል ስትሆን የኢትዮጵያ የባህር በር ጥያቄ ለአንዴና ለሁሌም ዘላቂ መፍትሔ ያገኘ መሰለ። ፌዴሬሽኑ ፈርሶ ኤርትራ

[60] Ibid.
[61] Ibid

ከኢትዮጵያ ጋር ሙሉ በሙሉ ስትዋሃድ ሁሉቱም ወደቦች የኢትዮጵያ ሉዓላዊ ግዛት ሆኑ፡፡

ሆኖም የፌዴሬሽኑ መፍረስ የኤርትራ የመገንጠል ጥያቄ አስነስቶ ሻቢያ፣ ጀብሃ እና በኋላም ሕወሓት ኤርትራን ቅኝ ገዢ ከሚሉዋት ከኢትዮጵያ ነጻ ለማውጣት የትጥቅ ትግል ጀመሩ[62]፡፡

## *2.2.5. የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር መንግሥት (ደርግ) ኢትዮጵያ ወደብ አልባ እንዳትሆን ያደረገው ጥረት*

ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ያደረሳቸው መጠነ ሰፊና ዘርፈ ብዙ ጥፋቶች እንዳሉ ሆኖ በኢትዮጵያ ሉዓላዊነትና አንድነት ላይ ፅኑ አቋም እንደነበረው ጠላቶቹ እንኳን አሌ ሊሉት ያልቻሉ እውነታ ነው፡፡ ምናልባትም ይህ በሉዓላዊነት ላይ ያለው ግትር አቋሙ ለውድቀቱ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን አስተዋጽዖ አድርጎአል ማለት ይቻላል፡፡ ማለትም ደርግ የኤርትራን መገንጠል ተቀብሎ አገሪቱን ወደብ አልባ ቢያደርግ ኖሮ በሥልጣን ሊቆይ ይችል ነበር ወይ የሚለው ጥያቄ ሊያከራክር ይችላል፡፡

ጊዜያዊ ወታደራዊ ደርግ ገና ከመነሻው በ1967 ዓ.ም አሰብን ከኤርትራ ለመለየትና "የአፋር ነፃነት ንቅናቄ"ን (Afar Liberation Movement) ከሻቢያ ጋር ለማጋጨት በማሰብ ንቅናቄውን ጋበዞ በኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለ ማርያም መሪነት ውይይት ይካሄድ ነበር፡፡ በውይይቱም ይኸው ንቅናቄ ለኤርትራ ነፃነት ከሚዋጉ ኃይሎች ለመለየት በደርግ በኩል ብዙ ጥረት ተደርጐ ነበር፡፡

ደርግ ከ1967 ዓ.ም ጀምሮ ከኤርትራ ከማንኛውም ክፍል በላይ አሰብን አጥብቆ ይዞ ትኩረቱ ያሳረፈበት እንደነበር ይታወቃል፡፡ ኢትዮጵያ በሶማልያ ጦርነት ተጠምዳ ስለነበር ሻቢያ

[62] See Tekeste Negash. Professor ,Brothers at War Making sense of Eritrean-Ethiopan War (Eastern African Studies),(April 1,2001)



በአብዛኛው የኤርትራ ግዛቶች መንቀሳቀስ ችሎ በነበረበት ጊዜ እንኳን አሰብ ቁጥሩ ከፍተኛ በሆነ የኢትዮጵያ ጦር ጥበቃ ስር ስለነበረች ሻቢያ አንድም ጊዜ አሰብ ለመዘለቅ ባለመቻሉ በአካባቢው ሰላም ሰፍኖ ነበር[63]፡፡

የቀይ ኮከብ ዘመቻ ታውጆ ደርግ ከተሸነፈ በኋላ ምናልባትም ሻቢያንና ሕወሓት ሊቋቋማቸው የማይቻለው ኃይሎች መሆናቸውን ደርግ እራሱ እየተረዳ መጣ፡፡ የኤርትራ መገንጠልም ዕውን ሊሆን እንደሚችል ስለተገነዘበ የኢትዮጵያን የባህር በር ከመዘጋት የሚያድን የመሰለው አማራጭ የኢትዮጵያና የኤርትራንም ጨምሮ የውስጥ ድንበሮችን የሚያሸጋሽግ ቀመር ቀየሰ[64]፡፡ በማያያዝም ኤርትራ ተገንጥላ ብትሄድም አሰብን በኢትዮጵያ እጅ ለማቆየት እንዲቻል ዝግጅት ሲያደርግ ቆየ፡፡

ደርግ በቀየሰው ቀመር መሠረት አሰብን ራስ ገዝ አደርጎ ሙሉ በሙሉ ከኤርትራ መለየት ነበር፡፡ ራስ ገዝ አሰብ በቋንቋ፣ በባህል፣ በዘር፣ በጂኦግራፊም ሆነ በሕዝብ ሥነ ልቦና ከኤርትራ ጋር ምንም የሚያገናኛት ነገር አለመኖሩን በአፅንኦት ከአስቀመጠ በኋላ ነበር በአዋጅ ቁጥር 16/1980 አሰብን ራስ ገዝ አስተዳደር አድርጐ ያወጀው፡፡ የዚህም መሠረታዊ ዓላማው ኤርትራ ብትገነጠልም እንኳን አሰብን ለይቶ ወደ ኢትዮጵያ ማስቀረትና የኢትዮጵያ የባህር በር እንዳይዘጋ መከላከል ይቻላል ከሚል ግምት ተነስቶ ነበር፡፡

ደርግ አሰብንና ሌሎችንም ራስ ገዝ ያደረገበትን ምክንያት ሲያስቀምጥ የሰጣቸው ምክንያቶች በኢኮኖሚ ራሳቸውን መቻላቸው፣ በአውራጃው የብሔር ጥያቄ መኖር፣ የጂኦግራፊ አቀማመጥ፣ ለአስተዳደር አመቺነት፣ የሕዝቡ አንድ ጎሳ

[63] John Markakis, Resource and Conflict in the Horn of Africa. Thousand Oaks, Ca. Sage publications, (1998),p.188.

[64] Andargachew Tiruneh, The Ethiopian Revolution 1974-1987 A Transformation From an Aristocratic to a Totalitarian Autocracy. Press Syndicate of the University of Cambridge, Cambridge (1993), p 283.

መሆን፣ፖለቲካዊ እሳቤዎች፣የአገር ደህንነትን ከግንዛቤ በማስገባት እንደነበረ ገለጸ።

ደርግ እነዚህ ሁኔታዎችን ለራስ ገዝነት እንደ መሥፈርት ቢያስቀምጣቸውም ዋነኛው ዓላማው ግን አሰብን በሁሉም መልኩ ከኤርትራ ለይቶ ኤርትራ ብትገነጠልም አሰብን በመያዝ የኢትዮጵያ የባህር በር እንዳይዘጋ ለማረጋገጥ እንደነበር መገመት ይቻላል። ምክንያቱም እንደ አሰብ የአንድ ቋንቋ ተናጋሪዎች የብሔር ጥያቄ የሚንፀባርቅባቸው የአንድ የኢኮኖሚ ነፀብራቅ ወዘተ. የሆኑ ሌሎች ክልሎች ወይንም አውራጃዎች በሙሉ እንደ አሰብ ራስ ገዝ አልተባሉም። ድሬደዋና ኤርትራም ራስ ገዝ የተባሉበት ዋናው ምክንያት እንዲያውም ራስ ገዝ የሚል ቀመር የተቀረፀው አሰብን ከኤርትራ ለመለየትና ኤርትራ ከኢትዮጵያ ብትገነጠል አሰብን ወደ ኢትዮጵያ ማስቀረት ይቻል ይሆናል ከሚል እሳቤ መሆኑ ግልፅ ነበር።

ሆኖም እንደሚታወቀው ሁሉ ሻቢያ በጦርነቱ ደርግን አሸንፎ ኤርትራን በተቆጣጠራ ጊዜ አሰብም ከኤርትራ ጋር ከዚህ በታች እንደተገለጸው ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ ጠቀለለ። በኢሕአዴግ ቡራኬም አሰብን የኤርትራ አካል በማድረግ ኢትዮጵያ ለአርባ ዓመታት የተጠቀመችባቸውን የባህር በሮች ተነጥቃ ከዚህ በታች ያለው ሰሌዳ እንደሚያስረዳው በዓለም በሕዝብ ቁጥር ትልቋ ወደብ አልባ አገር ሆነች። በተጨማሪም በኢትዮጵያ ድንበርና በባህሩ መሃከል ያለው 60 ኪ.ሎ ሜትር በዓለም በአንድ አገርና በባህሩ ያለው እርቀት በጣም አጭሩ ለመሆን በቃ።



| ሰሌዳ 2 | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ተ.ቁ | አገር | የህዝብ ቁጥር | ተ.ቁ | አገር | የህዝብ ቁጥር |
| 1 | አፍጋኒስታን | 29,802,000 | 23 | ማሰዶኒያ | 506,928 |
| 2 | አንዶራ | 7,638 | 24 | ማላዊ | 15,263,417 |
| 3 | አርመንያ | 3,082,000 | 25 | ማሊ | 13,010,209 |
| 4 | አስትሪያ | 8,217,280 | 26 | ሞልዶቫ | 3,603,506 |
| 5 | አዘርባይጃን | 8,781,000 | 27 | ሞንጎልያ | 2,670,966 |
| 6 | ቤላሩስ | 9,049,000 | 28 | ኔፓል | 29,330,505 |
| 7 | ቡታን | 691,141 | 29 | ኒዠር | 15,263,417 |
| 8 | ቦሊቪያ | 9,362,860 | 30 | ፓራጓይ | 6,348,917 |
| 9 | ቦትስዋና | 1,949,780 | 31 | ሩዋንዳ | 9,997,614 |
| 10 | ቡርኪና ፋሶ | 15,756,927 | 32 | ሳንማሪኖ | 30,000 |
| 11 | ብሩንዲ | 8,303,330 | 33 | ሰርቢያ | 7,344,847 |
| 12 | ሴንትራል አፍሪካ ሪፑብሊክ | 4,000,004 | 34 | ስሎቫኪያ | 5,400,000 |
| 13 | ቻድ | 11,206,152 | 35 | ስዋዚላንድ | 1,184,936 |
| 14 | ቼክሪፐብሊክ | 10,500,000 | 36 | ታጂኪስታን | 6,250,000 |
| 15 | ኢትዮጵያ | 82,824,732 | 37 | ኡጋንዳ | 32,709,865 |
| 16 | ሃንጋሪ | 10,000,000 | 38 | ኡዝቤኪስን | 27,767,100 |
| 17 | ካዛኪስታን | 25,000,000 | 39 | ቫቲካን ሲቲ | 826 |
| 18 | ኪርጊስተን | 5,138,000 | 40 | ዌስት ባንክ | 2,514845 |
| 19 | ላኦስ | 6,800,000 | 41 | ዛምቢያ | 12,935,368 |
| 20 | ሌሴቶ | 3,066,919 | 42 | ዚምባብዌ | 12,891,000 |
| 21 | ሊተንሽንይን | 34,247 | 43 | ቱርክሚስታን | 4,254,000 |
| 22 | ሉክሱምበግ | 500,000 | 44 | ዌስት ባንክ | 2,514,843 |

*Source: Compiled from the Internet on February 20, 2011*

በአንዳንድ ሰዎች ስሌት ኢትዮጵያ ከ90 ሚሊዮን ሕዝብ በላይ ሲኖራት በዚህ ሰሌዳ መሠረት ግን የኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጥር 82,824,732 ነው ተብሎአል። እንደ አውሮጳውያን አቈጣጠር በ2015 የኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጥር ከመቶ አሥራ አምስት ሚሊዮን በላይ እንደሚሆን ይጠበቃል። በሕዝብ ብዛት ከኢትዮጵያ ቀጥሎ ያለው ወደብ አልባ አገር ኡጋንዳ ሲሆን የሕዝቡ ቁጥር የኢትዮጵያ አንድ ሦስተኛው ያህል (32,709,865) ነው። ቀጥሎም ሦስተኛዋ አገር ኔፓል ስትሆን እርስዋም 29,330,505 ሕዝብ ያላት ሲሆን ቫቲካን ሲቲ፤ ሉክስምቡርግ አንዶራና ሊሽተንታይን የአዲስ አበባን አንድ አምስተኛ አያህሉም።

## 2.2.6. የኢትዮጵያን የባህር በር ለማዘጋት ሕወሓት/ኢህአዴግ/ ያደረገው ጥረት

የሕወሓት መሪዎች ኤርትራን አስገንጥሎ ኢትዮጵያን ወደብ አልባ እንድትሆን የሰረጸባቸው ምኞት ገና በተማሪነታቸው "ማህበረ ገስገስቲ ብሄረ ትግራይ" የተባለው የተማሪዎች ማህበር ከአቋቋሙበት ጊዜ ጀምሮ ነበር። ወደ ሕወሓትነት ከተለወጡም በኋላ ይህንን ዓላማቸውን ከግብ ለማድረስ የኤርትራ ጥያቄ የብሔረሰቦች እኩልነት የማረጋገጥ ጥያቄ ሳይሆን የመገንጠልና ነፃ የመውጣት የቅኝ ግዛት ጥያቄ ነው በማለት የትግላቸውን አንኳር መሠረት ጣሉ። ይህንን ኢትዮጵያ የባህር በር የሚያሳጣ ኤርትራን ማስገንጠልና ደርግን ከሥልጣን ማባረር ዋነኞቹ ዓላማዎቻቸው ሆነው መሪዎቹ ይህንኑ በሕወሓት አባላትና በህዝቡ እንዲሰርጽ ቅስቀሳ ጀመሩ። ከሕወሓት ቀዳሚ መሪዎች አንዱ አቶ መለስ ዜናዊ በ1979 ዓ.ም ኤርትራን አስመልክቶ በጻፉት መፅሐፍ "…. ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ነች ማለት ትክክለኛና ሳይንሳዊም ነው"[65] ሲሉ ፅፈዋል። በተጨማሪም "…ኢምፔርያሊስቶች የዛሬይቱን አፍሪቃ እንደ ቅርጫ ሥጋ

[65] መለስ ዜናዊ <u>የኤርትራ ሕዝብ ትግል ከየት ወዴት</u>? (ግምገማ)፣ (1979 ዓ.ም), ገጽ 20.



ይከፋፈሉት የነበረበት ወቅት ስለነበር የማንኛውም አፍሪቃ አገር አንድ ወጥ ሆኖ መፈጠር የራሱ የታሪክ ምዕራፍ የመጀመር ታሪኩንም ከዚሁ ይጀምራል። አንድ አገር ሆኖ መፈጠርም በዚሁ ወቅት ይጀምራል"[66]። "ኢትዮጵያ የ3000 ዓመት ዕድሜ ያለው ጠንካራ ታሪክ የላትም። በአንድ በማእከላይ መንግስት በመተዳደር በሃገር ደረጃ መቆም ከጀመረች ከዳግማዊ ምኒልክ ዘመን ወዲህ የ100 ዓመት ዕድሜ አይሞላትም"[67] በማለት፣መጽሐፋቸው የኤርትራ ትግል እንዲያሸንፍ በመመኘት ይደመድማል። በዚህ አባባል የዛሬይቱ ኢትዮጵያ መቼም ቢሆን የጥንቷ የአክሱም ወራሽ ሆና አታውቅም። የአክሱም ወደቦችም ከኢትዮጵያ ጋር ግንኙነት አልነበራቸውም። ጥንታዊት ኢትዮጵያ የባህር በር ኖሮአት ስለማታውቅ ዛሬ የባህር በር ባይኖራት ምን ያስገርማል ለማለት የተሰነዘረ ይመስላል።

አቶ መለስ በኢትዮጵያ ውስጥ በኤርትራ ጥያቄ ላይ የጠራና ሳይንሳዊ አቋም ያኗቸው ዴሞክራቲክ ኃይሎች እንደነበሩ ይነግሩንና ሕወሓትም ከእነዚሁ ውስጥ መገኘቱን ገልጸው ሕወሓት ለዚህ ዓላማ ለብዙ ጊዜ መታገሉን ያስረዳሉ። አከታትለውም ይህ ኢትዮጵያ በኤርትራ ላይ የጫነችው የቅኝ ግዛት ቀንበር መደምሰስ እንደዋነኛ ዓላማው አድርጎ የተነሳው ሻቢያ የሚያደርገው ትግል መደገፍ እንዳለበት አቶ መለስ ያሳስባሉ። ሕወሓት የትግራይ ሕዝብን ለማሳሳት እንደሞከረ አቶ መለስ ሲገልጹ "ሕወሓት የትግራይ ህዝብ በኤርትራ ሕዝብ የመገንጠል ጥያቄ ላይ ትክክለኛ የድጋፍ አቋም እንዲይዝ አድርጓል " ይላሉ። ዘለዓለም በኢትዮጵያ ሉዓላዊነት ላይ የተሰነዘሩ ጥቃቶችን በመመከት የወራሪዎች ቀዳሚ ገፈት ቀማሽ የሆነው የትግራይ ሕዝብ የኤርትራን መገንጠልን ደግፎ አገሩን ወደብ አልባ የማድረግ የሕወሓት ስብከት ተቀብሎ ነበር ብሎ ጠላቱም ቢሆን አያማውም። በሕወሓት መሪነት ግን ኤርትራን ከኢትዮጵያ "ቅኝ ተገዥነት" ነጻ ለማውጣት በኮሎኔል አምሳሉ ገብረዝጊ አባባል "የትግራይ ልጆች በማይመለከታቸው ጉዳይ ወደ

[66] ዝኒ ከማሁ ገፅ 6.

[67] ዝኒ ከማሁ.

ኤርትራ መሬት ሄደው ጸረ ኢትዮጵያ ለሆነው ለሻቢያ ወታደራዊ ድጋፍ በመስጠት ቀስለዋል፤ ሕይወታቸውንም አጥተዋል"[68]፡፡

አንዳንድ የሕወሓት መሪዎች ኢትዮጵያ የአክሱም ወራሽ አይደለችም የሚለው አቋማችው እስከ ዛሬም ይዘው እንደቀጠሉበት ነው፡፡ "ኢትዮጵያ የአክሱም ወራሽ አይደለችም፤ እንደ አገር ከተቋቋመች ከመቶ ዓመት አይበልጥም፤ ኤርትራ በኢትዮጵያ ቅኝ ግዛትነት ተይዛለች" እየተባለ በሕወሓት መሪዎች የተሰፈሩ ኃላፊነት የጉደላቸው አባባሎች ከሃያ ዓመታት በፊት የተባሉ ከመሆኑም በላይ በጊዜው ከዕውቀት ማነስና ከዕድሜ ለጋነት የመነጩ ይሆናሉ ተብሎ ሊታለፉ ይቻል ነበር፡፡ ሆኖም ግን እነዚህ ሰዎች አቋማቸውን ስለ መቀየራችውና በአባባሎቻቸው ስለ መጸጸታቸው ምንም ያሳዩት ወይንም ያሉት ነገር ካለመኖሩም በላይ በተለይ ኤርትራ የኢትዮጵያ "ቅኝ ግዛት" ነበረች የሚለው አቋማቸውን ዛሬም እንደገፉበት ነው፡፡

ይህንኑ በኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 39 እና በአልጀርስ ስምምነት በማያጠራጥር መልኩ አረጋግጠዋል፡፡ አንቀጽ 39 የመጀመሪያው ክፍል ኢትዮጵያ ውስጥ ያለ ማንኛውም ብሔረሰብ አንዳንድ ፎርማሊቲዎችን እስካሟላ ድረስ ውሃ ቀጠነ ብሎ መገንጠል እንደሚችል በግልጽ ይደነግጋል፡፡ እንዲህ ዓይነት ቅድመ ሁኔታ ወይንም ምክንያት አልባ መገንጠል የዓለም አቀፍ ሕግ የሚፈቅደው ተገንጣዩ የሌላው አገር ቅኝ ግዛት ከነበረ ነው[69]፡፡ ሕወሓት/ኢሕአዴግም የኤርትራን መገንጠል የደገፈው ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ነች ከሚል እምነት ተነስቶ ነው፡፡ ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ነች ካለ ደግሞ ነፃነትን ወይንም መገንጠልን ከመደገፍ ሌላ አማራጭ አልነበረውም፤ ምክንያቱም ቅኝ ግዛት የሆኑ አገሮች ነፃ የመውጣት ያልተገደበ መብት ስላላቸው የተቀረው የዓለም አቀፍ

---

[68] አምሳሉ ገብረዝጊ (ኮሎኔል) <u>የኤርትራ መዘዝ</u> አዲስ አበባ ፤ጥር 11 ቀን (2002 ዓ.ም) ፤ገጽ 52

[69] Macolm N. Shaw, <u>International Law, 6th edition,</u> Cambridge, university press, (2008) p. 257.



ሕብረተሰብ ድጋፉን እንዲለግሳችው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ስለሚያሳስብ ነው፡፡

እንዲሁም በአልጀርስ ስምምነት አንቀጽ 41 ኢትዮጵያና ኤርትራ ለወሰናቸው መካለል የአፍሪቃ አንድነት ድርጅት የካይሮው የመሪዎች ጉባዔ እ.አ.አ በ1964 ዓ.ም ያሳለፈው ውሳኔ ለድምበር ኮሚሽኑ ውሳኔ ኢሕአዴግ መሠረት ሲያደርገው ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ነች ከሚል እምነት ተነስተው ነው፤ ምክንያቱም ይህ የአፍሪቃ አንድነት ድርጅት የመሪዎች ጉባዔ ውሳኔ አግባብነት የሚኖረው ከቅኝ ግዛት ነጻ ለሚወጡ አገሮች ብቻ ነው፡፡ ይህም ውሳኔ ቅኝ ግዛት የነበሩ የአፍሪቃ አገራት ነፃ ሲወጡ በቅኝ ግዛት ጊዜ የነበረው ወሰን መከበር አለበት የሚል ሲሆን ሕወሓት ይህንኑ ተቀብሎ ኤርትራ የኢትዮጵያ "ቅኝ ግዛት" በነበርችበት ጊዜ የነበራትን ድንበር እንዲከበርላት ተስማማ፡፡

እነዚህን የቅኝ ግዛት መርሆዎችውን በመከተል ሻቢያና ሕወሓት ፓሊሲዎቻቸውን ቀርፀው በመታገላቸው ቅኝ ግዛት ይ኏ት የነበረችው ኤርትር ዛሬ ነፃ ወጥታለች፡፡ ለመሆኑ የሕወሓትና አንዳንድ የሌሎች የኢትዮጵያ ብሔርና ብሔረሰቦች መሪዎች አገሮች ቅኝ ግዛት ናቸው ሲሉ ቅኝ ግዛት ምን ማለት እንደሆነ፣ የቅኝ ገዢዎቹ ዓላማና ፍላጐት ምን እንደሆነ፤ እነዚህ ሁኔታዎች በኢትዮጵያ ውስጥ ይንፃባረቁ እንደሆነ በቅጡ ተገንዝበውታልን የሚል ጥያቄ ያስነሣል፡፡

ቅኝ ግዛት በመሠረቱ ከ15ኛው እስከ 20ኛው በነበረው ክፍለ ዘመን አውሮፓውያን ወደ ሌሎች አህጉራት ተሻግረው በአገሬው ሕዝብ ላይ የጫኑት የአገዛዝና የብዝበዛ ሥርዓት ነበር፡፡ ዓላማቸው ትርፍ ፍለጋ በቅኝ ግዛቱ ተገዢው ሕብረተሰብ ኪሳራ ለመበልፀግና፤ የሃይማኖት ወይንም የፖለቲካ እምነት ለማስፋፋት ነበር፡፡ ቅኝ ግዛት በአገሬው ተወላጆችና በወራሪ መጤዎች መሃከል የጌታና የሎሌ ግንኙነት ይመሠረታል፡፡ ቅኝ ገዢዎች በዋና ከተሞቻቸው ተቀምጠው የቅኝ ግዛቱ አገርና ሕዝብ የእለት ተእለት ኑሮውና መጻኢ እድሉን ይወስናሉ፡፡ ቅኝ ገዢዎች የተገዢዎችን ባህል በማንቋሸሽ ሰብእናቸውን በማሳነስ የበታችነት ስሜት እንዲሰርጽባቸው አድርገዋቸዋል፡፡ ቅኝ ገዢዎች እነዚህን ሕዝቦች ለመግዛት የተፈጠሩ ናቸው የሚለውን እምነት

በተገዢዎች ላይ በማሳደር በንብረትና በህይወታቸው ወሳኝ ሆነው ኖረዋል[70]።

ቀደም ሲል የሕወሓት መሪዎች የማርክሲስት ሌኒኒስት እምነት አክራሪ ተከታዮች (የአልቤንያው ዓይነት) ስለነበሩ የኢትዮጵያና የኤርትራ ግንኙነት በዚህ በማርክሲስት መነፅር ያዩት ነበር። በማርክሲስት ሌኒኒስቶች አስተሳሰብ የቅኝ ግዛት ዋናው ዓላማ ተገዢውን ሕዝብ መበዝበዝ ነው። የቅኝ ግዛት ሥርዓት የተቀነባበረ ብዝበዛ እያካሄደ ለቅኝ ገዢዎች ኢንዱስትሪ ጥሬ ዕቃ በጣም በእርካሽ ዋጋ ወይንም በነፃ ማቅረብ ሲሆን፣ ምርቱንም በተገዢው ሕብረተብ ለይ መገልበጥና እንዲሁም የቅኝ ተገዢው መሬቱን ነጥቆ ለቅኝ ገዢዎች ማከፋፈል ነው።

በእነዚህ የቅኝ ግዛት መስፈርቶች ሲለካ የኢትዮጵያና የኤርትራ ግንኙነት የቅኝ ገዥና ተገዥ ነበረ የሚያስብል አንድም ምክንያት የለም። ኢትዮጵያ ለየትኞቹ ፋብሪካዎቿ ነበር ኤርትራን የምትበዘብዘው? በወቅቱ እንዲያውም የጥሬ እቃው ትራፊክ የሚያመዝነው ከኢትዮጵያ ወደ ኤርትራ ሲሆን በጊዜው ኤርትራ ውስጥ የነበሩ ኢንዱስትሪዎች ኢትዮጵያ ውስጥ ከነበሩት በቁጥር ይበልጡ ስለነበር የፋብሪካ ምርቶች ከኤርትራ ወደ ኢትዮጵያ ይጓዙ ነበር።

በኢትዮጵያውያንና በኤርትራውያን መሃከል የነበረው ግንኙነት የጌታና የሎሌ ሳይሆን የመከባበርና የመፈቃቀር፣ የወንድማማችነትና የእህትማማችነት እንደነበር አንዳንድ ኤርትራውያን ከኢትዮጵያ በተባረሩ ጊዜ በግልጽ ታይቶአል። አንዳንድ ኢትዮጵያውያን ኤርትራውያን ጎረቤቶቻቸውንና ወዳጆቻችውን ወደ ኤርትራ እንዳይላኩ ደበቀው መከላከል ሲያቅታቸው ደግሞ በእምባ እየተራጩ የሸኙባቸው ሁኔታዎች ታይተዋል።,

የትኛውስ የኤርትራ ለም መሬት ነው ኢትዮጵያውያን ከኤርትራውያን ነጥቀው የሰፈሩበት። ይልቁንስ ኤርትራውያን በተለይ በአፄ ኃይለ ሥላሴ የአስተዳደር ዘመን በኢትዮጵያ

[70] Colonialism, http://en.wikipedia/wiki/colonialism.com. Accessed on 22 January 2011.



በከፍተኛ የሥልጣን እርከን በመገኘት በተጨማሪም በነበራቸው የሥራ ትጋትና ተሞክሮ በተለያዩ የሥራ ዘርፎች ተሰማርተው ሃብት አፍርተው ከብረውና ከብደው ያለ አንዳች ስጋት ከተቀረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጐን በፍቅር ይኖሩ እንደነበር የትናንት ሐቅ ነው። ስለዚህ የኢትጵያ አካል የነበረችው ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ነበረች ማለት "ትንሽ ዕውቀት አደገኛ ነው" Little Knowledge is Dangerous ከሚለው የእንግሊዘኛ ብሂል የመነጨ ይመስላል።

ዛሬ ኢትዮጵያ የባህር በር አያስፈልጋትም በጐረቤት አገራት ወደቦች እንጠቀማለን የሚሉ የሕወሓት መሪዎች በአንድ በኩል ኤርትራን ለማስገንጠል ሲጥሩ በሌላ በኩል ደግሞ በመጀመሪያ ታላቋ ትግራይን ፈጥረው የትግራይ ሪፐብሊክን አቋቁመው የቀይ ባህረ ሰላጤን ከታላቋ ትግራይ ጋር ለመቀላቀል ወጥነው እንደነበር ፕሮፌሰር ተኮላ ወርቅ ሃጎስ ያስገነዝቡናል[71]።

ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ነችና እንደማንኛውም ቅኝ ግዛት ነፃ መውጣት አለባት፤ ለዚህም የተራማጆች ድጋፍ የግድ ይላል የሚለው የጨቅላ አስተሳሰብ ከሕወሓትም ውጭ ሌሎችም ተስፈንጣሪ ማርክሲስት ሌኒኒስት እርዮተ ዓለም ይከተሉ የነበሩ ጥቂት ኢትዮጵያውያንም የሚያራምዱት አቋም ነበር። እነዚህ ጥራዝ ነጠቆች ቅኝ ግዛት ምን እንደሆነ፣ ቅኝ ገዥውና ተገዢው ምን ዓይነት የኢኮኖሚ፤ የፖለቲካና የሶሻል ግንኙነት እንዳላቸው ተንትነው ተረድተው ሳይሆን፤ በጊዜው ተራማጅ መስሎ ለመታየት የኤርትራንና የሌሎች ጎሳዎች መገንጠልን መቀበልና ማጠንጠን ያስፈልግ ስለነበረ ነው።

ከዚህም አልፎ በእነዚህ ሰዎች አስተሳሰብ ማንኛውም ኤርትራዊ ነገር መወደስ ሲገባው ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ጉዳይ ደግሞ መንኳሰስ ነበረበት፤ በኢትዮጵያዊነት የሚያኮራ ምንም ነገር አልነበረም። ጸረ ኮሎኒያሊስት ድሎች እንኳን ፊውዳሎችን

[71] Tecola W. Hagos, Professor, "Prime Minister Meles Speaks at the National Press Club in Washington DC" http://ethioembassy.org.UK. Accessed on Febrary 2011.

በሥልጣን ለማቆየት ካልሆነ በቀር ለሰፊው ህዝብ የሰጡት ጥቅም የለም በማለት ሲያንኳስሱ ተደምጠዋል። እንዲያውም ጉዳቱ አመዝኖአል ሲሉ የሚከራከሩም አልጠፉም። በእነዚህ ሰዎች እይታ ኤርትራውያን ለ60 ዓመታት በጣልያን ስለተገዙ እንደሰለጠኑ ሲቆጥሩአቸው ኢትዮጵያውያንን ግን ትናንት ከዛፍ የወረዱ አድርገው የሚያዩ ነበሩ።

እነዚሁ ተስፈንጣሪ ግራ ዘመም እምነት ተከታይ ኢትዮጵያውያን በበታችነት ስሜት (Inferiority complex) ተለክፈው ስለነበር ኤርትራውያን ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ይበልጥ በተፈጥሮ ብልህ (Intelligent) ናቸው ከማለት እንኳን አይመለሱም ነበር።

ከኢትዮጵያውያን ተራማጅ የፖለቲካ ድርጅቶችም አንዳንዶቹ ኤርትራውያን ለሰብአዊና ለፖለቲካዊ መብቶቻቸው ሲታገሉ ሊደገፉ ይገባል ከማለት ሌላ ከሕወሓት በስተቀር ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የፖለቲካ ቡድን ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ነች፤ ተገንጥላ ነጻ ትውጣ፤ የኢትዮጵያና የኤርትራ ህዝብ ይለያዩ ፤ የኢትዮጵያ የባህር በር ይዘጋ ያለ የለም።

በጊዜው ዋነኞቹ ተራማጅ ይባሉ የነበሩ የፖለቲካ ፓርቲዎች የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) እና የመላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ (መኢሶን) በኤርትራ መገንጠል ተመሳሳይ አቋም ያራምዱ ነበር። ኢሕአፓ በኢትዮጵያ በሙሉ በኤርትራም ጭምር በደርግ ይደረግ የነበረውን ጨካኝና መጠነ ሰፊ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን በፅኑ ተቃውሞአል። በዚህም ትግል ወጣት የኢሕአፓ አባላትና መሪዎች ከባድ መስዋዕትነት እንደ ከፈሉ የትናንት ትዝታ ነው። ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ነችና ነፃ ትውጣ፤ የባህር በሯ ይዘጋ የሚል አቋም ኢሕአፓ እንዲቀበል ሻቢያ ከፍተኛ ጫና ቢያደርግበትም ኢሕአፓ ይህን አቋም ለማራመድ እስከ መጨረሻው ፈቃደኛ አልሆነም። በዚህም ምክንያት ኢሕአፓ ከሻቢያና ከሕወሓት ጋር ከፍተኛ ውዝግብ ውስጥ ገብቶ በዚህም አቋሙ በሻቢያ በሚያደግፈው ሕወሓት ግፊት አሲምባን ለቅቆ እንዲወጣ ተገድዶአል። መኢሶንም በጊዜው የደርግ ፖሊሲ ተጋሪ ወይም [illegible] ተያሽ ስለነበር



ኤርትራ ተገንጥላ አገሪቱን ወደብ አልባ ማድረግን በጽኑ ይቃወም ነበር።

ሕወሓት/ኢህአዴግ ገና ከጅምሩ በ1983 ዓ.ም አዲስ አበባ ለመግባትና ሥልጣን ለመጨበጥ በሚያከብብበት ወቅት በሻቢያ፣ በኢሕአዲግ፣ በደርግና በኦሮሞ ነፃ አውጪ ግንባር (ኦነግ) መሃከል በአሜሪካ አደራዳሪነት ለንደን ስብሰባ ተቀምጠው በነበረ ጊዜ ኢሕአዴግ ከኦነግ ጋር ሥልጣን ተጋርቶ አዲስ አበባ ገብቶ በትረ ሥልጣኑን እንዲጨብጥ፤ ኤርትራም ነፃ እንድትወጣ ሲወሰን በድርድሩ ላይ ወሳኝ ሚና ይጫወት የነበረው አደራዳሪው አሜሪካዊው ባለስልጣን ኸርማን ኮኸን (Herman Cohen) የኢትዮጵያ የባህር በር መብት ጉዳይ አንስቶ እንደነበር ይነገራል።

በዚህ ጊዜ የሕወሓት/ኢሕአዴግ ቡድን መሪ አቶ መለስ ዜናዊ አደራዳሪው ያነሳው ጥያቄ ለድርድሩ ምንም አግባብነት እንደሌለው በመግለጽ የኢትዮጵያ የባህር በር መብት ጥያቄ በዚሁ ተቋጭቶ በፕሮፌሰር ቢጋዬ መብራሕቱ አባባል "በአንድ ሰው የግድየለሽነት ኢትዮጵያ በ60 ዓመታት ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ከቀይ ባህር ሰላጢ (Red sea littoral) ሙሉ በሙሉ ተገለለች።

የሕወሓት መሪዎች የአልጀርስ ስምምነት ድርድር ከመጀመሩ ቀደም ብሎ የሕወሓትን ፖሊሲ በማንፀባረቅ በተደጋጋሚ በተለያዩ ሚድያዎች አሰብ የኤርትራ አካል ነች፤ ወሰን መካለሉም አጼ ምኒልክ ከጣልያኖች ጋር በፈረሙአቸው ውሎች መሠረት እንደሚሆን አስታውቀው ነበር። ይህም በአቶ ብላይ አባይና በአቶ ዘርሁ ክሂሽን እይታ ገና በድርድሩ ወቅት ኢትዮጵያ አሰብ ይገባኛል የሚል ጥያቄ እንደማታነሳ በድርድሩ ተሳታፊ ለነበሩት ለኤርትራ መንግሥት፤ ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ለአፍሪካ አንድነት ድርጅት፤ ለአውሮፓ ሕብረትና ለዩናይትድ ስቴትስ ለማስታወቅ ነበር። እነዚህ የድርድሩ ተሳታፊዎች

ቢያነሱት እንኳን በኢሕአዴግ በኩል ተቀባይነት እንደማይኖረው ለማስታወቅና በቅድሚያ ጥያቄው በእንጭጩ ለማስቀረት ነበር[72]።

ሕወሓት የኢትዮጵያ የባህር በር መብትን ማስከበርና አሰብን ወደ ኢትዮጵያ የመመለስ ሃሳብ ጭራሹኑ እንደሌለው የሚያመላክት የኢሕአዴግ የአሁንም ይሁን የወደፊት ፖሊሲው አቶ መለስ ዜናዊ ከአስመሪኖ ድሬ ገፅ ባለቤት ከአቶ ተስፋ ልደት መሐረነ ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ ቁልጭ አድርገው አስቀምጠውታል።

አቶ መለስ እንዳሉት "ይህ አሰብን እንይዛለን÷ እንወርራለን የሚል አካሄድ ከዚያው ከዘውዳዊ ትምክሕቷዊ አስተሳሰብ የሚመነጭ ነው። ሁለተኛ ደግሞ ይህ አስተሳሰብ የተጠናወታቸው ሰዎች ከዘመነ ግሎባላይዜሽን ጋር አብረው ሊሄዱ ያልቻሉ ከድንጋይ ዘመን አስተሳሰብ ያልተላቀቁ ናቸው።....አሰብን ካልያዝን እያሉ ይፎክራሉ። ተግባራዊ ለማድረግ በአሰብ ላይ ወረራ እስካልተፈፀመ ድረስ እርምጃ ልንወስድባቸው አንችልም"[73] ብለው ነበር። ከዚህ በተቃረኒ አቶ መለሰ ዜናዊ በአንድ ወቅት ከሲ.አይ.ኤው ፓል ሄንዝ ጋር ባደረጉት ምሥጢራዊ ውይይት "ትግራይ የባህር በር እንዲኖራት እንፋልጋለን። ይህ ደግሞ የሚሆነው በኤርትራ በኩል ነው። ኤርትራ የኢትዮጵያ አካል ሆነችም አልሆነችም ወደብ ያስፋልገናል"[74] ብለው ነበር። ትግራይ የኢትዮጵያ አካል እንደመሆንዋ መጠን ወደብ ብታገኝ ጥቅሙ ለመላው ኢትዮጵያ ስለነበር ትግራይ ወደብ ቢኖራት ኢትዮጵያውያን እሰይ ባሉ ነበር። ይህ ትግራይ ወደብ ያስፈልጋታል የሚለው የአቶ መለስ አቋም መቼና ለምን እንደተቀየረ አይታወቅም።

ይኸ ሁሉ የአቶ መለስ ማስፈራሪትና ስጋት ለምን እንዳስፈለገ ግልፅ አይደለም። ምክንያቱም የወደፊቱ ባይታወቅም እስካሁን

[72] Belai.Abbal.and.ZeruKehishen,http://Ethiopians.com/belai_and_zeruml July 15, 2000. Accessed May 22, 2010

[73] See WWW.Ethiomedia.com accessed on December 12, 2010

[74] "የመለስና የ ሲ፡አይ፣ኤው አባል ምስጢራዊ ውይይት" [illegible]ራምባ ታይምስ ቅዳሜ ሰኔ 4,2003.



በፅሁፍም ይሁን በቃል አንድም ኢትዮጵያዊ የኢትዮጵያ የመከላከያ ኃይል ታንክ አሽከርክሮ ሳንጃ ወድሮ አሰብ ዘልቆ በጦር ኃይል አሰብን ይያዝ ያለበት ጊዜ የለም።

ይህም ማለት ግን የአሰብ ጉዳይ በሰላማዊ መንገድ ብቻ ይስተናገድ የሚለው አቋም ለወዳፊት ሊሸረሸር አይችልም ማለት አይደለም። እንዲያውም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ሉዓላዊ ግዛታችን አሰብን አስፈላጊ በሆነ በማንኛውም መንገድ ሁሉ ማስመለስ ይገባል የሚሉ ኢትዮጵያውያን ቁጥር እየተበራከተ ሄዷል።

ከላይ በተጠቀሰው በአቶ መለስ አባባል ኢሕአዴግ የኤርትራ አካል አድርጎ በሚቆጥረው በአሰብ ላይ ጥቃት ቢደርስ ኢሕአዴግ የኢትዮጵያ ወጣቶችን በማሰለፍ ኤርትራን እንደሚታደጉ አቶ መለስ ግልጽ አድርገውታል። እነዚህ አባባሉችን በማጠናከር አቶ ስብሐት ነጋም ለድምፅ ወያኔ ሬድዮ በሰጡት ቃለ ምልልስ ሕወሓት/ኢሕአዴግ አሁንም ቢሆን የኤርትራ ሉዓላዊነት የሚፈታተን ኃይል ከመጣ ሕወሓት/ ኢሕአዴግ ከኤርትራ ሕዝብ ጎን እንደሚቆም አረጋግጠዋል። ይህ የአቶ ስብሃት ነጋ አባባል እንዴት እንደሚያዩት አቶ መለስ ተጠይቀው ሲመልሱ "ከድርጅታችን መግለጫዎች አብሮ የሚሄድ ይመስለኛል" ብለው ነበር።

ሌላው የኢሕአዲግ የአሰብ ፖሊሲ ጠቋሚ የሚሆነው የመንግስት ኮሙኒኬሽን ሚኒስትር አቶ በረከት ስምዖን ለእንግሊዝ ብሮድካስቲንግ ኮርፓሬሽን ባልደረባ ለሚስተር ሮቢን ኂይት ጥያቄዎች የሰጡት መልስ ነው። .

ሚስተር ሮቢን ኂይት አሰብን አስመልክቶ አቶ በርከትን ለጠየቋቸው ጥያቄዎች እንደሚከተለው መልሰውልታል፡-

*እኛ የአሰብን ወደብ አንፈልገውም። መንግሥታችን አቋሙን በግልጽ ነው ያስቀመጠው፤ በአልርስ ስምምነቱ ላይ የትኞቹ አካባቢዎች የእኛ እንደሚሆኑ በትክክል አስቀምጠናል። በዚህ ወቅት የአሰብ ወደብ ከጥያቄአችን ውስጥ አልተካተተም። ጥቂት ኢትዮጵያውያን የአሰብን ወደብ የኢትዮጵያ ግዛት አድርገው ያስባሉ። ነገር ግን አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝቦች*

*አሰብን አይጠይቁም፡፡ ምክንያቱም የአሰብ ወደብ የኤርትራ ሉዓላዊ ግዛት መሆኑን ስለሚያውቁ ነው፡፡ አሰብ የኢትዮጵያ የተፈጥሮ የባህር በር ነች ይላሉ፡፡ ጅቡቲም ቢሆን እንደዚሁ ተመሳሳይ ጠቀሜታ አለው፡፡ የቅኝ ግዛት ውሉች አሰብን የኢትዮጵያ አካል አድርገው ባለማካለላቸው የይገባኛል ጥያቄ ለማንሳት የምንሔድበት ምክንያት አይኖርም*[75]፡፡

አቶ በረከት እንደሚሉት ጥቂት ኢትዮጵያውያን አይደሉም አሰብ የኢትዮጵያ ግዛት ነች የሚሉ፡፡ ሁልቄ መሣፍርት ከሊቅ እስከ ደቂቅ ከገበሬው እስከ ምሁሩ በጠቅላላው መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው አሰብ የኢትዮጵያ ነች የሚለው፡፡ በቤተ መንግሥት ቅጥር ግቢ ሳይወሰኑ እንደልባቸው በአዲስ አበባና በተቀረው የአገሪቱ ከተሞችና በገጠሩም ተዘዋውረው በማየትና በመስማት ከአቶ በረከት ይበልጥ አሰብን በተመለከተ የህዝቡ ስሜትና እምነት ሊያውቁና ሊገመግሙ የሚችሉት አቶ ኃይለ ሚካኤል ገብረ አናንያ ከሕዝቡ የሚከተለውን አድምጠዋል፡፡ "ይሄ የባህር በር ጉዳይ የኢትዮጵያ ሕዝብ ተቀብሎታል ብሎ ዝም ማለት ያስቸግራል፡፡ ምክንያቱም ሕዝቡ በየሆቴሉና በየካፌው የሚናገረው ስለዚህ ጉዳይ ነው፡፡ በፖለቲካ ስብሰባ የሚናገረው ይሄንኑ ነው"[76] በማለት የታዘቡትን ገልጸዋል፡፡

በደርግ፤ በሕወሓትና በሻቢያ መሃከል የተደረጉ ፍልሚያዎችን አስመልክቶ የፓለቲካና የጦርነት ትንታኔ በማድረግ ጥልቅ ምርምር የደረጉት ፕሮፌሰር ገብሩ ታረቀ የሚከተለውን ጽፈዋል፡፡ "...ሕወሓት ትግራይ ውስጥ ደርግን ባያሸንፍ ኖሮ የኤርትራ ነፃነት ለዛላለም ባይሆንም ላልተወሰነ ጊዜ ሊዘገይ ይችል ነበር" ብለዋለል፡፡ ይህም ማለት ሕወሓት ሻቢያን በጦርነቱ ባይረዳ ኖሮ ኤርትራ ከኢትዮጵያ በጦር ኃይል የመገንጠልና የባህር በር መዘጋት እጅግ ቢያንስ አጠራጣሪ በሆነ ነበር፡፡[77]የሕወሓት ሻቢያን

---

[75] BBC Interview with Mr.Robin White circa 2001

[76] ኃይለ ሚካኤል ገብረአናንያ ሪፖርተር ‌፤እሁድ የካቲት 7 ቀን 2002 ዓ.ም.

[77] Gebru Tareke , Professor, The Ethiopian Revolution War in the Horn of Africa, Yale University Press, New Haven & London, (2009), P321.



መርዳት ቀደም ሲል በሻቢያና በደርግ መሃከል ተደጋግም የተሞከረው የሰላም ድርድር እንዲቀር አስተዋጽኦ አድርጎአል*፡፡

የባህር በር አስረካቢዎች አቋም ለማጠቃለል ያህል፤ ኢሕአዲግ አሰብን ለኤርትራ ለማስረከብ የነበረው ጉጉት ጥቅምት 11 ቀን 1995 ዓ.ም በወጣው የኢሕአዴግ ልሣን የሆነው አብዮታዊ ዴሞክራሲ ጋዜጣ የጻፋውን በመገመገም ኢትዮጵ የተባለው ሳምንታዊ መጽሔት የሚከተለውን ጽፎአል "......ኢትዮጵያ አወዛጋቢነት በሌላቸው ቦታዎች ማለትም በመላው ምሥራቃዊ ወሰን ....ድንበሩ በአስቸኳይ እንዲካለል የኢሕአደግ መንግሥት የሚያደርገው ግፊት ታዛቢዎችን አስገርሞአል፡፡ የአሰብ ወደብ የኤርትራ ግዛት ሆኖ እንዲቀጥል ተጨማሪ ማረጋገጫ እንዲሰጥ ከኤርትራ በላይ የኢትዮጵያ መንግሥት የሚያደርገው ግፊትና አቶ መለስ ቀይ ባህር ሲነሳባቸው የሚበሳጩበት ምክንያት ከማስገረምና ከማሳዘኑም አልፎ ይበልጥ አሳሳቢ ሆኖአል"[78]

የሕወሓት መሪዎች የኢትዮጵያን ዋባህር በር አዘግተዋል ሲባል የሁሉም የሕወሓት አመራሮችን አያጠቃልልም፡፡ ጥቂትም ቢሆኑ በጊዜው ድምጻችው ባይሰማም የኢትዮጵያ የባህር በር አልባ መሆንዋ የሚቈረቁራቸው አንዳንድ የሕወሓት የአመረር አባላት እንደነበሩ አቶ አሰግድ ገብረ ሥላሴ የሕወሓት መሥራች አባልና የዓረና ትግራይ ማዕከላዊ ኮሚቴ አባል ከአውራምባ ታይምስ ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ ገልጸዋል፡፡ በዚሁ ቃለ ምልልሳቸው "ኢሕአዴግ በታሪኩ ዴሞክራሲያዊ ሆኖ አያውቅም፡፡ የተለየ ሃሳብ የሚያቀርቡ ወገኖችም ጠላት አድርጎ ስለሚያያቸው ባለው አቅም ሁሉ ለመታገል ወደ ኋላ አይልም" ካሉ በኋላ ኢሕአዴግ [የኤርትራን መንግሥት] ለማስወገድ በቅርቡ የአቋም ለውጥ አድርጎአል ወይ ለሚለው ጥያቄ ሲመልሱ "ዋናው ነገር ይኸ የኤርትራ መንግሥትን የማስወገድ ነገር እስከ የት ድረስ ይሄዳል? ያለ አግባብ ያጣናቸውን መብቶቻችን ያረጋግጥልናል ወይ? የባህር በር ባለቤትነታችንስ ያረጋግጥልናል ወይ? የሚሉት መመለስ

---

* ፕሮፌሰር ገብሩ በሻቢያና በኢትዮጵያ መንግሥት መሃከል አውሮፓ ውስጥ ብዙ ውይይቶች ተደርገው እንደነበር ይጠቅሳሉ፡፡

[78] ኢትዮጵ፤ ጥቅምት 18 ቀን 1996 ዓ.ም

አለባቸው" ሲሉ እነዚህ እስካልተፈጸሙ ድረስ ግን የኤርትራ መንግሥት መወገድ ፍሬ ከርስኪ መሆኑን ገልጸዋል። ስለ አንዳንድ የሕወሓት መሪዎች ለኤርትራ ያላቸው ተቈርቋሪነትና ስለአሰብ ኢትዮጵያዊነት ሲገልጹ አቶ አስገድ የሚከተለውን ብለዋል።

*ይህ ታላቅ ነጥብ ነው ። ይኸ ሸንጥን ጉትሮ [ለኤርትራ] ጥብቅና መቆም በትግሉ ወቅትም ነበር ። ያን ጊዜ የአሰብ ጉዳይ ሲነሳ እንኳን ልዩነታችን የሁለት አገር ዜጎች የሆንን ያህል እስከ መወዛገብ ያደርሰን ነበር። በምንም አግባብ አሰብ የኤርትራ እንዳልሆነች ይታወቃል። እነዚህ የሕወሓት አመራሮች ግን ይህንን ሃሳብ የምናነሳውን ትምክህተኞች ይሉን ነበር። ነገሩ በቅስቀሳ ብቻ ያቆመ አልነበረም። ለምሳሌ ሸብሃት ነጋ በኤርትራ ነፃነት ላይ የሚቃወም ካለ ከምንጠላው ሻቢያ ጋን ተሰልፈን እንዋጋለን ብሎ ነበር። ምን ማለት ነው እስከዚህ ድረስ ወሰን ያለፈ ተቈርቋሪነት?*[79] ሲሉም ጠይቀዋል

እንደሚታወቀው ሕወሓት ከጥንስሱ ጀምሮ ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ነች፣ ከነወደቦችዋ ነጻ መውጣት አለባት እያለ ለዚህም የደም ዋጋ የከፈለ ድርጅት መሆኑ ከዚህ በላይ ተገልፆአል። በጣም የሚገርመውና ግር የሚለው ግን፣ በቅርብ ጊዜ ከሕወሓት ጋር በመቀላቀል ኢሕአዴግን የፈጠሩ ድርጅቶች መሪዎች አሰብን አስመልክቶ የሕወሓትን አቋም ሲያስተጋቡ መስማት ነው። እነዚህ ሰዎች አሰብ የኤርትራ ግዛት ነች፣ኢትዮጵያ በአሰብ ላይ ምንም መብት የላትም ከሚል እውቀትና እምነት ተነስተው ወይንም በሌላ ሌላ ምክንያት ይሁን ይህንን ለህሊናቸው እንተወዋለን። የእነዚህ ከሕወሓት ጋር ተቀላቅለው ኢሕአዴግን የፈጠሩ መሪ ተብዮች አቋም ምን እንደሚመስል በአሁኑ ወቅት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የሆኑት አቶ ኃይለ ማርያም ደሳለኝ ከጥቂት ወራት በፊት የመንግስት ተጠሪ በነበሩበት ጊዜ <u>ለሪፖርተር ጋዜጣ</u> የተናገሩትን በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል። አቶ ኃይለ ማርያም ሲናገሩ "ኢትዮጵያ የባህር በር ቢኖራት አንጠላም። ተቃዋሚዎች

[79] <u>አውራምባ ታይምስ፣</u> ቅዳሜ ሚያዝያ 15/2003 ዓ.ም.



ኢትዮጵያ የባህር በር ባለቤት እናደርጋታለን የሚሉት የህዝብን ስሜት ለመግዛት እንጂ በተግባር የወደብ ባለቤት ለማድረግ አይደለም"[79] ብለዋል ። ተቃዋሚዎች በዚህ አቋማቸው ያላቸውን ማስረጃ አሰባስበው ወደ ሕግ ቢያመሩ መንግሥት ድጋፍ ስለመስጠቱ ሲጠየቁ "ኢሕአዲግ የሚሰጠው አንዳችም ድጋፍ የለም። በጉዳዩ ቢያምንበት ኖሮ ራሱ ኢሕአዲግ ይሄድበት ነበር"[80] ብለዋል።

የአቶ ኃይለ ማርያም ደሳለኝ መልሶች ብዙ ሐቆችን የያዙ ናቸው። በመጀመሪያ ተቃዋሚ ኃይሎች ኢትዮጵያን የባህር በር ባለቤት እናደርጋታለን የሚሉት የህዝብን ስሜት ለመግዛት መሆኑን ሲገልፁ የባህር በር ባለቤትነት በሕዝብ ስሜት ትልቅ ቦታ እንዳለውና የህዝቡንም ስሜት ሲገዛ እንደሚችል ይቀበላሉ ማለት ነው። በመቀጠልም የአቶ ኃይለ ማርያም ደሳለኝ ገለጻ ኢትዮጵያ የባህር በር ባለቤት ሊያስደርጋት የሚችል ማስረጃ ወይንም መከራከሪያ ነጥብ የለም ሳይሆን "ኢሕአዲግ ስለማያምንበት" መሆኑን ይገልጻሉ። እዚህ ላይ እውነቱን ነው የተናገሩት። ኢሕአዲግ አሰብ የኢትዮጵያ የባህር በር መሆንዋ በታሪክና በሕግ የተደገፉ ምክንያቶች እንዳሉ ጠፍቶት ሳይሆን ስለማያምንበት ወይንም በሌላ ሌላ ምክንያት ነው። እነዚሁ ከሕወሓት ጋር ተቀላቅለው ኢሕአዴግን የፈጠሩ አንዳንድ አዳዲስ መጤዎች የሚያስተጋቡት አቋም በጣልያን ጊዜ የተገጠመ ስሞታን ያስታውሰናል። አንድ ገንዘብ የሚሰጠውና ጠላቶቹን የሚያጠቃለት አርኮ የተባለ ጣልያንን ተማምኖ ጎረቤቶቹን ይበድል የነበረ ኢትዮጵያዊ ነበር። በዚህ ኢትዮጵያዊ በደል የደረሰበት ሌላው ኢትዮጵያዊ እንዲህ ሲል እሮሮውን አሰማ።

[79] ሪፖርተር ፣የካቲት 24ቀን 2002 ዓ.ም.
[80] ዝኒ ከማሁ.

*አርኮም (Arco) ይሄድና ሶልዲም ያልቅና፤*

*ያስተዛዝበናል ይቺ ቀን ታልፍና፤*

ከጊዜ በኋላ ጣልያኑ አርኮም አገሩ ገባ፤ ሶልዲውም ጠፋ፤ግፈኛው ኢትዮጵያዊውም በሕብረተሰቡ ዘንድ ትዝብት አተረፈ። አንዳንድ የቀድሞ የሕዋሓት መሪዎች፥ ዛሬም በአባልነት ያሉት ቢሆኑም በፓርቲያቸው የተሳሳተ አቋም ኢትዮጵያ አገራቸውን ወደብ አልባ ማድረጋቸው እንደ ውስጥ እግር እሳት ይለበልባቸዋል። አሁንም ለይስሙላም ቢሆን አሰብ የኤርትራ ግዛት ነች በሚለው አቋማቸው የፀኑት እንኳን አንጀ ከተሳሳትኩ አይመልሰኝ ሆኖባቸው ነው እንጂ የስሕተታቸውን ግዙፍነት ይረዱታል። የኢትዮጵያ የባህር በር ማዘጋት ለኤርትራ ነፃነት ደማቸውን ያፈሰሱለት የሕወሓት የቀድሞ መሪዎች እንኳን የሚጸጸቱበት ጉዳይ እነዚህ ትናንት ከሕዋሃት ጋር ኢሕአዴግን የተቀላቀሉ አዳዲሶቹ አሰብ የኤርትራ አካል ነች እያሉ የሕዋሓትን ሕቋም ሲያስተጋቡ መስማት ግርም ይላል።

የኢትዮጵያ ብቸኛዋ የባህር በር ለሌላ አገር ማስረከብ ከፍተኛ ብሄራዊ ጥፋት መሆኑ እንኳን የበቁና የነቁ የሕዋሃት መሪዎች ቀርቶ ቅንጣት ያህል የአገር ፍቅር ያለው የገጠሩ ገበሬ ሊስተው አይችልም።

በዚህ ጉዳይ እንኳን ኢትዮጵያውያን ለኢትዮጵየ በጎ የሚያስቡ ሁሉ ያዝናሉ* ምናልባት ይህንን በመረዳት ይሆናል ሕወሓት የኢትዮጵያ ወደብ አልባ መሆን በሌላ ኃይል ሊያላክከው የፈለገው። ሕወሓት ከደሙ ንፁህ ነኝ ለማለት ይመስላል አቶ መለስ በአንድ ወቅት "አሰብ የኢትዮጵያ ወደብ ሆና የማገልገልዋ ጉዳይ

* ሶልዲ በጣልያን ጊዜ በኢትዮጵያ ውስጥ ይሠራበት የነበረ የጣልያን ገንዘብ ነበር።

* የኢትዮጵያና የኤርትራ ውዝግብ ለአልጀርስ ድምበር ኮሚሽን በቀረበ ጊዜ አሰብ ወደ ኢትዮጵያ እንዲካለል ኢትዮጵያ ብትጠይቅ ኖሮ ሁለት የአውሮጳ አምባሳደሮች አገራቸው የኢትዮጵያን ጥያቄ ይደግፉ እንደነበር ለዚህ ጸሐፊ አረጋግጠውለታል።



እንዲያበቃ ያደረገው የ30 ዓመት ትግል ነው። የ30 ዓመቱ ትግል ለአሰብ ጉዳይ መልስ ሰጥቶአል"[61] ሲሉ የተናገሩት።

ኢሕአዲግ የአልጀርስን ስምምነት በመቀበል፤ የሽግግር መንግሥት ኤርትራን ከነወደቦችዋ፡ እውቅና እንድታገኝ አደረገ። በድምበር ኮሚሽኑ ክርክር ጊዜ የአሰብን ወደ ኢትዮጵያ እንዲካለል ባለመከራከር፤ የአፋር ሕዝብ የራሱን ዕድል በራሱ የመወሰን መብት በመቃወም፤ የአሰብ እራስ ገዝ ከኤርትራ ጋር ደባልቆ እውቅና ሰጠ። በእነዚህና በመሰል ምክንያቶች ሁሉ ሕወሓት አሰብን ለኤርትራ መርቆ መስጠቱና ኢትዮጵያን ወደብ አልባ ማድረጉን ሊክድ አይችልም። ኃላፊነቱም ከጫንቃው አይወርድም።

ኢትዮጵያ የባህር በርዋ አሰብ እስካልተመለሰላት ድረስ ኢሕአዴግ ከየትኛውም በጉም ይሁን መጥፎ ሥራዎቹ የባህር በር ማዘጋቱ ከሁሉም በላይ ጉልቶ ይወጣል። አሰብ ለኢትዮጵያ እስካልተመለሰ ድረስ ዘመናት እልፈው ዘመናት ሲተኩ በጊዜው ኢሕአዴግ ማን ነበር ሲባል መልሱ መንገዶችን፤ ትምህርት ቤቶችን ወይንም ሐኪም ቤቶችን ያነጸው አይሆንም ። መልሱ የኢትዮጵያን የባህር በር ያዘጋው መንግሥት ነው የሚሆነው።

[61] መለስ ዜናው ፣ዝኒ፣ ከማሁ

## ምዕራፍ ፫

# 3. በሁለተኛው የዓለም ጦርነት አሸናፊ የነበሩት አራቱ አገራት፣ የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባዔ ፣ ጣልያንና ኢትዮጵያ ኤርትራን አስመልክቶ የደረሱባቸው ውሳኔዎች

አሰብ የኤርትራ አካል ሳትሆን ጣልያን ከኤርትራ ጋር ደባልቆ እስከ ፌዴሬሽኑ ስለገዛት በጣም ጥቂት ኢትዮጵያውያን አሰብና ኤርትራን መለየትና አሰብ የኢትዮጵያ ሉዐላዊ ግዛት መሆንዋን መቀበል ይቸግራቸዋል። የዚህ ምዕራፍ ዓላማ አሰብ የኢትዮጵያ ሉዐላዊ ግዛት መሆንዋን በተጨባጭ ሕጐች፣ ማስረጃዎችና በተባበሩት መንግሥታት ውሳኔዎች ላይ በመመርኮዝ ለማስረዳት ነው። በታሪክ፣ አሰብ ማለት ጠቅላላው የአፋር አውራጃ የኢትዮጵያ አካል እንደነበርች አጼ ምኒልክ ግዛታቸውን ለዓለም ያስታወቁበት ደብደቤና ሌሎችም መረጃዎችም እያሉ አሰብ አለ ኢትያጵያ መንግሥት እውቀት ለጣልያን ኩባንያ እንደተሸጠችና ቆይቶም በጣልያን መንግሥት መጠቃለሏ ከላይ ተገልጾአል።

ከዚህ በታች ደግሞ ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኂላ አሰብ በተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባዔ የኤርትራ ባለ አደራ በነበሩት በአራቱ ኃያላን አገራት፣ በተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባዔና በኤርትራ ፓርላማ ውሳኔ እንዴት ወደ ኢትዮጵያ እንደተመለሰች እንተነትናለን።

ጣልያን በጦርነቱ በተሸነፈች ማግሥት በአፍሪቃ የቀድሞ የጣልያን ቅኝ ግዛቶች ጉዳይ የተረከቡት አራቱ ኃያላን አገራት (ፈረንሳይ፣ እንግሊዝ፣ አሜሪካና የሶቭየት ሕብረት) የውጭ ጉዳይ ምክትል ሚኒስትሮች፣ የጣልያን ተወካይ፣ በጊዜው የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የነበሩት ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም በግፍ የገደላቸው ጸሐፊ ትዕዛዝ አክሊሉ ሀብተወልድ፣ እ.አ.አ በ10 ፌብርዋሪ , 1947 ዓ.ም የሰላም

ስምምነት በፓሪስ ከተማ ፈርመው ነበር። በዚህም ውል መሠረት ጣልያን በአፍሪቃ ቅኝ ግዛቶችዋ የነበራትን ማንኛውም መብትና በቅኝ ገዢነትዋ ጊዜ የተፈራረመቻቸው ውሎችንም ጨምሮ ተሰረዙ።

የአራቱ ኃያላን አገራት ምክትል የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች ለእነዚሁ አገራት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች የቀድሞዋ የጣልያን ቅኝ ግዛት መጻኢ እድል ምን መሆን እንዳለበት የውሳኔ ሐሳብ እንዲያቀርቡ ታዘዙ። በዚሁ መሠረት የፈረንሳይ ተወካይ በአቀረቡት የውሳኔ ሃሳብ በዙላ ገልፍና በፈረንሳይ ሱማሌላንድ ያለው የባህር ዳርቻ(አሰብን ማለት ነው) ከሙሉ ሉዐላዊነት ጋር ለኢትዮጵያ እንዲሰጥ ሲያሳስብ የአሜሪካ ተወካይ ደግሞ የደንከልን ጠረፍ፤አክለጉዛይና፤ሠራኤን፤ወደ ኢትዮጵያ እንዲጠቃለሉ፤እንግሊ በበኩልዋ የደንከል አረጅም የባህር ጠረፍ አሰብን ጨምሮ ወደ ኢትዮጵያ እንዲካለልና የአፋር ሕዝብ አንድነት እንዲጠበቅ ሃሳብ አቀረቡ[83]። እዚህ ላይ እንግዲህ የኤርትራ ጉዳይ ባለቤቶች የነበሩት አራቱ ኃያላን አገራት የኤርትራ የወደፊት እጣ ምንም ይሁን ምን የኢትዮጵያን የባህር በር መብት አረጋግጠዋል[84]።

የእነዚህም የአራቱ ኃያላን አገራት አቋም የዓለም አቀፍ ሕግ አካል ሆነ። ይህ የኢትዮጵያ የባህር በር መብት ዕውቅና እንዳለ ሆኖ አራቱ ኃያላን አገራት የኤርትራን የወደፊት ዕጣ ፈንታን አስመልክቶ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ውሳኔ ካልሰጡ የኤርትራ ጉዳይ ወደ የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባዔ እንዲመራ ተስማሙ።

በዚህም መሠረት የተባበሩት መንግሥት ጠቅላላ ጉባዔ የመጀመሪያው ኮሚቴ (First Committee) እ.ኤ.አ. በ13 ሜይ 1949 ዓ.ም. በ34 የድጋፍ በ16 የተቃውሞና በ 7 ድምጸ ተአቅቦ የምዕራቡ ኤርትራ ከሱዳን ጋር እንዲቀላቀል የተቀረው ኤርትራ

---

[83] Report of the United Nations Commission For Eritrea, General Assembly, Official Records: Fifth Session Supplement No. 8 (A/1285).

[84] Belai Abbai, The Ethiopian Regime Cedes National Territories. Washington D.C (2001).



በሙሉ ወደ ኢትዮጵያ እንዲታጠፍ የሚለው የኮሚቴው አሳብ በጠቅላላው ጉባዔ በሁለት ሶስተኛ ድምጽ ስላልተደገፈ የውሳኔው ሃሳብ ውድቅ ሆኖ፣ ለኤርትራ ጉዳይ የመፍትሔ ሃሳብ እንዲሹ በጠቅላላው ጉባዔ የውሳኔ ቁጥር 289 A (IV) በርማ፣ ጓታማላ፣ ኖርዌይ፣ ፖኪስታንና ደቡብ አፍሪቃን የያዘ አንድ ኮሚሽን ተቋቋመ። ይህም ኮሚሽን በተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባዔ የሚከተለውን ቀጥሎ ያለው መመርያ ተሰጠው።

1. የኤርትራ ሕዝብ የተለያዩ የኃይማኖቶችና የሕዝባዊ ማህበራትና የጎሣ አባላትንም ፍላጎት ተገንዝቦ እንደሁም የኤርትራ ሕዝብ ራሱን ለማስተዳደር ያለውን አቅም አገናዝቦ፤
2. የምሥራቅ አፍሪቃን ሰላምና ደህንነት ከስሌት ውስጥ አስገብቶ፤
3. ኢትዮጵያ በጂኦግራፊ፣ በታሪክ፣ በዘር፣ በኢኮኖሚ ተመስርታ የምታነሳው በተለይም የኢትዮጵያ ተገቢና ሕጋዊ የባህር በር ባለቤትነት ጥያቄ አዎንታዊ መልስ እንዲያገኝ፤ ኮሚሽኑ ለተባበሩት መንግሥታት ጠቅለላ ጉባዔ የውሳኔ ሐሳብ እንዲያቀርብ ታዘዘ።

ለሥራዉ ክንውን እንዲረዳ የተለያዩ ኮሚቴዎች ተቋቁመው የተባበሩት መንግሥታት ሰንደቅ ዓላማ እ.አ.አ በጀንዋሪ 10 ቀን 1950 በአሥመራ ተተከለ። ኮሚሽኑ አርባ ሕዝባዊና ሰላሳ ምሥጢራዊ፤ በጠቅላላው ሰባ ስብሰባዎችን አካሄደ። ኮሚሽኑ እ.አ.አ ከፌብርዋሪ 29 ቀን 1950 ዓ.ም እስከ ማርች መጨረሻ ባለው ጊዜ ውስጥ በኤርትራ ግለሰቦችም ሆኑ ቡድኖች ፣ ማናቸውም የሕዝብ ተወካዮች አሳባቸውን ለኮሚሽኑ እንዲያቀርቡ ተጋበዙ።

ኮሚሽኑ የተለያዩ የፖለቲካ ፖርቲዎች ወኪሎችን፣ የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያንና የሙስሊም ምዕመናን ተወካዮችን፣ የንግዱ ማህበረሰብን መሪዎችን ተቀብሎ አነጋገረ። የኤርትራ የተለያዩ ክፍሎችና ኢትዮጵያን ጎብኝቶ ሃሳቦችን አሰባሰበ። እ.አ.አ በኤፕሪል 10 ቀን 1950 ዓ.ም የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የአቶ አክሊሉ ሃብተ ወልድ ንግግሮችን ካአዳመጠ በኋላ ኮሚሽኑ ግብጽንና ጣልያንን ጎብኝቶ ሪፖርቱን አዘጋጀ።

በዚህ መሠረት የበርማው፣የኖርይና የደቡብ አፍሪቃ ተወካዮች የኤርትራን አጠቃላይ ሁኔታ አጥንተው የውሳኔ ሃሳብ አቀረቡ፡፡ በዚሁ የውሳኔ ሃሳባቸው "ኤርትራ በጣም ጥቂት የተፈጥሮ ሃብት እንዳላት፣ በአጭር ጊዜ እይታ ኢኮኖሚዋ በጣም ደካማና በአብዛኛው በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ላይ የተንጠለጠለ (dependent) እንደሆነ አመለከቱ፡፡ የፖለቲካውን ሁኔታ ሲመረምሩ በጊዜው ከነበሩት ፓርቲዎች ሁሉ የአንድነት ፓርቲ (Unionist Party) ትልቁ መሆኑንና ይህ ፓርቲ ከደጋፊው ሙስሊም ፓርቲ ጭምር ከኢትዮጵያ ጋር ውህደት እንደሚፈልጉ ገለጹ፡፡ ስለሆነም አብዛኛው የኤርትራ ሕዝብ ከኢትዮጵያ ጋር መቀላቀል እንደሚፈልግ ይኸው ቡድን አረጋግጠናል አለ[85]፡፡

የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥትም መላው ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር እንድትቀላቀል ፍላጎቱ የጸና ቢሆንም የኤርትራ ምዕራብ ጠቅላይ ግዛቶች ከዚህ የተለየ ፍላጎት ካላቸው ይህንኑ በመቀበል ለምዕራቡ ክፍል የሚሰጠው ልዩ መፍትሔ እንደሚያከብር ለኮሚሽኑ አረጋገጠ፡፡ የፈረንሳይ መንግሥት ተወካይ አስተያየታቸውን ሲሰጡ ለኤርትራ መፍትሔ የኢትዮጵያና የጣልያን ትብብር አስፈላጊ መሆኑን ከገለጹ በኋላ ጣልያን ደግሞ ከዚህ ቀደም እንደጠየቀችው አሁንም ኤርትራን በአደራ እንድታስተዳድር የምትጠይቀውን ለቅቃ በኤርትራ ለሚገኙ ጣልያኖችና ልጆቻቸው ጥበቃ ብቻ እንዲደረግላቸው አስገነዘበች፡፡ እንግሊዝም ቀደም ሲል ሲያራምደው የነበረው የቀይ ባህር አውራጃ ምጽዋንም ጨምሮ አከለጉዛይ፣ ሠራዬና፣ ሃማሴን ወደ ኢትዮጵያ ተጠቃልለው በኤርትራ ለሚኖሩ ጣልያኖች ልዩ ጥበቃ እንዲደረግላቸው አሳሰበ፡፡ በመቀጠልም ቡድኑ ኤርትራ ለብቻዋ እንደ አገር ሆና ብትቆም የምሥራቅ አፍሪቃ ሰላምና ደህንነት አደገኛ ሁኔታዎች ውስጥ ይወድቃል ሲል ገለጸ፡፡ ስለሆነም የአብዛኛው የኤርትራ ሕዝብ ፍላጎት ያንጸባርቃል በሚል ኖርዌይ ኤርትራ ሙሉ በሙሉ ከኢትዮጵያ ጋር እንድትዋሃድ አቋም ስትይዝ፣ በርማና ደቡብ አፍሪቃ ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር

[85] Report of the United Nations Commission For Eritrea, General Assembly Official Records, supra note 83.



በፌዴሬሽን እንድትተሳሰር የሚል አቋም ለጠቅላላው ጉባዔ አቀረቡ[86]፡፡

ሌሎቹ ሁለቱ የኮሚሽኑ አባላት ጉዋታማላና ፖኪስታን ኤርትራ ለአሥር ዓመታት በተባበሩት መንግሥታት ከተዳደረች በኋላ ነፃነትዋን እንድትጐናጸፍ የሚል የውሳኔ ሃሳብ ለተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባዔ አቀረቡ፡፡ ይህ አምስት አባላት የያዘው ኮሚሽን በተሰጠው መመርያ መሠረት ስምምነት ስላልደረሰ በተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባዔ በውሳኔ ቁጥር 390 (V) ኤርትራ በኢትዮጵያ ዘውድ ስር በፌዴሬሽን እንድትቀላቀለ ተወሰነ፡፡ በኢትዮጵያና በኤርትራ በ1952 ዓ.ም ፌዴሬሽን ተመሠረተ፡፡ ፌዴሬሽኑ በሆይሆይታ ሳይሆን በጥንቃቄና በትዕግሥት የተከናወነ ለመሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ስለሆነም የፌዴሬሽኑ መመሥረት ሕጋዊ አልነበረም ብሎ የሚያከራክር ምንም ነገር አልነበረም፡፡

ይኸ ሁሉ የኃያላን አገራትም ሆነ የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባዔ አካሄድ ሃቅና ሕግን የተከተለ አይደለም፡፡ ምክንያቱም በ1900 ዓ.ም "ውል" ኢትዮጵያና ጣልያን በተስማሙት መሠረት ጣልያን በማንኛውም ምክንያት ኤርትራን ብትለቅ ኤርትራ ወደ ሌላ መንግሥትም ሆነ ተቋም ሳትዛወር በቀጥታ ወደ ኢትዮጵያ እንድትታጠፍ ተደንግጉ ነበር፡፡ ስለሆነም ኤርትራ ወደ አራቱ ኃያላን አገራት ብሎም ወደ የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባዔ መመራት አይገባትም ነበር፡፡ ከመጀመሪያውኑ ኤርትራን ከጣልያን የተረከቡት አራቱ ኃያላን አገራት የኤርትራ የወደፊት እድል ምን መሆን ይገባዋል ከማለት ይልቅ ኤርትራን በቀጥታ ወደ ኢትዮጵያ መመለስ ይገባቸው ነበር፡፡ ይህም መሆን ይገባው የነበረው የቅኝ ግዛት ውል ስለሚደነግግ ብቻ ሳይሆን ከመነሻው ኤርትራ የጥንታዊ ኢትዮትጵያ አካልም ስለነበረችም ጭምር ነው፡፡

የተባበሩት መንግሥታት ቻርተር አንቀጽ 10 የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባዔ በቻርተሩ በተጠቀሱ በማንኛውም ጉዳዮች ላይ ተነጋግሮ ለአባላቱ ወይንም ለጸጥታው ምክር ቤት

[86] Ibid

ወይንም ለሁሉቱም የውሳኔ ሐሳብ ሊሰጥ ይችላል ይላል[87]:: የተባበሩት መንግሥታት የኤርትራን ጉዳይ በአጀንዳነት ይዞ የተወያየው ይህንኑ ሥልጣኑን ተገን በማድረግ ነው ማለት ይቻላል::

የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤ በውሳኔ ቁጥር 390 (V) የሰጣቸው የውሳኔ ሃሳቦች በኢትዮጵያ፣ በጣልያን፣ የኤርትራን ጉዳይ በተረከቡት በአራቱ ኃያላን አገራት ላይ አሳሪነት አለው ወይ የሚለው ጠሳኝነት ያለው ጥያቄ ነው:: የዚህ ጥያቄ መልስና ሌሎች ዓለም አቀፍ ሕግጋት የኢትዮጵያ የባህር በር መብትን ስለሚያረጋግጡ በዝርዝር ይታያሉ::

በመሠረቱ የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባዔ የሚያስተላልፋቸው ውሳኔዎች አንዳንድ ሁኔታዎችን ካላሟሉ በስተቀር አሳሪ ሊሆኑ አይችሉም[88]:: ሆኖም ዓለም አቀፍ ድርጅቶች የተባበሩት መንግሥታትም ጭምር የተስማሙባቸውና የተቀበሉአቸው የውሳኔ አሳቦች አሳሪ ሊሆኑ ይችላሉ:: የዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት "በሬፓሬሽን" ጉዳይ እንዳተተው እነዚህ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች የፈጠሩአቸው አገራት የሚሰጥዋቸው ሥልጣን ይኖራቸዋል:: ይህ ሥልጣናቸው ከተቋቋሙባቸው መመሥረቻ ጽሁፎች ወይንም ከድርጅቶቹ ባህርያት ሊመነጭ ይችላሉ[89]:: እነዚህ ጉዳያቸውን ወደ ጠቅላላ ጉባዔ የሚያቀርቡ አገራትም ሆኑ ድርጅቶች ጠቅላላ ጉባዔው የሚሰጠው ውሳኔ አሳሪ እንዲሆን ተስማምተው ነው:: የእነዚህ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ሥልጣንን አስመልክቶ "በሬፓሬሽን" ጉዳይ ዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት የሚከተለውን ብሎአል:: "በዓለም አቀፍ ሕግ መሠረት አንድ ድርጅት በግልጽ ባያስቀምጠውም የተቋቋመበትን ዓላማ ለማስፈጸም የሚያስችል ሥልጣን ይኖረዋል" በማለት ወስኖአል::

ስለሆነም የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባዔ የኤርትራ ጉዳይ ከአራቱ ኃያላን አገራት ተረክቦ ለኤርትራ ጉዳይ መፍትሔ ይህ ነው ብሎ ያቀረበው የፌዴሬሽን ውሳኔ ከሥልጣኑ በላይ ነበር ማለት አይቻልም:: ስለሆነም ኤርትራ በፌደሬሽን ከኢትዮጵያ ጋር

87 U.N.Charter Article 10

88 Malcolm Shaw. supra note 69 p. 1212.

89 Ibid



እንድትተሣሰር የተሰጠ ውሳኔ ተዋዋዮቹ፤ ኢትዮጵያ የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባዔ፣ ጣልያን፣ አራቱ ኃያላን አገራትን የሚያስር ውሳኔ ነው::

የተባበሩት መንግሥታት ያሳለፉቸው የውሳኔ ቁጥር 390 (V) አራቱን ኃያላን አገራትን ወክሎ በተባበሩት መንግሥታት፣ በጣልያንና በኢትዮጵያ መሃከል የተፈረሙ ውሎች (Treaties) ናቸው:: የዋናውን ውል የውሳኔ ቁጥር 390 (V) ይዘትን ስመድገም ያህል እንደሚከተለው ይነበባል:: "የኤርትራ ሕዝብ የተለያዩ ኃይማኖቶች ምዕመናንና የጐሣ አባላትን ፍላጐት አገናዝቦ ፤ እንዲሁም የኤርትራ ሕዝብ እራሱን ለማስተዳደር ያለው አቅም ፈትሾ፤ የምሥራቅ አፍሪቃን ሰላምና ደህንነት ከስሌት አስገብቶ፣ የኢትዮጵያ ከኤርትራ ጋር በጆኦግራፊ፣ በኢኮኖሚ፣ በዘር ያላትን ትስስር ተገንዝቦ፤ <u>በተለይም የኢትዮጵያ ተገቢና ሕጋዊ የባህር በር ጥያቄ አምንታዊ ምላሽ እንዲያገኝ</u> (ሰርዝ የተጨመረ) ጠቅላላው ጉባዔው ኤርትራን ከኢትዮጵያ ጋር በፌዴሬሽኑን ቀላቀለ:: በዚህም መሠረት የኤርትራ ሕዝብ ከኢትዮጵያ ጋር የነበረው የአንድነት ፍላጐት ተካትቶአል:: ኤርትራ እራስዋን የማስተዳደር አቅም እንደሌላትና በረሰዋ ብትቆም ለአፍሪቃ ሰላምና ደህንነትን ስጋት መሆንዋን አረጋግጦአል:: ከሁሉም በላይ (ውሉ "በተለይ" ይለዋል) የኢትዮጵያ የባህር በር መብት በምጽዋና በአሰብ አማካይነት ተረጋግጦአል:: በውሳኔው ተዋዋዮቹ ፌዴሬሽኑ ለመመሥረት አመዛኙና ዋናው ምክንያታቸው የኢትዮጵያ የባህር በር ባለቤት እንድትሆን ነው ቢባል ከእውነትነት የራቀ አይደለም:: እንደዚሁም ጀኔራል አበበ ተክለ ሃይማኖት ካህሣይም አራቱን ኃያላን አገራት ወክሉ የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባዔ ያሳለፈው የውሳኔ ሃሳብ ጣልያንና ኢትዮጵያ የተስማሙባቸው ውሎች አድርገው ይቁጥሩታል[90]:: በኢትዮጵያና በኤርትራ መሃከል የፌዴሬሽን ሥርዓት የመሠረቱት የውሳኔ ሃሳቦች የተባበሩት መንግሥታትም ሆነ ኢትዮጵያ ወይንም ኤርትራ ሊጥሱአቸው የማይችሉ የሕግ ሰብእና የተላበሱ ውሎች ወይንም በተዋዋዮቹ የሕግ የተመሠረቱ ሕጎች ናቸው::

90 Abebe T. Hamare Kabsay sup e.cote 3.

ይህ ጣልያን የሰላሙን ውል ፊርማ በኤርትራ ላይ የነበራትን መብት ስትለቅቅ አራቱ ኃያላን አገራት የጣልያን መብቶች ወራሾች ሆነው እነርሱንም ወክሎ የተባበሩት መንግሥታት ከኢትዮጵያ ጋር የተፈራረሙት የፌዴሬሽን የዘወትር ዓይነት ውል ባይሆንም አንድ ውል ሊኖረው የሚገባውን ሁሉ ያካትታል። በውሉም መሠረት የተባበሩት መንግሥቷት ጠቅላላ ጉባዔ ወኪል ኮሚሽነር በመመደብ ኢትዮጵያና ኤርትራ ተደራድረው የሚቀበሉት የፌዴራል ሕግ ተዘጋጅቶ፤ ይህም የፌዴራል አስተዳደር ሕግ በ1952 ዓ.ም ጸድቆ በሥራ ላይ ዋለ። እነዚህ ውሎች ከ1947 ዓ.ም ከተፈረመው የሰላሙ ውል ቃልና መንፈስ የመነጩ ስለሆነ እንደ ሰላሙ ውል በተዋዋዮቹ መሃከል ማለትም በአራቱም ኃያላን መንግሥታት እነዚህኑ በወከለው በተባበሩት መንግሥታት በጣልያንና በኢትዮጵያ መሃከል አስሪ መሆናቸውን አቶ ሞገስ ሰለሞንም ይስማማሉ[91]። ፌዴሬሽኑ የ1947 ዓ.ም የሰላሙ ውል የደነገገውን በሥራ ላይ አዋለ እንጂ የሰላሙን ውል ሆነ የተባበሩት መንግሥታት ውሳኔዎችን የሚያፈርሱ ወይንም የሚቃረኑ ግዴታዎችን በተዋዋዮቹ ላይ አልጫነም።

የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔ አሳሪ ሆኖ አባላቱ ለውሳኔው ተገዢ ሲሆኑ ይህ የመጀመሪያው አይደለም። በዓለም ብዙ ተመሳሳይ ሁኔታዎች ተከናውነዋል። ከሊግ ኦቭ ኔሽን ጊዜ ጀምሮ ሁለት አገራት የሊጉ ካውንስል የውሳኔ ሃሳቦች ተቀብለው አሳሪ ግዴታዎች ያደረጉባቸው አያሌ ጊዜአት አሉ። በእንዲህ ዓይነት ውሳኔዎች ድንበር የተካለሉ አገሮች ድንበራቸው የመጨረሻ ሆነዋል ሲሉ አቶ ሞገስ ሰለሞን በጽሁፋቸው አስረድተዋል[92]። የኤርትራና የኢትዮጵያ ሕጋዊ ግንኙነት በተባበሩት የተመሠረተው አሁንም ሕጉ የሚያውቀው ግንኙነት በተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባዔ 390 (V) የተደነገገው ቀጥሎም እ.አ.አ በ1962 ዓ.ም የኤርትራ ፓርላማ ሁለቱን አገራት

[91] Moges Solomon. "Outlet to the Sea and Ethiopia's claim over the Port of Assab". Thesis, Faculty of Law, Addis Ababa University. (Unpublished (May 2000).
[92] Ibid



ያዋሃደበት ውሳኔ ነው። የኤርትራ መገንጠል ይህንን ሕጋዊ ሐቅ ሊሽረው አይችልም።

ምናልባትም ካሴሴ (Cassese) እንዳለው የተባበሩት መንግሥታት አባል አገራት የተለያዩ የፖለቲካ ስትራተጂና ጥቅሞች ከዕውነተኛው የኤርትራ ሕዝብ ስሜት በላይ ሆኖ የነጻነት ጥያቄውን አደብዝዞት ሊሆን ይችላል[93]።ሆኖም አረረም መረረም ይህ የፌዴሬሽን ትስስር አሴ ሊባል ውይንም በተዋዋዮቹ ወይንም መሃከል አሳሪ አልነበርም ለማለት አይቻልም።

የኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር በፌዴሬሽን መተሳሰር በተነሳ ቁጥር ኤርትራውያን በፌዴሬሽን ውይይት ወቅት የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዝነኛው ሚስተር ጆን ፎስተር ያሉትን ይጠቅሳሉ።የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ያሉትን በየአጋጣሚው ኤርትራውያን የሚጠቅሱት ከዚህ በታች የተጻፈውን ነው ። "ከፍትሕ አንጻር ስናየው የኤርትራ ሕዝብ ነጻነቱን መጐናጸፍ ይገባው ነበር። አሜሪካ በቀይ ባህር ሰላጤ ላይ ያላት ስትራቴጂክ ጥቅሞችና የዓለም ሰላምን ከግንዛቤ ስናስገባ ኤርትራ ከደጋፊአችን ከኢትዮጵያ ጋር መተሳሰር አለባት"[94]ብለው ነበር። ይህ የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የአሁኑ አባባል ቀደም ሲል የደንከል የባህር ጠረፍ (አሰብ) ወደ ኢትዮጵያ መካለል አለበት ከሚለው ጋር የሚጣረስ አይደለም። ኤርትራ በጊዜው የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔም ሆነ በአራቱ ኃያላን አገራት ውሳኔ ሙሉ ነፃነትዋን ብትጐናጸፍ ኖሮ ቢያንስ አሰብን ወደ ኢትዮጵያ ያካልሉ እንደነበር ምንም አያጠራጥርም። ይህንን አሰብን ወደ ኢትዮጵያ ማጠፍ የኤርትራ ነፃነትን ይደግፉ የነበሩት እንደ ፖኪስታን ያሉ አገራት እንኳን የሚቀበሉት ጉዳይ እንደነበረ ምንም ሊካድ አይቻልም። በተባበሩት መንግሥታት

[93] Antonio, Cassese "Self Determination of Peoples: A Legal Reappraisal," University Press,1955 p.222 cited in Moges Solomon, supra note 89.
[94] Quoted in a speech by Eritrean Ambassador at the 275th meeting (Ministerial level) of the African Union. Peace and Security Council, Addis Ababa, 26th April 2011.

ልዩ ልዩ ኮሚቴዎችም ሆነ በጠቅላላው ጉባዔ በተደረጉ ውይይቶች አንድም ጊዜ አንድም አገር ኢትዮጵያ ወደብ አልባ መሆን አለባት ያለበት ጊዜ የለም። ዛሬም ቢሆን ከሻቢያን ከሕወሓት/ኢሕአዴግ በስተቀር ኢትዮጵያ ወደብ አልባ ትሁን ሲል የተደመጠ አገርም ሆነ መሪ የለም።

ይህንኑ የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ቀደም ሲል በ1947 ዓ.ም በአራቱ ኃያላን አገራት በውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች ስብሰባ የኤርትራ ምሥራቃዊ ክፍል ምጽዋንም ጨምሮ ወደ ኢትዮጵያ መታጠፍ አለበት ብለው ነበር። የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በንግግራቸው ኤርትራ ነፃ መሆን ይገባት ነበር ሲሉ የኢትዮጵያ የባህር በር መብት ተጠብቆ ለመሆኑ ግልጽ ነበር።

የኤርትራ ሕዝብ ፍላጎት ምን እንደሆነ ለማረጋገጥ የተሄደው ወደ የተለያዩ የሕዝብ ቡድኖች፣ የፓለቲካ ፓርቲዎች፣ የሠራተኛ ማህበራት፣ የሃይማኖት ተቋማት ወዘተ ሲሆን ከእነዚህ ቡድኖች አንዱም ከኢትዮጵያ ጋር በፌዴሬሽን እንተሳሰር ያለ የለም። የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባዔ በራሱ ተነሣሽነት በባለጉዳዮቹ ማለት በአራቱ ኃይላን አገራትና በኢትዮጵያ ላይ የጫነው ነገር ነው። ምናልባት እነዚህ ሕዝባዊ ቡድኖች ፌዴሬሽኑን ቢቃወሙም በጊዜው የሚያመጡት ለውጥ አይኖርም ነበር።

ፌዴሬሽኑ በኢትዮጵያም ጉርሮ የተሸናቀረ እንጂ ኢትዮጵያ ወድዳ የተቀበለችው ነገር አልነበረም። የኢትዮጵያን ተቃውሞ በመግለጽ ጸሐፊ ትዕዛዝ አክሊሉ ሃብተወልድ ቀጥሎ ያለውን ብለው ነበር።

*"ለብዙ ምዕት ዓመታት ነጻና ሉዐላዊ ሆና የኖረች አገር አንድ ሃያኛ ከማታህልና ነፃ ሆና ከማታውቅ አገር ጋር በፌደሬሽን ተቀላቅላ ሉዓላዊነቷ ጠፍቶ ከምድረ ገጽ ልትደመሰስ ፈቃደኛ አትሆንም። ኢትዮጵያ ዓለማቀፋዊ ልዕልናዋ ታሪኳና ሕልውናዋ እስካልተጠበቀ ፌደሬሽን የሚባል ነገር አይኖርም። የኤርትራ ችግርም አይፈታም። ኢጣልያን ያቀረበችው የከሰረ የነጻነት ፎርሙላ ሥራ ላይ ከዋለ ኢትዮጵያ ብሔራዊ ደህንነትዋን አደጋ ላይ እንደወደቀ ትቆጥረዋለች። ጣልያን በተባበሩት መንግሥታት ምንም የአስተዳዳሪነት አደራ ሳይሰጣት ተሸቀዳድማ ሉማሌላንድ መግባትዋ እንዳለ ሆና ኢትዮጵያ በድጋሚ ከኤርትራ በኩል*



*ለሚሰነዘርባት ጥቃት አጸፋውን ለመመለስ የማታደርገው ነገር አይኖርም"*[95] በማለት ቁርጠኝነታቸውን ገለጹ።

ስለሆነም የኢትዮጵያ መንግሥት ለውሀደቱ የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባዔ ሁለት ለስተኛ ድምጽ እንደማያገኝ ስለተረዳ ፌዴሬሽኑን የግድ ተቀበለ።

ኢትዮጵያ ፌደሬሽኑን ያለ ውዴታዋ ብትቀበልም እንዲፈርስ ወዲያውኑ ጥረት ማድረግ ጀመረች። ፕሮፌሰር ጆን ስፔንሰር፣ አሜሪካዊ የኢትዮጵያ መንግሥት የሕግ አማካሪ እንዳሉት ከሆነ የተባበሩት መንግሥታት ጊዜያዊ ኮሚቴ ስለፌዴሬሽኑ ውይይት በሚያደርግበት ወቅት ፌዴሬሽኑ ሙሉ በሙሉ የኢትዮጵያና የኤርትራ ፓርላመንት ሰርዘውት ውህደት ቢፈጥሩ ፌዴሬሽኑ እንዳይፈርስ የተባበሩት መንግሥታት ጣልቃ እንደማይገባ የኮሚቴው አባላት ለሚስተር ስፔንሰር እንደአረጋገጡላቸው ገልጸው ነበር[96]።

አሜሪካ ቃኘው ሻለቃ ቴሌኮሙኒኬሽን ጣቢያ ከአሥመራ ትንሽ ወጣ ብሎ ባለው አካባቢ አቋቁማ ስለነበር የፌደሬሽኑ መፍረስ እምብዛም አላስከፋትም ነበር። እንዲያውም የኢትዮጵያ መንግሥት ፌደሬሽኑ በተመሠረተ በሁለተኛው ዓመቱ ሲያፈርሰው ይፈልግ እንደነበረ ኢትዮጵያ ለእነዚህ መንግሥታት አስታውቃ ነበር ይላሉ ጆን ስፔንሰር[97]። ለማንኛውም የኢትዮጵያ መንግሥት ፌዴሬሽኑን በቀዘቀዘ ስሜት ሲቀበለው ለንጉሡ "ውህደት" ወይም "ፌዴሬሽን" ምንም ልዩነት እንደሌላቸው ተናግረው ነበር[98]።

በተቃራኒው ደግሞ ከላይ እንደተገለጸው በጊዜው የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የነበሩት ጸሐፊ ትዕዛዝ አክሊሉ ሃበተ ወልድ ፌዴሬሽኑ ይፍረስ ከተባለ በኤርትራ ሕዝበ-ውሣኔ (Refurendum) መሠረት መሆን እንደሚገባው አስገንዝበው

---

[95] ዘውዴ ረታ (አምባሳደር) <u>የኤርትራ ጉዳይ 1941-1963</u> ዓ.ም አዲስ አበባ ገጽ 416.
[96] John Spencer,<u>Ethiopia at Bay: A Personal Account of Halle Selassie</u> (1984) p 211.
97 Ibid
[98] Shumet Sishagne, Professer supra note p.43 P.175-176

ነበር። ፌዴሬሽኑ በመንግሥት ውሳኔ ይፍረስ ከተባለ ቀይቶ ችግር እንደሚፈጠር አሳስበው ነበር። ለማንኛውም ከ1952 ዓ.ም ጀምሮ ለ 10 ዓመታት በሞትም በሕይወትም መካከል ሲያጣጥር የነበረው ፌዴሬሽን እ.አ.አ ረቡዕ ሕዳር 15 ቀን 1962 ዓ.ም በከፍተኛ ስነ ሥርዓት በኤርትራ ፓርላማ ውሳኔ ግብአተ መሬቱ ተፈጸመ[99]።

ከዚያም ኤርትራ ውስጥ ምንም ዓይነት ነጻ የፓለቲካ እንቅስቃሴ ለመደምሰስ ከነበራቸው የንጉሡ ጉጉት ኳተቃዋሚ ፖርቲዎች ጀምሮ የውህደቱ ደጋፊዎችንም ጭምር አጠፉአቸው[100]። በዚህም ድርጊታቸው ዋነኛው የኢትዮ-ኤርትራ ውህደት አቀንቃኝ የነበረው "የአንድነት ፓርቲን" ሲዘጉ የውህደቱ ዋነኛ አንቀሳቃሽ የነበረውን ኃይል ናዱትዞ "የኤርትራ መንግሥት" የሚለው ቃል "የኤርትራ አስተዳደር" በሚለው ተቀየሮ ማንኛውም የኢትዮጵያ ሕጐች በኤርትራ ላይ ተጭነው በኤርትራ ፖርላማ ውሳኔ በሙሉ ድምጽ የኤርትራ ፖርላማ ራሱን አፍርሶ ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጠቅላይ ግዛቶች አንዷ ሆነች[101]።

ጆን ስፔንሰር የኤርትራ ፖርላማ ፌዴሬሽኑ ፈርሶ ውህደት እንዲመሠረት ፍላጐቱ መሆኑን ቢያውቁም አንዳንድ ኃያላን መንግሥታት ይቃወማሉ በማለት በእርሳቸው በኩል የፌዴሬሽኑ መፍረስ መቃወማቸውን ገልጸዋል[102]።

ፌዴሬሽኑ እንዲፈርስ በኤርትራ ፖርላማ የተሰጠው ድምጽ ነፃ አልነበረም አባላቱ ተገድደው ነው፤ የሚል ስሞታ ከኤርትራውያን ብዙ ጊዜ ተደምጦአል። ሆኖም የትኞቹ የፖርላማ አባላት ፖርላማውን እንዲያፈርሱ ተገድደው ድምጽ ሰጡ፤በምን መልኩ ነው የተገደዱት ለሚለው ሁሉ እስከ ዛሬ ታአማኒ የሆነ ማስረጃ አልቀረበም። ምናልባትም ፌዴሬሽኑ እንዲፈርስ ፍላጎት የነበራቸው የፓርላማ አባላት እንደማንኛውም አማራጭ ሃሳብ ወይንም የሚደግፉትን አቋም ተቀባይነት እንዲያገኝ ቅስቀሳ

[99] ዘውዴ ረታ (አምባስደር) ዝኒ ከማሁ ገጽ 502
[100] Shumet Sishagne, Professor, supra note p. 43, p.176
[101] ትዕዛዝ ቁ.27/1962 ነጋሪት ጋዜጣ 20ኛው ዓመት ቁ 27 አዲስ አበባ
[102] John Spencer, supra note 96, p.303



አድርገው ከሆነ ይህ በሕግ የተፈቀደና የትም የሚደረግ ነው። ሕጉ የማያውቀው ግን የኤርትራ ፖርላማ በዚያው በኤርትራ ፖርላማ አባላት ሙሉ ድምጽ ያለ አንዳች ተቃውሞ መፍረሱ ነው። እዚህ ላይ ምናልባት አንድ የሕግ ጥያቄ ሊነሳ ይችል ይሆናል።

የኤርትራ ፓርላማ ፌዴሬሽኑን አፍርሶ ኤርትራን ከኢትዮጳያ ጋር ለመቀላቀል ሥልጣን ነበረው ወይ የሚለው ነው። የፌዴሬሽኑ ሁኔታ በሙሉ የሚገዛው በፌዴራል ሕግ (Federal Act) ሲሆን በዚህ ሕግ ስለፌዴሬሽኑ መፍረስ የሚያትተው ነገር የለም።

እስከ ዛሬ ድረስ ስለ ኤርትራ በተደረሱ ጽሁፎች የኤርትራ ፓርላማ ፌዴሬሽኑን ለማፍረስ ሥልጣን አልነበረውም የሚል ክርክር ተሰምቶ አያውቅም። በእርግጥም ውህደቱ በሕዝብ ተቀባይነት እንዲኖረው ጸሐፊ ትዕዛዝ አክሊሉ እንዳአሳሰቡት በሕዝብ ውሳኔ ቢደረግ በተሻለ ነበር። ጸሐፊ ትዕዛዝ ስለዲፕሎማሲ የጠለቀ ዕውቀት የነበራቸው ሰው ስለነበሩ የተባበሩት መንግሥታት የመሠረተው ፌዴሬሽን በኤርትራ ፓርላማ ቢፈርስ በተባበሩት መንግሥታትና በዓለም አቀፍ ሕብረተሰብ ያስወቅሳል ከሚል ተነስተው ነው እንጂ ጸሐፊ ትዕዛዝ ውህደቱ ከመሠረተ ሃሳቡ ሳይወዱትና ሳይፈልጉት ቀርተው አይደለም። ጸሐፊ ትዕዛዝ አክሊሉ ሃብተ ወልድ ኤርትራን ከኢትዮጵያ ጋር ለማዋሃድና ኢትዮጵያ የባህር በር ባለቤት እንድትሆን ያደረጉት ትልቅ ትግል በደርግ ታስረው በነበረ ጊዜ ለመርማሪ ኮሚሽን እራሳቸው ከጻፉት ማስታወሻ መረዳት ይቻላል[103]።

ፌዴሬሽኑ የፈረሰው በኢትዮጵያ መንግሥት አስገዳጅነትና ጫና ነበር የሚሉ ብዙዎች ሲሆኑ በአንጻሩ ደግሞ በጊዜው እጅግ የተከበሩ ለኤርትራ ነፃነት ወይንም ከኢትዮጵያ ጋር እንድትዋሃድ ከፍተኛ ትግል ያደረጉ ግለሰቦች መኖራቸው መዘንጋት የለበትም። ከእነዚህም በዋናነት ሊጠቀሱ ከሚችሉት አንዱ የሕግ

[103] ጸሐፊ ትዕዛዝ አክሊሉ ሃብተወልድ የአክሊሉ ማስታወሻ፣ መስከረም 10 ቀን 1967 ዓ.ም. (ለመርማሪ ኮሚሽን ያቀረቡት ማስታወሻ፣)፥ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ፕሬስ (2002 ዓ.ም.)

አስፈጻሚው ክፍል የበላይ የነበሩት ደጃዝማች ተድላ ባህሩ ናቸው። እርሳቸውም "...... ያገሬ የመረብ ምላሽ ሕዝብ ከእናት አገሩ ከኢትዮጵያ ጋር በፌዴሬሽን ከማደር ይልቅ ፍጹም የሆነ ውሕደት እንዲደረግ በመርጥ ለደስታዬ ወሰን አልሰጠውም"[104] ብለው ነበር።

ደጃዝማች ተድላ ፌዴሬሽኑ ከፈረሰ በኋላ ብዙም ሳይቆዩ አቋማቸውን ቀይረው በኤርትራ የነጻነት ትግል ተሠማሩ። ልጃቸው አቶ ሕሩይ ተድላ ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ ከተመረቁ በኋላ የኤርትራን ትግል ተቀላቅለው ከጀብሃ መሪዎች አንዱ ሆነው ነበር። ኤርትራ ነፃ ከወጣች በኋላ ግን ከአቶ ከኢሣያስ ዋነኛ ተቃዋሚዎች አንዱ ሆነው የአቶ ኢሣያስ ተቃዋሚዎችን በማስተባበር ላይ ይገኛሉ። ለዚህም ጥረታቸው ከኢትዮጵያ መንግሥት ድጋፍ የሚያገኙ ሲሆን በተለያዩ ጊዜአት አዲስ አበባን ጎብኝተዋል።

ፌዴሬሽኑ እንዲፈርስና ሙሉ ውሕደት እንዲደረግ ከማንም በላይ የደከሙት ቢትወደድ አስፍሐ ወልደሚካኤል ከዚሁ ቢታች የተመለከተውን ተናግረዋል።

*"........የፌዴሬሽን አስተዳደር ስሙም ሆነ ግብሩ ከታሪካችንና ከባህላችን የራቀ ለጠላት መሣርያ ከመሆኑ በስተቀር ለሕዝባችን የማይጠቅም መሆኑን ተረድተነው፤ አንድ ኢትዮጵያዊ የሆነ ሕዝብ ሰው ሠራሽ በሆነ ባዕዳዊ ድርጅት መመራት እጅግ የሚጎዳው መሆኑን ተገንዝበን የሕዝባችንን ሀሳብና ምኞት ገላጮች ሆነን ይህን ፌዴሬሽን የተባለ አስተዳደር ከላያችን አንስተን ከዛሬው ዕለት ጀምሮ ከእናታችን ከኢትዮጵያ ጋር ተዋህደናል..."*[105]

ቢትወደድ አሥፍሐ እስከ እለተ ሞታቸው በአቋማቸው ጸንተው ለኢትዮጵያና ለኤርትራ አንድነት የደከሙ የኢትዮጵያና የኤርትራ ሕዝብ ባለውለታ ናቸው። የኢትዮ-ኤርትራ ፌዴሬሽን የተመሠረተው በዋናነት ኢትዮጵያ የባህር በር እንዲኖራት ታስቦ እንዲሁም የኤርትራ ሕዝብ ፍላጎት ለመተግበር እንደነበር ከላይ

[104] ዘውዴ ረታ (አምባሳደር) ዝኒ ከማሁ 95, ገጽ 417.
[105] ዘውዴ ረታ (አምባሳደር) ዝኒ ከማሁ 95, ገጽ 539.



ተገልፆአል። የፌዴሬሽን መፍረስ የአራቱ ኃያላን አገራትና የተባበሩት መንግስታት ጠቅላላ ጉባዔ ፌዴሬሽኑን ሲመሠርቱ እነዚህ ሁለት መሰረታዊ ዓላማዎችን አጠናክሩ እንጂ አልሻሯቸውም። ስለሆነም ፌዴሬሽኑን ያፈረሰው የኤርትራ ሕዝብን የሚወክለው አካል ከመሆኑም በላይ ፌዴሬሽኑ የተመሠረተባቸው መሠረታዊ ዓላማዎችን ስለማይጻረር መፍረሱ ሕገ ወጥ ነበር ማለት አይቻልም።

ለማጠቃለል ያህል የኢትዮጵያ የባህር በር መብት ብሎም አሰብ ቢያንስ በሁለት መንገድ ወደ ኢትዮጵያ ታጥፎአል፤ የኢትዮጵያ የባህር በር መብትም ተረጋግጦአል።

1. በጦርነቱ አሸናፊ የነበሩና ኤርትራን ከጣልያን ተረክበው የጉዳዩ ባለቤቶች የሆኑት የአሜሪካ፣ የእንግሊዝ፣ የፈረንሳይና ሶቭየት ሕብረት ተወካዮችና የተባበሩት መንግሥታት ጣልያንን ጨምሮ በ1947 ዓ.ም አሰብ ወደ ኢትዮጵያ መጠቃለል እንደሚገባው በውሳኔ ሃሳብ ደረጃ ተስማሙ።
2. አራቱ ኃያላን አገራትን ወክሉ የተባበሩት ምንግሥታች ጠቅላላ ጉባዔ በውሳኔ ቁጥር 390 (V) በተለይ በዋናነት ሕጋዊና ፍትሐዊ የኢትዮጵያን የባህር በር መብት ለማረጋገጥና የኤርትራ ሕዝብ ፍላጎት ገቢራዊ ለማድረግ ኤርትራና ኢትዮጵያ በፌዴሬሽን ተቀላቀሉ። ይህም ፌዴሬሽን ሊጣስ በማይችል የኤርትራን ባለአደራ በነበሩት በአራቱ ኃያላን አገራት ወኪሎች በተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባዔ፤ በኢትዮጵያና በጣልያን ሲፈረም ኢትዮጵያ የባህር ባለቤት ሆነች።

## ምዕራፍ 4

# 4. የኤርትራ በጦር ኃይል መገንጠል ኢ-ሕጋዊነትና በኢትዮጵያ የተሰጣት ዕውቅና

የራስን ዕድል በራስ መወሰን እስከ መገንጠል ያለው መብት በማያጠራጥር መልኩ በሕግ የተረጋገጠው ከሦስት ሁኔታዎች ቢያንስ አንዱ ሲኖር ነው። እነዚህም አንድ በቅኝ ግዛት ሥር የሚገኝ ሕብረተሰብ ራሱን ከቅኝ ግዛት መውጣትና ነፃ መንግሥት ማቋቋም መብቱ ሲሆን ይህንን ለማሳካት ኃይል መጠቀም ከመቻሉም በላይ ሌላውም የዓለም አቀፍ ሕብረተሰብ ድጋፍን እንዲሰጠው ዓለም አቀፍ ሕግ ይደነግጋል*።

ቀጥሎም አንድ ሕብረተሰብ በባዕድ ጦር ኃይል ተይዞ ከሆነ ይህንን ጦር ከአገሩ ለማባረርና ሉዐላዊነቱን ለመጐናጸፍ መብት አለው። በመጨረሻም ብዙ ዘሮች ባሉበት አገር አንዱን ዘር ከሌላው ሕዝብ እኩል ተሳትፎ ከተነፈገ ይህንንም በሰላማዊ መንገድ በውይይት ይህንን መብቱ ማስከበር ካልቻለ የመገንጠል መብት እንዳለው የዓለም አቀፍ ሕግ ይደነግጋል[106]። ሆኖም የራስን ዕድል በራስ መወሰን የሚባለው መርህ ነፃና ሉዐዓላዊ አገራትን ለመበታተን መጠቀም ስለማይቻል ከላይ በተጠቀሱት ሁኔታዎች ካልሆነ በቀር ዓለም አቀፍ ሕግም ሆነ የዓለም ሕብረተሰብ አንድ ሉዓላዊ አገር ተከፋፍሎ አንዱ ከሌላው በኃይል ተገንጥሎ የራሱን መንግሥት ማቋቋም አይደግፍም። ብሔሮች በዘፈቀደ ከአንድ ሉዓላዊ አገር እንዳሰኛቸው ቢገነጠሉ በዚህ ዓለም ስፍር ቁጥር የሌላቸው ጥቃቅን አገራት ከመፈጠራቸውም ባሻገ የዓለምን ሰላምና ጸጥታ ሊያናጋ የሚችል ሁኔታ ይፈጠራል በሚል የዓለም ሕብረተሰብ የአገራት የግዛት አንድነትን ይደግፋል።

* ሕወሓት ለሻቢያ ድጋፍ የሰጠውም ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ነች ከሚለው ተነስቶ ሲሆን ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት አልነበረችም እንጂ ቅኝ ግዛት ብትሆን ኖሮ ድጋፉ ትክክልና ሕጋዊ በሆነ ነበር።

[106] Antonio Cassese, supra note 93, p.62-63



ስለሆነም በሎሜ ቶጐ እ.አ.አ. በ2000 ዓ.ም የተደነገገው የአፍሪቃ ሕብረት መሠረታዊ ሕግ (Constitutive Act) አንቀጽ 3 ከአፍሪቃ መሠረታዊ ዓላማዎች አንዱ የአባል አገርን "ሉዐላዊነት፣ የግዛት አንድነትና ነፃነት ማረጋገጥ" መሆኑን ይገላጻል። እንዲሁም በአንቀጽ 4 የአፋሪቃ አገራት ነፃ ሲወጡ የነበራቸው ወሰን መከበር እንደለበት የድርጅቱ እምነት መሆኑን ያስገነዝባል። በአፋሪቃ ቢያፍራክ፣ናይጀርያ፣ካታንጋ፣ከኮንጐሪፑብሊክ፣ኤርትራ፣ከኢትዮያ ሣህራዊ አረብ ሬፑብሊክ ከምሮኮ፣አዲሲቱ ደቡብ ሱዳን ከሰሜን ሱዳን ለመገንጠል የተደረጉ እንቅስቃሴዎች ብዙ ደም ያፋሰሱ ስለሆነ የአፍሪቃ አገርት መገንጠልን አይደግፋም፣ እንዲያውም በአብዛኛው ይቃወሙታል። ስለሆነም በአፍራቃ ሕብረትም ሆነ በሌሎች ዓለም አቅፍ የሕግ መሠረታዊ ሰነዶች ወይንም የሰብአዊ መብት ጥበቃ ድንጋጌዎች በአንዱም ከአንድ ነፃና ሉዐላዊት አገር የመገንጠል መብት እውቅና የተሰጠበት ቦታ የለም።

በአንድ አገር መንግሥቱ በግዛቱ የሚገኘውን መላውን ሕዝብ ሳያበላልጥ በእኩልነት ከአስተዳደረ የሕዝቡ የራሱን ዕድል በራሱ የመወሰን መብቱ እስከተከበረለት ድረስ የአገሪቱ የግዛት አንድነት እንዲከበር ሕጉ ጥበቃ ያደርግለታል[107]። ይህንን በማጠናከር የዓለም ሕግ የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት ሲያረጋግጥ በዚህ መብት መጠቀም የሚቻለው በሉዐላዊ አገር ማቀፍ ውስጥ ሆኖ የአገሪቱ የግዛት አንድነት ተጠብቆ መሆን እንዳለበት ያረጋግጣል[108]። እንዲሁም ኢ.አ.አ በ1970 ዓ.ም "የወዳጅነት ግንኙነት" መርሆችን የደነገገው መግለጫ (1970 Declaration on Principles of International Law Concerning Relations between States)የራስን ዕድል በራስ መወሰን ማለት ነፃናሉዓላዊ አገራት እንዲገነጣጠሉ መፍቀድ ወይንም ማደፋፈርናና የግዛት አንድነታቸውን ማናጋት ማለት አይደለም ይላል[109]።

[107]Supreme Court of Canada in Reference to Secession of Quebec, cited in Antonio Cassese, supra note p.93, P.68

[108] Canadian Supreme Court "The case of Quebec " Cited by Medhane Tadele"The Scope of powers of the Security Counicil to decide on Imumities and. Previleges of Head of States/Governments with Special Emphasis on Sudan" LLM Thesis ,Faculty of Law,Addis Ababa universisity june 2011

[109] Malcolm Shaw, supra note 69, P.140

የኤርትራ ሕዝብ እንደ ኢትዮጵያ ሕዝብ ሁሉ በመሠረቱ አንድ ቋንቋ የሚናገር አንድ ኃይማኖት የሚከተል አንድ ወጥ ዘር አይደለም። በኤርትራ በአብዛኛው ሕዝቡ ክርስቲያንና ሙስሊም ሲሆን ከዘጠኝ የማያንሱ ቋንቋዎች ይነገራሉ እነዚህም ትግርኛ ትግረ፣አረብኛ፣አፋር፣ሳሆ፣ቢለን፣ቤጃ፣ ባርያናኩናማ ናቸው። እነዚህ ቋንቋ ተናጋሪዎች በተለያዩ የኢኮኖሚ ደረጃ የሚገኙ ሲሆኑ እያንዳንዳቸው በራሳቸው የቆሙ መሆናቸውና እራሳቸውን እንደ አንድ ሕዝብ ይቆጥራሉ። ስለዚህ እነዚህ ሕዝቦች እያንዳንዳቸው እንደ አንድ ሕዝብ ተቆጥረው የመገንጠል ጥያቄ ቢያነሱ ጥያቄው የኤርትራ ሉዐላዊነት ለሚገረስስ የዓለም አቀፍ ሕግ ድጋፍ ሊኖረው አይችልም።

ኤርትራውያን ከኢትዮጵያ ጋር በነበሩበት ጊዜ በተለያዩ ከተሞች ተሰማርተው የንግድ ሥራ ሲያካሄዱ በቢሮክራሲውም ገብተው ከፍተኛ ደረጃ ደርሰው ነበር። በአጼ ኃይለ ሥላሴ አስተዳደር ዘመን ከማንም ኢትዮጵያዊ በእኩልነት ከመታየታቸውም በላይ እንዲያውም የኤርትራውያኑን ልብ ለማግለል ሲባል የኤርትራ ሕዝብ ከሌላው ጠቅላይ ግዛት ሕዝብ በተሻለ ተጠቃሚ ነበር የሚሉም አሉ። ያም ሆነ ይህ በአጼ ኃይለ ሥላሴ የአስተዳደር ዘመን ኤርትራውያን ተለይተው ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚአዊም ሆነ ሰብአዊ በደልና ጥቃት አልተፈጸመባቸውም። በነበረው ነባራዊ ሁኔታ ኤርትራውያን ከኢትዮጵያውያን እኩል የሕግ ጥበቃና ከለላ አልተነፈጉም።

በ1960ዎቹ አካባቢ ኤርትራውያን በክልላቸው ሆነ በመላው ኢትዮጵያ በተለይም በአዲስ አበባ በኢኮኖሚ ከየትኛውም ብሔረሰብ አባል በተሻለ የኑሮ ደረጃ ላይ ይገኙ ነበር ማለት ይቻላል። ስለዚህ ኤርትራውያን ኢትዮጵያውያን ዜጎች በነበሩ ጊዜ ከሌላው ኢትዮጵያዊን በእኩልነት ኖረዋል። በመሆኑም የመገንጠል ጥያቄአቸው በሕግ ፊት ተቀባይነት የለውም። በኤርትራዊነታቸው ተለይተው ሰብአዊም ሆነ ፖለቲካዊ መብቶቻቸው አልተነፈጉም ነበር። እንዴ ሌላው ኢትዮጵያዊ ሁሉ የፊውዳል ሥርዓት ያመጣው ጉዳትም ሆነ ጥቅም ገፈት ቀማሾች ነበሩ። ስለሆነም እንደማንም ኢትዮጵያዊ ሥርዓቱን ለመለወጥ በሰላማዊ መንገድ



መታገል እንጂ ሁኔታው የመገንጠል መብት አያጎናጽፋቸውም ነበር።

በደርግ የአገዛዝ ዘመን በኤርትራ የእርስ በርስ ጦርነት ይካሄድ ስለነበር ብዙ ኤርትራውያን ለጦርነቱና ለኤርትራ መገንጠል ድጋፍ ይሰጣሉ በሚል በመሃል አገርም ሆነ በኤርትራ የሚኖሩ ኤርትራውያን ላይ ይደርስ የነበረው የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ከሌሎች ኢትዮጵያውያን በላይ የከፋ ነበር ማለት ይቻላል። ሆኖም ግን ኤርትራውያንን በኤርትራዊነታቸው ብቻ ከሌላው ኢትዮጵያዊ የተለያ ጥቃት እንዲፈጸምባቸው የተወጠነ ዓላማ ነበር የሚል የለም።

እጅግ አሳዛኝ በሆኑ ጦርነቶች ከአጼ ኃይለ ሥላሴ መንግስት ጀምሮ በኤርትራም በኢትዮጵያም በኩል ብዙ ሰው አልቆአል። በእነዚህ ጊዜያት ውስጥ የጦርነቶቹ ዓላማ መገንጠሉን ለማክሸፍ እንጂ ኤርትራውያንን ከምድረ ገፅ ለማጥፋት እንዳልነበር ማንም ሊክደው የሚችል አይደለም። ደርግ አንድ የማይታማበት ነገር ቢኖር ዘርን ወይንም ኃይማኖትን ለይቶ ሰዎችን አልገደለም። ይህም ማለት ደርግ ለሁሉም እኩልና ተመሳሳይ ዕድል የሰጠ ገዳይ ወይንም ፈረንጆች እንደሚሉት (Equal Opportunity Killer) ነበር።

ኤርትራውያን የትጥቅ ትግል ያደረጉትና ኤርትራን ለመገንጠል ዋናው ምክንያት ነው ያሉት በ1952 ዓ.ም. ተመሠርቶ የነበረው ፌዴሬሽን ያላግባብ ተሰርዞ፣ የራሳችንን ዕድል በራሳችን መወሰን አልቻልንም ከሚል ተነስተው ሲሆን ጥያቄዎቻቸው በሰላማዊ መንገድና በድርድር መፍታት ሲችሉ እነዚህ መብቶቻቸውን እውን ለማድረግ የግድ ጦር መምዘዝ አስፈላጊ አልነበረም።

በተለያዩ ወቅቶችም ድርድሮች ተጀምረው አንድ ጊዜ የደርግ መንግሥት በሌላ ጊዜ ደግሞ የኤርትራ ግምባሮች ድርድሮቹን ሲያጨናግፉ ቆይተዋል። እነዚህ ውይይቶችና ድርድሮች ማድረግ በራሳቸው ውዝግቡን በሰላማዊ መንገድ መፍታት ይቻል እንደነበርና መፍትሔው የግድ መገንጠል እንዳልነበረ ያሳያሉ።

ለድርድሮቹ መክሸፍ በደርግና በሻቢያ መሪዎች መሃከል በጐ ፈቃድ መጥፋት እንጂ በመሃከላቸው የነበሩ ቅራኔዎች በድርድርና ሰጥቶ በመቀበል ሊፈቱ የማይችሉ ስለነበሩ አይደለም።

ከመገንጠል በመለስ የኤርትራ ውዝግብ ከመቼውም ይበልጥ ለሁለቱም ወገኖች አጥጋቢ የሆነ መፍትሔ ሊገኝ ይቻል የነበረው ሻቢያና ሕወሓት ሥልጣን በጨበጡበት በ1983 ዓ.ም. ነበር። እነዚህ ሁለት ድርጅቶች ለብዙ ዓመታት ደርግን ተፋልመው ለቆሙለት ዓላማ ብዙ ዋጋ ከፍለው ሊጥሉት ችለው ነበረ በዚያን ጊዜ ይኸ የኢትዮጵያ የኤርትራ ግንኙነት የቅኝ ገዢና ተገዢ ነው የሚለውን የጨቅላ አስተሳሰበ ትተው አለአግባብ ፈረሰ ወዳሉት ወደ ፌዴሬሽኑ በመመለሰ ሕጋዊነትን ሊይዙ በቻሉ ነበር። ሕወሓት ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ነች በሚል መሠረተ ቢስ ዕርዮተ ዓለም እራሱን ቀፍድዶ አስሮ ስለነበር ፊዴሬሽን የሚል ሃሳብ ከናካቴው አልመጣላትም ይሆናል። ምክንያቱም የአንድ ቅኝ ገዢና ተገዢ ትስስር ሊበጠስ የሚችለው ቅኝ ተገዢ ተብየው ነፃ ሲወጣ ብቻ ነው። ኢሕአዴግ እስከ ዛሬ ለኤርትራ መሪዎች የፌዴሬሽን ወይንም የኮንፌዴሬሽን ሃሳብ አቅርቦላቸው ነበር የሚል ሃሜት ተሰምቶበትም አያውቅም። እንዲያውም እንዲህ ዓይነቱ ትስስር ሕወሓት ይቃወም እንደነበር አንዳንድ ሰዎች ይመሰክራሉ። ስለዚህ የኢትዮጵያ የኤርትራ ውዝግብ በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት ዕድሉ ሰፊ ስለነበር በኃይል መገንጠሉ የዓለም አቀፍ ሕግ ጥሰት ያደርገዋል[110]።

የኤርትራውያን መገንጠል ከሁሉም በላይ ሕገ ወጥ የሚያደርገው የተባበሩት መንግሥታት የጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔ ቁ. 390 አንቀጽ (V) መጣሱ ነው። የዚህ ውሳኔ ዋናው ሐረግ "ኤርትራ በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ዘውድ ሥር እራስዋን የቻለች (autonomous) ሆና ከኢትዮጵያ ጋር በፌዴሬሽን ትዋሃዳለች" የሚለው ነበር።

ይህ የፌዴሬሽን ትስስር ጣሊያን ኢትዮጵያና የተባበሩት መንግሥታት የወከሉትን አራቱ ኃያላን አገራት የገቡት ውል ወይንም ግዴታ መሆኑን ከላይ ተገልጾአል። ውሉ ትስስርን የሚመሠርት እንጂ ተቃራኒውን መገንጠልን የሚያግፍ አልነበረም። የተባበሩት መንግሥታት ኤርትራ ከኢትዮጵያ እንድትገነጠል ቢፈልግ ኖሮ ድሮውንም ሁለቱን አገራት

---

[110] See Minasee Haile, "Legality of Secession: The Case of Eritrea," 8 Emory Int'l Law Review, 479 (1944).



በፌዴራል ግንኙነት ማስተሳሰር ሳያስፈልግ ኤርትራ ነፃና ሉዓላዊ አገር ባደረጋት ነበር።

ስለዚህ ሻቢያ በ1983 ዓ.ም. ኤርትራን ሲገነጥል በመጀመሪያ አራቱ ኃይላን መንግሥታትን የወከለው የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባዔ ኢትዮጵያና ጣልያን የተስማሙበት ውል ቀጥሎም የኤርትራ ፓርላማ የወሰነውን ውህደት አፍርሶአል። የፌዴሬሽኑ ዋነኛ ዓላማ የነበረው የኢትዮጵያ ወደ ባህር የመዝለቅ መብትንም ሰርዞአል። ሻቢያ ሕጋዊነት ቢከተል ኖሮ በሁለቱ አገራት መሃከል የነበረው የተባባሩት መንግሥታት መሥርቶት የነበረውን ፌዴሬሽን መልሶ ከዚያ በኋላ ሕዝቡ በፌደሬሽን ከኢትዮጵያ ጋር መቆየት ይፈልግ እንደሆነ አልያም ነጻነቱን መርጦ ሉዓላዊ አገር መሆን ይመርጥ እንደሆን በኢትዮጵያ ወይንም በተባበሩት መንግሥታት አዘጋጅነት ሕዝበ ውሳኔ (referendum) መካሄድ ነበረበት። ይህ አካሄድ ሊሠራ የሚችለው ግን የፌዴሬሽኑ ሃሳብ በሥልጣን ላይ ያለው ሕዋሐት/ኢሕአዴግ ከተቀበለው ብቻ ነበር።

በግንቦት 1983 ዓ.ም ኢህአዴግ አዲስ አበባን ሻቢያ አሥመራን ከተቆጣጠሩ በኋላ ኢሕአዴግ የሰላም ጉባኤ ያለውን ስብሰባ ጠርቶ በአብዛኛው የብሔር ብሔረሰቦች፣ ጥቂት የፖለቲካ ፓርቲዎችና የሲቪክ ማህበራት ተወካዮች በጉባዔው ተገኝተው ከአስተላለፉአቸው ውሳኔዎች አንዱ የኤርትራን ነጻነት ማፅደቅ ማለት ኤርትራን ከኢትዮጵያ መገንጠል ነበር። ከእነዚህ ሁሉ የስብሰባው ታዳሚዎች የአዲስ አበባው ዩኒቨርሲቲ ተወካይ ፕሮፌሰር አሥራት ወልደየስ ብቻ ኤርትራን ለማስገንጠል ሥልጣን የለኝም በማለት ከጉባኤው ውሳኔ እንደተለዩ የሚታወስ ነው።

የፕሮፌሰር አሥራት ወልደየስ* አቋም በፖለቲካውም ሆነ በሕጉ አንጻር ሲታይ በጽኑ መሠረት ላይ የቆመ ነበር። ጉባኤው

---

* አቶ ኢሳያስ አፈወርቂ በታዛቢነት በተገኙበት በአዲስ አበባው 1983 ዓ.ም "የሰላም ጉባዔ" ፕሮፌሰር አሥራት ወልደየስ አሰብ በታሪክም በሕግም የኢትዮጵያ የባህር በር ስለሆነች ወደ ኢትዮጵያ መካከል አለበት ባሉ ጊዜ አቶ ኢሳያስ "ታሪክና ሕግ የሚሉት ዝባዝንኬ ለትምህርት ቤት ክፍል ይተዉት። ይህ ፖለቲካዊ ጉዳይ በጦር ሜዳ ተፈትቶአል" በማለት ተሳለቁባቸው

አንዳንድ ብሔረሰቦች እንወክላለን ያሉ ግለሰቦች የሲቪክ ማህበራትና የጥቂት ፓርቲዎች መሪዎች ነን ባዮችና በጦርነቱ ደርግን አሸንፈው ሥልጣን የጨበጡ ድርጅቶች ተወካዮች የተገኙበት ሲሆን ማናቸውም በህዝብ የተመረጡ ሕዝቡን የሚወክሉ አልነበሩም። ይህም በመሆኑ ጉባዔው ምናልባት የአገሪቱን ሰላም ለማስጠበቅ የሽግግር መንግሥት ከማቋቋም ውጭ ሌላ በአገሪቱ ላይ አሳሪ የሆነ ግዴታ ውስጥ የሚከትት በተለይም የአገሪቱን አንዱን ክፍል የሚገነጥል ውሳኔ ለመወሰን ሥልጣን አልነበረውም። ጉባኤው ግን በሌለው ሥልጣን እንዲያውም የኢትዮጵያ ሕግ በመተላለፍ በሕዝብ ያልተመረጠ ስብስብ ቀርቶ ሕዝብን የሚወክል ፓርላማ እንኳን ሊያደርገው ሥልጣን በሌለው በአገር አንድነት ጉዳይ ውሳኔ ሰጠ። በአፄ ኃይለ ሥላሴ ከተደነገገው ከ 1923 ዓ.ም ሕገ መንግስት አንስቶ እስከ ደርግ ሕገ መንግስት አንዳቸውም አንዲት ጋት የኢትዮጵያ መሬት ለሌላ አሳልፎ መስጠት ወይንም ማንኛውም የኢትዮጵያ ክፍል ማስገንጠል አይፈቅዱም ነበር። ምናልባት አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ የኢትዮጵያ መሬት ለሌላ መንግስት ወይንም አገር ሊሰጥ የሚችለው መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ በሕዝበ ውሳኔ (Referendum) ሲስማማ ብቻ ነው።

ጉባኤው የሽግግር መንግሥት መሥርቶ ከተነሳ በኋላ የሽግግር መንግሥቱ ፕሬዚደንት አቶ መለስ ዜናዊ የጉባኤው ውሳኔ ለተባበሩት መንግስታትና ለአፍሪካ አንድነት ድርጅት አስተላልፈው ለኤርትራ እውቅና እንዲሰጡ ያሳወቁበት ደብዳቤ ከትጥቅ ትግሉ ያላነሰ ኤርትራን ያዋለደ በጣም ትልቅ ዋጋ ያለውና ሕወሓት ከብዙ ጊዜ ጀምሮ የተዋደቀለት የኤርትራ ነፃነት እውን የሚያደርግና ኤርትራን ሙሉ ሕጋዊ ሰውነት ሊያጎናጽፋት የሚችል ኤርትራ ከዓለም መንግሥታት ተርታ የመሰለፍ ዕድል የከፈተላት ታላቅ እርምጃ ነበር።

ኢትዮጵያ ለኤርትራ እውቅና ለመስጠት የመጀመሪያ አገር ስትሆን ከዚያም አልፋ ለተባበሩት መንግስታትና ለአፍሪካ አንድነት ድርጅት ኢትዮጵያ እውቅና መስጠትዋን ስታስታውቅ በመጀመሪያ በሰላም ጉባኤው ቀጥሎም በሽግግር መንግስቱ የተለያዩ የኢትዮጵያ ህግጋት ተጥሰዋል። ኤርትራን ማስገንጠል በጊዜው የነበረው የደርግ ሕገ መንግስትን የሚጥስ ቢሆንም የደርግ ሥርዓት



ሲደመሰስ የሥርዓቱ መሠረት የነበረው ሕገ መንግሥትም ተደምስሶ ነበር ማለት ይቻላል። ሆኖም ሌሎቹ የአገሪቱ ሕግጋት እንደነበሩ ሲሆኑ በተለይም በ1949 ዓ.ም የተደነገገው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ በጉባዔው ወቅትም ያገለግል እንደነበር የሚታወቅ ነው። ይኸው ሕግ ዛሬም ጥቃቅን ለውጦች ተደርገውለት እያገለገለ ነው። የኢትዮጵያ አካል የነበረችው ኤርትራን ማስገንጠል የዚሁ የወንጀል ሕግ ቁጥር 253 የሚጻረር ድርጊት ነው*።

ይህ ኤርትራን አስገንጥሎ እውቅና የሚያሰጥ እርምጃ ኢትዮጵያ የተቀበለችውና የዓለም አቀፍ ሕግ አካል የሆነው የአፍሪካ አንድነት ቻርተርንም ይጥሳል። ቻርተሩ በአንቀፅ 2 እንደ ደነገገው ከድርጅቱ ዓላማዎች አንዱ "የአባል አገራት ሉዓላዊነት፤ የግዛት አንድነትና ነፃነትን ማክበርና ማስከበር" ሲሆን የኢትዮጵያ የግዛት አንድነትን የሚንድ የሽግግር መንግሥቱ ኤርትራን አወቁልኝ ጥያቄ በኢትዮጵያ መንግሥት ጠያቂነት ባይቀርብ ኖሮ ጥያቄው በተባበሩት መንግስታት ወይንም በአፍሪቃ አንድነት ድርጅትና በሌላውም ዓለም አቀፍ ሕብረተሰብ ተቀባይነት አግኝቶ ኤርትራ ሕጋዊ ሰውነት ባልተጎናጸፈችም ነበር። የተባበሩት መንግሥታ ድርጅት አገራት እውቅና ለሰጡአቸው መንግሥታት በአባልነት መቀበል እንጂ እውቅና አይሰጥም። ስለሆነም የሽግግር መንግሥቱ ፕሬዚዳንት አቶ መለስ ዜናዊ ይሰጥ በማለት ለተባበሩት መንግሥታት የጻፉው ደብዳቤ የተባበሩት መንግሥታት የሕግ አማካሪን ሳያስገርም አይቀርም። ስለዚህ ኤርትራ በተባበሩት መንግሥታት እውቅና አገኘች ሳይሆን የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አባል ነው የሆነችው።

በጊዜው የአፍሪቃ አንድነት ድርጅት ዋና ጸሐፊ የነበሩት ታንዛንያዊው ሚስተር ሳሌም ሳሌም ኤርትራ የአፍሪቃ አንድነት ድርጅት እውቅና እንዲሰጣትና የድርጅቱ አባልም እንድትሆን

* አንቀጽ 253 እንዲህ ይላል "ማንም ሰው የህዝብን ያንድነት ሕብረት እንዲፈርስ የሚያደርግ ተግባር በመሥራት ወይንም ከንጉሡ ነገሥቱ መንግሥት ግዛት አገር ወይንም ሕዝብ ወይም ከፌዴሬሽኑ ተከፍሎ ወደ ሌላ መንግስት ሥርዓት ሕገ ወጥ በሆነ በማናቸውም ሁኔታ ይሁን የመሰለ ተግባር ያደረገ እንደሆነ ከአምስት ዓመት እስከ እድሜ ልክ ለሚደርስ በሚችል ፅኑ እስራት ወይም ነገሩ እጅግ ከባድ ከሆነ በሞት ፍርድ ይቀጣል" ይላል።

ኢትዮጵያ ጥያቄ ባቀረበች ጊዜ ዋናው ጸሐፊ ጭንቀት ውስጥ ገብተው እንደነበር ረዳታቸው የነበሩ አንድ ኢትዮጵያዊ ለዚሁ ጸሐፊ አጫውተውት ነበር። ዋና ጸሐፊ ሆነው የተመረጡት ቻርተሩ የሚያዝዘው የአባል አገራትን የግዛት አንድነትና ነፃነት ለማስከበር ሲሆን ይህንን ቻርተሩን የሚጥስ የአንድን አባል አገር መገንጣጠል እንዴት ሊያስተናግዱ እንደሚችሉ ግር ብሎአቸው ነበር። ቻርተሩ እንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ማስተናገጃ አንቀጽ ስለሌለውና ከዚህ በፊትም ተመሳሳይ ነገር ገጥሞአቸው ስለማያውቁ የሚየደርጉት ነገር ቢያጡ ጥቂት የአፍሪቃ መሪዎችን ያሉበት ቡድን አማከሩ። የመሪዎቹም ቡድን የኢትዮጵያ መንግሥት ኤርትራን አስገንጥሎ እውቅና ሰጥቶ ኤርትራ የአፍሪቃ አንድነት ድርጅት አባል እንድትሆን ካመለከተች መፈቀድ እንደሚኖርበት አሳሰቡ።

ልክ ከዛሬ 20 ዓመታት በፊት ከሶማሊያ ተገንጥላ ነፃነትዋን ያወጀችው ሲማሌላንድ ኢትዮጵያ በፍጹም የተሳናት ነፃ ምርጫ አድርጋ ገዢው ፖርቲ ተሸንፎ ኘሬዚዳንቱ አላንዳች ማንገራገር! እንኳን የ200 ሰው መገደል ቀርቶ አንድ ሰው ሳይታሠር ሥልጣናቸው ለተቃዋሚአቸው አስረከቡ። ይህም ቢሆን ዛሬ ሱማሌላንድ በአፍሪቃ የዴሞክራሲ ተምሳሌት ብትሆንም ምስቅልቅሏ የወጣው የሶማሊያ ሉዓላዊ አንድነት ላለመጋፋት ሲል የዓለም ሕብረትሰብ ሱማሌላንድን እስከዛሬ ዕውቅና ነፍጎአታል። የኤርትራ መገንጠልና ዕውቅና ማግኘት እንደ ዳቦ መቁረስ ቀላል ያደረገውና ከሦስት ሺህ ዓመታት በላይ ሉዐላዊነቷ ያስከበረች አገር ባንድ ቀን ጀምበር ሉዐላዊነቷ የተገረሰሰው የአገሩ መንግሥት ማለትም ሕወሐት/ኢሕአዴግ ለተገነጠለው አካል እውቅና ሰጥቶ ሌለውም የዓለም ሕበረተሰብ እውቅና እንዲሰግሳት በመማጠኑ ነው። ስለሆነም በኤርትራ መገንጠል ኢትዮጵያ ከተስማማችና ከገፋፋች አማራጭ ስለሌለ የአፍሪቃ አንድነት ድርጅትም ሆነ በጠቅላላው ዓለም አቀፉ ሕብረተሰብ የኢትዮጵያ የእውቅና ጥያቄ እንዲቀበሉ ተገድደው ጉዳዩ በዚሁ ተዘጋ።

ኤርትራ በተገነጠለችበት ጊዜ ከነበረችበት ሁኔታ ዛሬ ሱማሌላንድ ከአለችበት ጋር ሲነፃጸር በማንኛውም መስፈርት በዴሞክራሲ ምሥረታ ሕግና ሥርዓትን በማስፈን ሶማሌላንድ በጣም በተሻለ ደረጃ ላይ ትገኛለች። ያም ሆኖ ሶማሌላንድ እውቅና ተነፍጋለች። ስለሆነም ኢትዮጵያ ኤርትራን እውቁልኝ ጥያቄ ባታቀርብ ኖሮ ኤርትራ እውቅና ተነፍጎአት ዛሬ እንደ አገር ልትቆጠር አትችልም ነበር።

በኤርትራም በኩል ጦርነቱ ተጠናቀቆ ኤርትራ ከኢትዮጵያ ስትገነጠል በኤርትራ ሕዝብ ምርጫ ሳይሆን በአንድ ነፃ አውጪ ግንባር ውሳኔ ነው። ይህ ነፃ አውጪ ግንባር ሌሎች ተቀናቃኝ ቡድኖች በተለይም ጀብሃ በውሳኔው ሲሳተፍ አልፈቀደለትም።

ሻቢያ ኤርትራን ሲያስገነጥል የአገሪቱን ሰላም ከማስከበር ውጭ ሌላ ማንኛውም ውል ለመዋዋል የሚያስችል ሕጋዊ ሰውነት አልነበረውም። ኤርትራ ሕጋዊ ሰውነት ልትጎናጸፍና ውል ለመዋዋል የምትችለው ከዓለም ሕብረተሰብ ማለት ከመንግሥታት እውቀና ካገኘች በኋላ ብቻ ነበር። ነፃ አውጪው ግንባር ሻቢያ በራሱ ማንም ሳይወክለው በኤርትራ ሕዝብ ውሳኔ (Referendum) የማደራጀት ሥልጣን አልነበረውም። የኤርትር ጉዳይ በሕዝበ ውሳኔ እስኪወሰን ድረስ የኢትዮጵያ አካል በለነበረች ሕዝበ ውሳኔ ለማዳራጀት ሥልጣን የነበራት ኢትዮጵያ ስትሆን እንደ የተባበሩት መንግሥታት ደርጅትና የአፍሪቃ ሕብረት የመሳሰሉ ገለልተኛ አካለትም ሊያደራጁት ይችሉ ነበር ። ሕዝበ ውሳኔውን ሻቢያ ሲያደረጅ ለሕዝቡ ያቀረበው ጥያቄ ራሱ ሻቢያ የፈለገው መልስ ያሚያስገኝ ስለነበር ነፃነቱ መላው የኤርትራ ሕዝብ የተስማማበት ለመሆኑ ምንም ማስረጃ የለም።

ሻቢያ በሕገ ወጥ አካሄዱ ቀጥሉበት እንደ አውሮፖ አቆጣጠር በኤኘሪል 23-25, 1991 ዓ.ም በኤርትራ ውስጥ ለሕዝቡ ሌላ አማራጭ ሳይሰጠው "ነፃ መሆን ትፈልጋለህ አትፈልግም" የሚል ጥያቄ ብቻ ቀርቦለት ሕዝቡ በ99.8% (የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫን ይመስላል) ድምጽ ለመገንጠል ይሁንታውን ሰጠ ተባለ።

ከኢትዮጵያ ጋር በአንድ መልኩ ወይም በሌላ ተሳስረው ሲኖሩ የፈለጉ ኤርትራውያን ፍላጎታቸውን ሲገልጹ ሳይችሉ ስለቀሩ ሬፈረንደሙ በውን የኤርትራ ሕዝብ ፍላጐት ሙሉ በሙሉ ያንጸባረቀ ነበር ብሎ አፍ ሞልቶ መናገር አይቻልም። ቡተጨማሪም የኤርትራ መገንጠል ሌሎች ኢትዮጵያውንም የሚመለከት ጉዳይ እንደ መሆኑ መጠን ድምጽ መስጠቱ ኢትዮጵያውንን በሙሉ መሸፈን ነበረበት የሚሉም አሉ። የካናዳ አካል የሆነችዋ ኩዌቤክ ከካናዳ "ትለይ አትለይ" በሚባልበት ጊዜ

ድምጽ የሰጠው መላው የካናዳ ሕዝብ ነበር። በተጨማሪም በኤርትራ ጽምጽ የሰጠው ሕዝብ የቀረበለት አማራጭ "ነፃነት ወይንም ባርነት" የሚል እንድምታ ስለነበረው ለሕዝቡ ምንም ዓይነት አማራጭ ስላልተሰጠ ውሳኔው ሕጋዊ አልነበረም የሚሉ አሉ።

ምናልባትም የኤርትራ መሪዎች የግድ መገንጠልን ከመረጡ ሕግና ሥርዓት ተከትለው ነፃ ቢወጡ አዲሱ መንግሥት የዓለም አቀፍ ሕብረተሰብ ከበሬታ ይቸራቸው ነበር። ለዘለቄታውም ቢሆን ከኢትዮጵያ ጋር የሚያቀያይም ምንም ነገር አይኖርም ነበር። ያም ሆነ ይህ ኤርትራ ከህግ ውጭ ከኢትዮጵያ ተገንጥላለች፣ የኢትዮጵያ የባህር በርም ተዘጋ።

ቀደም ሲል እንደተገለጸው የኤርትራውያን ከኢትዮጵያ መለየት ምርጫቸው ከሆነ የወንድምና የእህት መለያየት እንደሚያሳምመው ሁሉ ኢትዮጵያውያን ቢያምማቸውም ተቀብለውታል። በዛሬው ወጣቶች ቋንቋ "ይመቻቸው" ከማለት ሌላ ምንም ማድረግ ስለማይችል ኤርትራውያን የወሰዱት እርምጃ ኢትዮጵያውያንን እንዳሳዘነ በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል።

የኤርትራ መገንጠል ለብዙ ኢትዮጵያውያን ጉዳያቸው የሚያደርገው ወንድምነቱና እህትነቱ ከመቅረቱ በተጨማሪ የባህር በራቸው እሰብን መነጠቃቸው ነው። በዚህ ጽሑፍም የኤርትራ መገንጠል የተነሳው ኢትዮጵያን ወደብ አልባ በማድረጉ ሲሆን ኢትዮጵያውያን ከዚህ ውጭ ከኤርትራውያን ጋር የሚያቃቅራቸው ምንም ነገር የለም።

ሆኖም የሁለቱ ወንድማማችና እህትማማች መለያየት ጉዳ እንደሆነ ብዙ ምክንያቶችን አስደግፎ መናገር ይቻላል። የአንድን አገር ክፍል ከሌላው መገንጠል የሚያስከትለው ጉዳት በመገንዘብ ይሆናል የኤርትራው ፕሬዝደንት አቶ ኢሣያስ አፈወርቂ ደቡብና ሰሜን ሱዳንን አስመልክቶ ለአንድ ጋዜጠኛ በሰጡት አስተያየት ከዚህ የሚከተለውን ብለዋል።

*"ከደቡብና በሰሜን ሱዳን መሃከል የተፈጠረው ሁኔታ በሰዎች ስህተት የመጣ አደጋ ነው ብዬ ነው የማስተምጠው። ሰሜንና ደቡብ ሱዳን መለያየት አልነበረባቸውም። የደቡብ ሕዝብ በዚሁ ደርሶበታል። እንደ አንደኛ ዜጋ የሚቆጠር አልነበረም። እንደ ሱዳናዊ ይህ መብቱ እንዲከበርለት መታገል መብቱ ነው። ከትግሉ ውጤት በኋላ በአዲሲቱ ሱዳን ከሰሜኑ ጋር አብሮ ቢኖር ጥሩ ነበር። ይህ የሆነው ለሱዳናውያን ታስቦ ሳይሆን ሱዳንን ለመበታተን ነው[111]።*

ይህ የአቶ ኢሣያስ አፈወርቂ አባባል ሕግን የተከተለ የበሰለ የአንድ የፓለቲካ ምሁር አስተያየት ነው። እንዲህ ዓይነት የበሰለ አቋም ምነው ወንድማማች ለሆነው ለኤርትራና ለኢትዮጵያ ሕዝብ ባመቻቹለት። በትልቅ ክብርና በፍቅር፣ በአንደኛ ደረጃ ዜግነት (ደረጃ ካለ) ከኢትዮጵያውያን ጋር ይኖሩ የነበሩ ኤርትራውያን ከኢትዮጵያ እንዲገነጠሉ ለብዙ ዓመታት የተዋጉ አቶ ኢሣያስ የኤርትራ መገንጠልና የሁለት ወንድማማች ሕዝቦች መለያየት ትክክል ነው ሲሉ፣ ተንቀው፣ ከሰው በታች ተቈጥረው አንዳንዴም በባርነት ይሸጡ የነበሩ ደቡብ ሱዳናውያን ነፃነታቸውን መጐናጸፍ አልነበረቸውም ማለታቸው በጣም አስገራሚ ነው። አቶ ኢሣያስ ምናልባት የኢትዮጵያና የኤርትራ መለያየት ስህተት ነበር፣ መለያየት አይገባቸውም ነበር፣የሚሉ ከሆነ አሁንም ኢትዮጵያውያን ኤርትራውያንን በእኩልነትና በወንድማማችነት መንፈስ እጃቸውን ዘርግተው እንደሚቀበሉአቸው ጥርጥር የለውም። እርሳቸውም እንዳሉት እንደ ሱዳኖች መለያየት ሁሉ የኢትዮጵያና የኤርትራ መለያየት በእርግጥም "በሰዎች ስህተት የመጣ" ነው እንጂ ሁኔታው አስገድዶ አይደለም። ምናልባት በዚህ ዓለም በፍጹም መለያየት ያልነበረቸውና የማይገባቸው ሁለት አገራትና ሁለት ወንድማማች ሕዝቦች ቢኖሩ ኤርትራና ኢትዮጵያ ናቸው ማለት ይቻላል።

[111] አዲስ አድማስ ቅጽ 10 ቁ 590 ቅዳሜ ሚያዝያ 29 ቀን 2003 ዓ.ም